# ምዕራፍ አንድ

## 1. የተውኔት ምንነትና ባህሪያት

t.me/BooksandYou

### መግቢያ

የተወደዳችሁ ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ስለተውኔት ምንነትና ስለባህሪያቱ እንመለከታለን፡፡ ድራማ (ተውኔት) የሰዎችን ስሜት ለመዳሰስና ለማንፀባረቅ የሚያስችል ልዩ መሳሪያ ነው፡፡ ድራማ ይተወናል፡፡ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ የሚያልፉባቸውን የተለያዩ አጋጣሚዎች አስቂኝ ወይም አሳዛኝ በሆነ መንገድ ያሳያል፡፡ የተውኔት ንግግሮችና ድርጊቶችም የሰዎችን የህይወት ኡደት እንደገና በመድረክ ላይ ይፈጥራሉ፡፡ በዚህም ምዕራፍ ተውኔት ምን እንደሆነና ተውኔትን ተውኔት የሚያስብሉት ጉዳዮችን እንዳስሳለን

### የምዕራፉ ዓላማዎች

የተወደዳችሁ ተማሪዎች የዚህ ምዕራፍ ዓብይ ዓላማ ምን ይመስላችኋል፡፡ ዓላማው የተውኔት ምንነትና ባህሪያትን ተንትኖ ማቅረብ ነው ካላችሁ ትክክል ናችሁ፡፡ ይህ ምዕራፍ የሚከተሉት ንኡሳን ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- ተውኔት ምን እንደሆነ መተንተን፡፡
- ተውኔት ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘሮች የሚለይበትን ነገር ማስረዳት፡፡
- ተውኔት ሊያሟላቸው የሚገባቸውን ነገር መተንተን፡፡

## 1.1 የተውኔት ምንነት

ወደ ምንነቱ ከመግባታችን በፊት እናንተ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ

- ተውኔት ምንድን ነው?
  ………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………………

ተውኔት ውህድ ጥበባዊ ቃል ሲሆን በውስጡ በተዋንያን የሚተወኑ ግጭቶችን፣ ድርጊቶችንና፣ የሚፈጠሩ ድባቦችን የያዘ ሲሆን በመድረክ ላይ ከተመልካቾች ፊት የሚተወን ነው፡፡ ተውኔት ድራማ እና ትያትር በሚሉ ተጨማሪ መጠሪያዎችም ይታወቃል፡፡

ተውኔት የሚለው ቃል በእንግሊዘኛ "ኘሌይ" የሚለውን ቃል በመተካት ስራ ላይ የዋለ ሲሆን ተውኔት ተዋናይ ከሚለው የግእዝ ቃል የረባ ነው፡፡ በቁም ጨዋታ የሚለውን ትርጉም ያመለክታል፡፡ ከዚህ ቃል በማርባት የቲያትሩን ድርሰት ተውኔት፣ ፀሐፊውን ፀሃፊ ተውኔት ፣ እንዲሁም ቲያትሩን በመድረክ ላይ የሚጫወቱትን ሰዎች ተዋናይ ብሎ መጥራት የተለመደ ሆኗል፡፡

በሌላ በኩል ቲያትር የሚለውን ቃል ከውጪው ቋንቋ እንዳለ ብንቀበለውም ባእድነቱ ሳይሰማን ተውኔትን ለማመላከት እንጠቀምበታለን፡፡ ድራማ የሚለውንም ቃል እንዲሁ በመድረክ ላይ የሚቀርቡ ተውኔቶችን ለመግለጽ እንጠቀምበታለን፡፡ ምንም እንኳን ተውኔት ፣ ትያትርና ድራማ በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢኖራቸውም በዚህ ሞጁል በተለዋዋጭነት እንጠቀምባቸዋለን፡፡ የተለያዩ ባለሙያዎች ስለተውኔት ምንነት ብዙ ብለዋል፡፡

t.me/BooksandYou

ከነዚህ ምሁራን መካከልም እስቲ ለአብነት የተወሰኑትን እንመልከት

> ተውኔት የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ በየጊዜው በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ታሪክ ነው፡፡ ተውኔት (ድራማ) የሚለው ቃል የተገኘው "ድራን" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም "ማድረግ" ወይም "መከወን" ማለት ነው፡፡ የተውኔት ምንነት በአጭሩና እምቅነት ባለው መልኩ አሪስቶትል ሲገልጽ "ተውኔት ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው፡፡" ይለዋል፡፡ በአጠቃላይ ተውኔት የሚለው ቃል ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አራት ፍችዎች የያዘ ነው፡፡
>
> 1. ሙሉ የተውኔት ድርሰት
> 2. የተውኔት ትምህርት መስክ
> 3. ከተውኔት ድርሰት አንዱ ክፍል ወይም ትዕይንት
> 4. መድረክ ላይ የተውኔት ዝግጅት የሚሉ ትርጉሞችን ያካትታል፡፡ (ፋንታሁን እንግዳ 199፣9-10)

አያልነህ ሙላቱም ተውኔትን በተመለከተ የሚከተለውን ብሏል፡፡ "ድራማ የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ትርጉሞች የሚሰጠው ጥበብ ሁኗል፡፡ ገፀባህሪያት በተላበሱ ተዋንያን የሚተረጎም ቃለ - ተውኔት ድራማ መባሉን አብዛኛዋቹ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ድራማ ከሀዘን እስከ ድንቃይ፣ ከአስቂኝ እስከ ቧልታይ ያሉትን የቴያትር ዘርፎች አጠቃሎ የያዘ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡" (1992 ፣ 3)

ደበበ ሰይፉም በበኩሉ ከተውኔት ጋር በተያያዘ የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡

> የቲያትር ጥበብ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ካለፉት ማህበረሰቦች የወረስዎቸውን ቁሳዊና ህልዮታዊ ትውፊቶች ÷ በየዕለቱ ውጣ ውረዳቸው ያካበቷቸውንና ያዳበሯቸውን ባህሎች ፣ ልምዶች፣ እሴቶች በውስጡ ያንፀባርቃል፡፡ የጥበቡ ቀማሪዎችም እኒህን ሁኔታዎች እስከ ውሑዱና መንታ ገፅታቸው (አንድነታቸውና ተቃርኖአቸው) ከማህበረሰቡ ሕይወት ውስጥ

እየቀነሱ ለተደራሲያን ያቀርባሉ ወደ ቤተ ቲያትር እሚታደሙትም ተደራሲያን ፍዝ ተመልካቾች ሳይሆኑ በየልቦናቸው የነገሩን (የቲያትሩን) ውጣ ውረድ እሚከታተሉ የሕይወት ተርጓሚዎች ተሆኑት ተዋንያን ጋርም በየልቦናቸው የሚያወያዩ ናቸው፡፡ (1973 ፣ 7)

ከላይ ከተዘረዘሩት የምሁራኑ ብያኔዎችም ተውኔት የሌሎችን ባህሪ፣ ሁናቴ እና ንግግር ለጊዜው ወርሶ ለተዝናኖት ፋይደው ሲባል አንድ አይነት ተግባርን ከቋንቋ ጋር አገናኝቶ የመጫወት ጉዳይን የሚመለከት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ተውኔት፣ ትያትርና ድራማ የሚሉትን ስያሜዎችም በተለዋጭ እንደሚጠቀም ከምሁራኑ ማብራሪያ ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተውኔት ህይወት የሚዘራው እንደ ጸሃፊ ተውኔት፣ ተዋናይ ፣ አዘጋጅ፣ የመድረክ ባለሙያዎች ወዘተ… በመሳሰሉ ጥበበኞች ውህደትም እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ተውኔት ከቃላት በመሰራቱ የስነፅሁፋዊ እና ገፀባህሪያት በተግባር ስለሚያሳዩት የመከወን ጥበቦች ቅንጅት ነው፡፡ ተውኔት በስድ ወይም በግጥም የሚዘጋጅ ሆኖ በምልልስና በድርጊት የሚተርክ የፈጠራ ትረካ (Story) ነው፡፡

t.me/BooksandYou

## 1.2 የተውኔት ባህሪያት

ወድ ተማሪዎች ወደ ተውኔት ባህሪያት ከመግባታችን በፊት እናንተ የሚከተለውን ጥያቄ ለመመለስ ሞክሩ፡፡

> ➢ ተውኔት ከሌሎቹ የስነፅሁፍ ዘርፎች በምን ይለያል?
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………

ተውኔት ከሌሎች የስነፅሁፍ ዘርፎች የሚለይባቸው የተለያዩ ባህሪያት አሉት፡፡

## 1.2.1 ቀውስ ፣ ውኸርንብርና ግራ መጋባት የተሞላ ነው፡፡

ይህ ሐሳብ በተውኔት ውስጥ ከሚገኝ ግጭት አፈጣጠር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ ገፀባህሪያት ቀውስ ዉስጥ የሚገቡብ በፍጥነት ነው፡፡ እንደ ልብወለድ ተውኔት ባህሪው እያዘገመ እንዲሄድ ስለማይፈቅድለት ብዙ ጊዜ የተውኔት ታሪክ የሚጀምረው በግጭት ፣ ግብግብ እና ግራ መጋባት ነው፡፡ ተውኔት የወዲያውነት ባህሪ አለው፡፡ ገፀባህሪያቱን ከነችግራቸው በተውኔት መጀመሪያ እንተዋወቃቸዋለን፡፡ ከመነሻው ተመልካቹ ችግሩን ተዋውቆ ግጭቱ ሲባባስና ሲጦዝ ማየት ይናፍቃል፡፡ ሂደቱ ፋታ በማይሰጥ መካለብ የተሞላ በመሆኑም ገና ከመጀመሪያው ገፀባህሪያትንና ተመልካቶችን ለተጋፍጦ ያጋልጣል፡፡

## 1.2.2፡- በቡድን ይዘጋጃል

ተውኔት በብዙ ሰዎች ትብብርና ጥረት ይዘጋጃል፡፡ ለተውኔት ህያውነት ብዙ ሰዎች የተለያዩ ሚናዎችን ይጫወታሉ  የመድረክ፣  የመብራት፣ የድምፅ ባለሙያዎች በተለያዩ ጥበቦች ያጅቡታል ወዘተ… ስለዚህ የተውኔት ህልውና በብዙ ሰዎች ተፅእኖ ስር የወደቀ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ደበበ ሰይፉ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> የቲያትር ጥበብ የብዙ ጥበቦች ጉባኤ ነው - መነሽሪያ፡፡ ሙዚቀኛው ÷ ሠዓሊው ÷ ፀሐፊው ተውኔቱ ÷ የመብራትና የድምጽ ባለሙያዎች  …  ሌሎችም የሌሎች ጥበቦች ቀማሪዎች ባንድ አብረው ነው ይህን ጥበብ እሚከሽኑ የአያሌ ተደራሲያን ልብ የማረከ ደማቅ ጥበብ መሆኑም ከልዩ ልዩ ጥበቦች ቀለማት በመሰራቱ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይሁንና በሌላ አንፃር ነገሩን ስናይ ÷ ይህ የደማቅነት ምክንያቱ የደብዛዛነት ምክንያቱም ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ እንገነዘባለን፡፡ የብዙ ጥበቦች ባንድ እስክስታ መውረድ ነው የቲያትር ጥበብ ብንል ÷ ከብዙዎቹ ጥበቦች አንዱ እንኳን ምት ባይጠብቅ ÷ ሌሎቹን ታዳሚ ጥበቦች ብሎም ድምሩን የትያትሩን ጥበብ እንደሚያስነክሰው እንረዳለን፡፡ አያሌ ሙያተኞች ቁጭ ብድግ ሲሉ የከረሙበትም የቲያትር ድግስ ተጋባዡን ተደራሲያን ሳያስደስት ይቀራል፡፡ የተደራሲያን አለመደሰት ደሞ አንዱና ዋናው የጥበቡ አለመሳካት ምልክት ነው፡፡ (1973 ፣ 9)

ከዚህ የምንረዳው ከሌሎች የጥበብ ዘሮች በተለየ የተውኔት ስኬት በአንድ ሰው ጀርባ ላይ የወደቀ አለመሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ልቦለድ ጥበባዊ ልቀቱም ሆነ ውድቀቱ የሚያያዘው ከደራሲው ጋር ነው፡፡ ግጥምም ከገጣሚው፣ ስዕልም ከሰዓሊው ፤ በተውኔት ግን የተውኔት ፅሁፍ ብቻ ጥሩ መሆን ተውኔቱን ጥሩ አያደርገውም ፣ አዘጋጁም ጥሩ አድርጐ ማዘጋጀት አለበት ፤ ተዋናዮቹም ሊዋጣላቸው  ይገባል፣ ወዘተ…፡፡

## 1.2.3፡- የተዘወተረ መሠረታዊ መዋቅር አለው

የተለያዩ የስነፅሁፍ ዘሮች እሚዋቀሩበት ስርአት ወይም ቅርፅ መዋቅር ይባላል፡፡ ተውኔትም እንደሌሎቹ የስነፅሁፍ ዘሮች ሁሉ የራሱ የሆነ የተዘወተረ መዋቅር አለው፡፡ ይህ መዋቅሩም ትዉቂያ ፣ትውስብና ልቀት በሚሉ ክፍሎች ይታወቃል፡፡

በትውቂያ የተውኔት ባለታሪኮች ፣ ግጭቱን ፣ ወዘተ… የምንተዋወቅበት ክፍል ነው፡፡ ስለትውቂያ ፈንተሁን እንግዳ የሚከተለውን ብሏል፡፡

> “በተውኔቱ የመጀመሪያ ክፍል ገፀ ባህሪያት አብይና ንኡስ ሳይል በአብዛኛው ሁሉም የታሪኩ ተሳታፊዎች ይተዋወቃሉ፡፡ ከዚህም ጋር የመቼቱ አይነት ይገልፃል፡፡ የተውኔቱ ግጭት ፤ ርዕስ ጉዳይ ፣ እና ድባብ እንዲሁ በተውኔቱ የመጀመሪያ ክፍል ለአንባቢ ወይም ለተመልካች ከሚተዋወቁ አላባዎች መካከል ናቸው፡፡” (1999 ፣ 59)

የተውኔት ትውቂያ ክፍል ብዙ ጊዜ አንድ የተምታታ ነገር ያሳያል፡፡ የዚህ የተምታታ ነገር ምክንያትንም ያሳውቃል፡፡ ትውውቁም እንደሌሎች የስነፅሁፍ ዘሮች አዝጋሚ ሳይሆን ፈጣን ነው፡፡ ገፀባህሪያቶቹን የምንተዋወቀው በግጭት ውስጥ እንዳሉ ነው፡፡

ሁለተኛው የተውኔት መዋቅራዊ ክፍል ትውስብ ይባላል፡፡ ይህ ደሞ የገፀባህርያቱ ግጭት የሚወሳሰብበትና በገፀባህሪያቱ መካከል ያለው ልዩነት የሚሰፋበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል በተውኔቱ መጀመሪያ በተምታታው ነገር የተፈጠሩ ምስቅልቅሎች ጐራ ለይተው የሚፋለሙ ወገኖችን ይፈጥራሉ፡፡ ገፀባህሪያት ይፋለማሉ ፤ ይህ ክፍልም በተውኔት ትልቅ ስፍራ ነው፡፡ ትውስብን በተመለከተ ዝኒ ከማሁ ያሉትን እንመልከት

> ትውስብ ከእውቂያ አሰረጫጨት በመቀጠል የሚመጣ የተውኔታዊ ሴራው ወሳኝ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል አስቀድሞ የተመሰረተውና በሚገባ የተዋቀረው ግጭት ልብን በሚሰቅል መልኩ እስከ ጡዘት ድረስ ይወሳሰባል፡፡ በትውስብ የሚከሰቱ ንዑስ ግጭቶች የሉም ባይባልም እንኳን ትኩረት የሚሰጠው አስቀድሞ በእውቂያ ክፍል ለተፈጠረው አብይ ግጭት ነው፡፡ በዚህ አብይ ግጭት ዙሪያ ጐራ ለይተው በሚገጥሙት አቀንቃኝና ፀረ-አቀንቃኝ ገፀ-ባህሪያት አማካይነት የፍልሚያ ደረጃው ይንራል፡፡ ትውስብ በዘልማዳዊ ተውኔታዊ መዋቅር በዋናነት ከሚከተቱት ከእውቂያና ልቀት ክፍሎች መሃል እንደመገኘቱ የተውኔቱን መጀመሪያና መጨረሻ ክፍሎች ይይዛል፡፡ (1993 ፣57)

ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ክፍልም ልቀት ሲባል ፣ አሸናፊና ተሸናፊው የሚለይበት ነው፡፡

## 1.2.4 ተመድራኪነት

ተውኔት የሚፃፈው ለአንባቢ ሳይሆን ለመድረክ ታስቦ ነው፡፡ በተመልካቾች ፊት በተዋናዮቹ አማካይነት በመድረክ ላይ ይቀርባል ነፍስ የሚዘራውም በዚህ ወቅት ነው፡፡ ከተውኔት የተመድራኪነት ባህሪ ጋር በተያያዘ ደበበ ሰይፉ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ፀሐፊ ተውኔቱ ከመድረክ ውጭ ባለው ነዋሪነቱ መታበዩን ሳይነቅፍ ÷ የቲያትር ጥበብ ሙሉ እሚሆነው ÷ መደበኛ መልኩንም አገኘ እሚባለው በመድረክ ላይ በሚድረግ ዝግጅት አማካኝነት ብቻ ነው ሲሉ በብርቱ የሚከራከሩ አንዳንድ ሐያስያንም አሉ፡፡ በእርግጥ ተውኔት ህያው ስነፅሁፍ ነው መባሉ በመድረክ ላይ በሚተጋ ብርሃን አማካይነት ግዙፍ ነስቶ በመታየቱ ነው፡፡ ይህንንም ማንም አሌ አይለውም፡፡ የጥበቡ ተወካይ ሊሆን የሚችልም ማለፊያ ፀሐፊ ተውኔት ድርሰቱን ሲደርስ የመድረክ ጣጣ ጥያቄዋችንም ሊመልስ የቻለ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመፅሐፍ ጥራዝነቱ ብቻ ማቆየት ÷ ቀድም ብለን የጠቀስነውን የጥበቡን ሰፊ እዩኝታም ማጥበብ ይሆናል፡፡ (1973 ፣ 15)

ከዚህ የምንገነዘበው ተመድራኪነት የተውኔት አይነተኛ ባህሪ መሆኑን ነው፡፡ ከሌሎች የስነፅሁፍ ዘሮች የሚለየውም በዚህ ባህሪው ነው፡፡ ፀሐፊ ተውኔቱ ሲፅፍ መድረኩን እያሰበ ነው፡፡ የመድረኩን ገፅታ ብቻ ሳይሆን የተዋናዮቹን እንቅስቃሴ፣ አገባብና አወጣጥ፣ ታሪኩን ፣ መቼቱን ሁሉ ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

## 1.2.5፡- በድርጊት የታጀበ የአተራረክ ብልሃት አለው

በተውኔት ታሪክ ነጋሪዎቹ ገፀባህሪያት ናቸው፡፡ የተውኔት ጥበብ የሚገለፀው በተዋናዮቹ ድርጊትና በቃለ ተውኔት ነው፡፡ የመድረኩ ቁስ ፣ የመድረኩ ገጽታ ፣ የተዋናዮቹ መዋቢያና አልባሳት ፣ ግብአተ ድምፁ ከተዋናዮቹ ድርጊት ጋር በመሆን ለታዳሚው ታሪኩን ያደርሳሉ እንደ ልብ ወለድ ተውኔት የተደረገውን ነገር ሁሉ የሚተርክ ታሪክ ነጋሪ የለውም ወይም በተውኔቱች ሶስተኛ መደብ ተራኪ አያስፈልግም፡፡ የተዋናዮቹ ድርጊት ነው ታሪኩን የሚያራምደው፡፡

## 1.2.6፡- ትኩረተ ብዙሃን

አንድ ተውኔትን ተውኔት ከሚያስብሉት ጉዳዮች አንዱ ህዝባዊ ጉዳዮችን ማንሳቱ ነው፡፡ በተውኔት የሚነሱ ርዕስ ነገሮች ተደራስያኑ በስሜቶቻቸው ንቃት ሊከታተሉዋቸው የሚችሉዋቸው መሆን አለባቸው፡፡ ተውኔቶችን ለመረዳት የተለያየ ገጠመኝ ወይም እውቀት ሊጠየቅ አይገባም፡፡ በተውኔት እሚተላለፉ ጉዳዮች ተመልካቹ የራሱ አድርጎ ሊመለከታቸው የሚችላቸው መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ተውኔት ትኩረት ብዙሃን እንዲኖረው ህዝባዊና የሰው ልጅን መሰረታዊ ጉዳዮች ማንሳት ይኖርበታል፡፡

ለምሳሌ፡- ቅናት

ስስት

በቀል

ተንኮል

ተውኔት ለተደረሲያኑ በሩን ክፍት ማድረግ አለበት ለዚህም በተውኔት ውስጥ የሚተላለፈው ማህበራዊ ሐቅ ለተደራሲያኑ ምናብ ቅርብ መሆን አለበት ወይም ከተደራሲያን የነባራዊው አለም ልምድ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት ምክንያቱም የምናብ መሰረት ይኸው የገሀዱ ዓለም ስለሆነ፡፡

በተውኔት የሚቀርቡ የተለያዩ ሁነቶች ተመልካቹ የተዋናዩ ፣ የግለሰብ ወይም የአንድ ማህበራዊ ቡድን ብቻ አድርጎ ሳይሆን የራሱ አድርጎ ሊመለከታቸወ ይገባል፡፡ ታዳሚው በሚመለከተው ቲያትር ውስጠ ራሱን ፣ ቤተሰቡን ፣ ጉረቤቱን ወይም የሚያውቃቸውን ሰዎችና ጉዳዮች ሊያስታውስ ይገባል፡፡

## 1.2.7 ግልፅነትና ቀጥተኝነት

ተውኔት ከተደራሲው እዉቀት በላቀ መልኩ የሚዋቀር አይደለም፡፡ ተውኔትን ለመታደም ወደ ቲያትር ቤት የሚመጣው ታዳሚ የተለያየ ዳራ ያለው ነው ስለዚህ ተውኔት ይህንን ከግንዛቤ አስገብቶ ቋንቋው ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የትያትር ታዳሚዎችም ትያትሩ ህዝብዊ ጉዳዮችን እስካስነሳ ድረስ ይህ ገጠመኛቸው ለመታደም በቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ደበበ ሰይፉ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ”እንደ ሙዚቃ ÷ እንደ ስእል ተደራሲ ሁሉ ÷ የቲያትር ተደራሲያንም የተማሩ ÷ ማለት ፊደል የቆጠሩ ብቻ መሆን የለባቸውም፡፡ ወደ ቤተ ቲያትር ገብተው በመድረክ ላይ

እንሚሆነውን ÷ እሚደረገውን ለመረዳት የሕይወት ልምዳቸው በቂ ነው የማህበረሰብ-
ገጠመኛቸው፡፡ በዚህ መነሻነት ጥበቡ ሰፊ እዩኝታ አለው፡፡” (1973 ፣ 9)

ስለዚህ ተውኔት የተለያዩ ተመልካቶች የሚታደሙበት ስለሆነ ቋንቋውም ሆነ ቅንጅቱ ግልፅና ቀጥተኛ መሆን አለበት፡፡ ከዚህም በላይ ተውኔት እንደሌሎች ጥበባት ለምሳሌ እንደ ልብወለድ ተደራሲው ያልገባውን ቋንቋም ሆነ ነገር ሂደት የሚያሰላስልበት ጊዜ የለውም፡፡ ታሪኩን የሚያገኘው መድረክ ላይ ተዋናዮቹ ከሚያደርጉትና ከሚናገሩት ነገር ስለሆነ ሙሉ ትኩረቱን መድረኩ ላይ አድርጐ መከታተል አለበት፡፡ ስለዚህ የቲያትር ቋንቋ የማያዳግምና እና እጥር ምጥን ያለ መሆን አለበት፡፡

## 1.2.8 የታሪኩ አነሳስና የመረጣ ሁኔታው ለየት ይላል

ተውኔት ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ለመግባት የጊዜም የቦታም ገደብ አለበት፡፡ በመድረክ ላይ በተወሰነ ሰአት ውስጥ የሚቀርብ ስለሆነ መረጣው ሚዛን በሚደፉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ታሪኩ ሀል ጊዜ ከመካከሉ ይጀምራል፡፡ ቲያትር ምን ቢረዝም ከ3 ሰዓት መብለጥ የለበትም በዚህ ጊዜ ውስጥ ሙሉ የሆነ ማህበራዊ ገጠመኝን ለታዳሚው ለማድረስ ዋና ዋና የታሪኩ አካላትን አላስፈላጊ ዝርዝር ውስጥ ሳይገባ ያዋቅራል፡፡ ተውኔት እምቅነት ሊኖረው ይገባል ብዙ ተጓዳኝ ታሪኮች አያስፈልጉትም፡፡ አስፈላጊ የሆነዉን ግን የተለያዩ ስልቶችን ለምሳሌ ምልሰትና መነባንብን በመጠቀም መግለፅ ይችላል፡፡

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ አንድን ትምህርት እዚህ ላይ አጠናቀናል በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጥህን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦልሃል የተነሳውን ነጥብ የምታውቀው ከሆነ ይህን ምልክት አድርግ [√] ነጥቡን ካላወቅከው ደግሞ የ [X]
ምልክት አድርግና እንደገና ተመልሰህ ትምህርቱን ከልስ

1. ስለ የተውኔት ምንነት መግለፅ እችላለሁ፡፡ ............ [ ]
2. የተውኔት ባህርያትን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ [ ]
3. ተውኔት ከሌሎች የኪነጥበብ ዘርፎች በዋናነት የሚለይበትን ጉዳይ ዘርዝሬ ማስረዳት እችላለሁ፡፡--- [ ]

**ግለ ፈተና አንድ** t.me/BooksandYou

በምዕራፍ አንድ ያቀረብነውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተለው ፈተና ተዘጋጅቷል። በትምህርቱ ውስጥ የቀረበውን ገለፃ ሳትመለከት ጥያቄዎቹን መልስ። ጥያቄዎቹን ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ በሞጅዩሉ የመጨረሻዎቹ ገፆች ካቀረብንልህ መልሶች ጋር አመሳክር።

***መመሪያ አንድ*** ፡- ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሽ።

------------------1. በተውኔት ታሪክ ታሪክ ነጋሪዎቹ ገፀባህርያት ናቸው።

------------------2. ተውኔቶችን ለመረዳት የተለየ ዕውቀት ወይም ገጠመኝ ያስፈልጋል።

------------------3. ተውኔተ የስነፅሁፋዊ እና የመከወን ጥበቦች ቅንጅት ነው።

------------------4. በትውቂያ በገፀባህርያት መካከል የተፈጠረ ግጭት ሲሰፋ ይታያል።

***መመሪያ ሁለት***፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስፈላጊውን ዝርዝር ሳታስቀር ባጭሩ መልስ።

1. የተለመዱት የተውኔት መዋቅራዊ ክፍሎች ምን ምን ናቸው?

ሀ-----------------------------------------------

ለ-----------------------------------------------

ሐ-----------------------------------------------

2. ከተውኔት ባህርያት ውስጥ አራቱን ዘርዝሩ።

ሀ-----------------------------------------------

ለ-----------------------------------------------

ሐ-----------------------------------------------

3. የተውኔት አይነተኛ ባህሪ ምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተውኔት አጀማመር

### መግቢያ

የተወደዳችሁ ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ስለ (ተውኔት) ድራማ አጀማመር ይሆናል፡፡ ተውኔት ድራማ የሚለውን ቃል የሚተካ ቃል ነው፡፡ እነዚህ መጠሪያዎችም በተለዋጭነት ተመሳሳይ ትርጉም ይዘው ሲሰራባቸው ይታያል፡፡ እኛም በዚህ ሞጁዩል እነዚህን ስያሜዎች በተለዋጭ እንጠቀምባቸዋለን፡፡

### የምዕራፉ አላማዎች

የተወደዳችሁ ተማሪዎች የዚህ ምዕራፍ አብይ ዓላማ ምን ይመስላችኋል፡፡ አብይ አላማው የድራማ አጀማመርን ተንትኖ ማቅረብ ነው፡፡ ካላችሁ ጥያቄውን መልሳችኋል፡፡ ስለ ድራማ አጀማመር ከማየታችን በፊት የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡

ተውኔት በአለም አቀፍ ደረጃ መቼ እና እንዴት ነው የተጀመረው?
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------------------------------------------------------
------------------------------------------------------------

ጥሩ ሙከራ ነው፡፡ አሁን ደግሞ የኔን ምላሽ ላቅርብ

## 2.1. የተውኔት አጀማመር በአለም አቀፍ ደረጃ

ድራማ የሚለው ቃል የመጣው ድርጊት (action) የሚል ፍቺ ካላው የግሪክ ቃል ነው፡፡ ድርጊት ሲኖር የሆነ ነገር ይፈጠራል ፤ ለምሳሌ አንድ ሰው እግሩ ቢሰበር፣ ሁለት ሰዎች ቢጋቡ ወይም ልጅ ቢወልዱ እነዚህ ድርጊቶች ቀጥሎ በሚፈጠረው ነገር ላይ ውጥረት ወይም አድናቆት ይፈጥራሉ ይህ ደሞ ታሪኩን በድርጊት ወይም በድራማ የተሞላ እንዲሆን ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ድራማ የሚለው ቃል አንድምታም ይህ ነው፡፡

ተውኔት በጣም ረጅም ታሪክ ያለው የስፅሁፍ ዘርፍ ነው ጥንት ግሪኮች የአኪላስ (Aeschylus) እና (Sophocles) ስራዎችን ከመተወናቸው በፊት ተውኔት ነበር፡፡ ጥንት በአለማችን ላይ ይከውኑ ነበር የተለያዩ ሃይማኖታዊ ስርአቶች (Religious rituals) እና ስነቃላዊ በዓላት (folk Celebrations) የድራማ ባህሪ ነበራቸው፡፡ እነዚህም የድራማ ጥልቅ መሰረቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ደበበ ሰይፉ የትያትር ጥበብ ከፀሐፊ ተውኔቱ አንፃር በሚለው መፅሐፋቸው ያሰፈሩትን እንይ

> የትያትር ጥበብ የሰው ልጆች ሕይወት ፥ በመድረክ ላይ የሚገለፅበትና የሚተረጐምበት አንዱ አብይ የኪነጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ጥበብ መደበኛ መልኩን አገኘ እሚባለው በግሪክ

ሀገር አስኪለስ ፥ “ አቤት ባዮቹ “ የተሰኘውን ተውኔቱን ባቀረበበት በ496 (እ. ኤ. አ) ላይ ነው ቢባልም ፍንጩ ግን ከዚያ በፊት በነበረ ቀደምት ዘመን በጥንታውያን ግብፆች የመቃብር ስርአት ወግና በቅድመ ታሪክ ጥንታዊያን ሕዝቦች የየዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኝ እንደነበር ይታወቃል። (1973 ፥ 7)

የምዕራቡ ዓለም ተውኔት ምንጭ ጥንታዊቷ ግሪክ ናት። የአቴንስ ከተማ የትያትር ባህል ሦስት የተውኔት ዘውጎችን ፈጥሯል። ትራጄዲ፣ ኮሜዲና ሳታየር። ምንም እንኳን አጀማመራቸው አከራካሪ ቢሆንም በ5 መ.ክ.ዝ ከክርስቶስ ልደት በፊት ዲዮኒሲዮስ “Dionysus” የሚባለውን ጣኦት ከማክበር ጋር በተያያዘ በሚዘጋጀው ፌስቲቫል ላይ በሚደረጉ ውድድሮች ተቀባይነትን እንዳገኙ ይነገራል።

የተለያዩ የታሪክ ተመራማሪዎች ብዙ የጥንት የግሪክ ድራማቲስቶችን ቢዘረዝሩም “ቴስፒስ“ (Thespis) የሚለውን ስም ግን ብዙ ጊዜ አያነሱትም። ቴስፒስ ከመዝፈን ይልቅ የሚናገር፣ እራሱን ወክሎ ከሚናገር ይልቅ ገፀባህሪያትን የሚያስመስል አካል ወይም “ተዋናይ” የፈጠረ ሰው ነው። የመጀመሪያው ተዋናይም ነው። ከጥንት የግሪክ ድራማዎች ብዙዎቹ ተሟልተው አልተገኙም። አሁን አለንበት ዘመን መድረስ የቻሉትም የአምስቱ የግሪክ ትራጀዲ ፀሐፊዎች አኪለስ (Aeschylus)፣ሶፎክልስ(Sophocles)፣ ኢዮሪፒደስ (Euripides) አሪስቶፓንስ (Aristophanes) እና ሚናንደር (Menander) ስራዎች ናቸው።

በ472 ከ.ክ ልደት በፊት የዲዮኔስያ (Dionysia) ውድድር ሽልማትን ያሸነፈውን የአስኪለስ አቤት ባዮቹ (The persians) የመጀመሪያው ድራማ እንደሆነ ይናገራል። ከዚህ በኋላ በ50 ዓ.ዓ ከ.ክ ልደት በፊት ወደ ተለያዩ የግሪክ ክልሎች የሮማ ሪፐብሊክ መስፋፋትን ተከትሎ ሮም ከግሪክ ድራማ ጋር ተዋቀረች። በሮም አማካኝነት ቲያትር በመላው አውሮፖ፣ በሜድትራኒያን አካባቢ ተስፋፋ ከዚያም እንግሊዝ ደረሰ ምንም እንኳን የግሪክ ድራማ በሮም ሲተወን ቢቆይም 240 ዓ.ዓ ከ.ክ.ል በፊት ሮም የራስዋን መደበኛ የሆነ ድራማ እንደጀመረች ይናገራል። ከመጀመሪያዎቹ የሮም ቲያትሮች መካከልም ሊቪስ አንድሮኒከስ የፃፋቸው ኮሜዲዮችና ትራጀዲዎች ይጠቀሳሉ።

በእንግሊዝ ውስጥም ድራማ በ16ተኛው ና 17ኛው መ.ክ.ዘ አብቧል። ብዙዎቹ ድራማዎች የተፃፉት በግጥም ሲሆን ከሼክስፒር በተጨማሪ ክርስቶፈር ማርሎው፣ ቶማስ ሚድልተን እና ቤንጆንስን ይጠቀሳሉ።

ወደ ዘመናዊው ድራማ ስንመጣም በ19ኛው ክ.ዘ ኖርዌያዊው የድራማ ሰው ሄነሪክ ኢብሰን (Henrik Ibsen) እና በ20 ክ.ዘ የጀርመናዊው ቤሮልት ብሬች (Bertolt Brecht) አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። እነዚህ ሰዎች ለብዙ ፀሐፊ ተውኔቶች ምሳሌ የሆኑና መነሳሳትን የፈጠሩ ናቸው። ስራዎቻቸውም ዘመናዊና እውናዊ ነበሩ።

ሌላው ከድራማ ታሪክ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የህንድ ሳንስክሪት ድራማ ነው። ሳንስክሪት ድራማ የተጀመረው ከግሪክና ሮማን ድራማ በኋላ ቢሆንም በእስያ ቀዳሚው ነው። የተጀመረውም 2 መ.ክ.ዘ ከ.ክ ልደት በፊት እንደሆነ ይነገራል፡- ፀሃፊውም ባህርታሙኒ (Bharata muni) የተባለው ሰው ነው።

## 2.2. የተውኔት አጀማመር በኢትዮጵያ

ውድ የርቀት ትምህርት ባልደረባችን በዚህ ክፍል በሀገራችን የተውኔትን ታሪክን በተለያዩ ዘመናት ከፋፍለን በስፋት እናጠናለን ከዚህ በተጨማሪም በየዘመናቱ የነበሩትን የተውኔት ፀሃፊዎች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡ ወደ ትምህርታችን ከመዝለቃችን በፊት እስኪ እነዚህን ጥያቄዎች መልሱ

| |
|---|
| በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ተወኔት ማን ነው? የተፃፈውስ በማን ነው?<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------<br>በሃገራችን ታዋቂ ከሆኑት ፀሃፊ ተውኔቶች አምስቱን ዘርዝሩ?<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>--------------------------------------------------------- |

### 2.2.1. የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ተውኔት

የመጀመሪያው ቲያትር በተክለሃዋርያት ተክለማርያም የተዘጋጀው የአውሬዎች ተረት የተባለው ቲያትር ሲሆን የቲያትሩ ገፀ ባህሪያት ሁሉ አንስሳት ሲሆኑ ታዳሚዎቹ የንጉሳዊያን ቤተሰቦች ነበሩ፡፡ የኢትዮጲያ ስነፅሁፍ ታሪክ በተባለው ጥራዝ ገፅ 123 ይህን አስመልክቶ የተቀመጠውን እንመልከት፡፡

ተክለሃዋርያት በኢትዮጲያ አስተዳደር ላይ የተከፉና የተሻለና ተራማጅ አስተዳደር እንዲፈጠር ይመኙ ነበር፡፡ ልጅ ኢያሱ ስልጣን ይዘው የልጅነት ፍትወት ባጠቃቸው ጊዜ በዚያን ጊዜ ለአገራቸው ተቆርቋሪነታቸውና ተራማጅ አስተያየት አላቸው ከተባሉት ከገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ፣ ከከንቲባ ገብሩና ከሌሎችም ጋር በማደም ልጅ እያሱን ከአልጋ እንዲወርዱ አድርገዋል፡፡ ይሁንና በንግስት ዘውዲቱም ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ አገዛዝ ስላልጣማቸው ሐሳባቸውን በድራማ መልክ የሚገልጹበት ለኢትዮጲያ የመጀመሪያው ልብ ወለድ ድራማ የሆነውን የአውሬዎች ተረት /ፋቡላ/ የተባለውን መጽሃፍ እ.አ.አ በ1913 ዓ.ም. ደረሱ፡፡ ይህ ድርሰት በላፎንቴን ድርሰት ላይ የተመሰረተ ሲሆን በተረትና በምሳሌ አስመስለው በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ይታይ የነበረውን የሥልጣን ብልግና፣ ኋላቀርነትና ደካማ አስተዳደር የሚያመለክት ነበር፡፡ ድርሰቱ ለመድረክ ቀርቦ ከታየ በኃላ ምንም እንኳን ታላቅ አድናቆትን ያተረፈ ቢሆንም የሚነካካው የዚያን ጊዜያቱን ሹማምንትና ባላባቶች ስለነበረ እነዚሁ ሰዎች በትዕግሥት አላለፉትም፡፡ ሁለተኛውም እንዳይታይ ለብዙ ጊዜ ታገደ፡፡ የመጽሐፉ ደራሲ ስለዚህ ሁናቴ እንዲህ ይላሉ፡፡

> ..ፋቡላ /ተረት/.. በተባለው ድርሰቴ ውስጥ የተመሰሉ አውሬዎች እርስ በርሳቸው ተነጋጋሪዎች አስመስዬ በፍጥረት አዘጋጅቼ በቴያትር ባሳይ የሚቀል ዘዴ መሆኑ ታወቀኝ፡፡ እንደዚሁ አደረግሁና በጥቂት ጊዜ ውስጥ አሰናዳሁና ልዑል አልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ በተቀመጡበት ብዙ መኳንንቶች በነበሩበት /በራስ ሆቴል/ አሳየሁ፡፡ የታተሙትም መጻፎቼ በገበያ እንዲሸጡ አደረግሁ፡፡ በጣም ተፈላጊዎች ስለሆኑ ባንድ ቀን ውስጥ ብቻ ወደ 300 ያህል መጻፎች ተሸጡ፡፡ወዲያው ወሬው ለንግሥት ዘውደቱ ደረሳቸው፣ ወሬውን ያደረሱላቸው ሰዎች በመሆናቸው እሳቸውን የሚነካና የሚቃወም ሐሳብ ያለበት አስመስለው

> ድርሰቱን ተረጉሙላቸው፣ ንግሥትም በየዋሕነት እውነት መሰላቸውና በኔ ላይ ተቀየሙ፡፡ ወዲያው መቀየማቸውን ገልጸው ለልዑል አልጋ ወራሽ የወቀሳ ስሞታ ተናገሩ፡፡ ልሁል አልጋ ወራሽም አስጠርተውኝ የንግሥትን መቀየም ገለጹልኝ፡፡ መጻፎቼንም ሁሉንም ለልጅ መኮንን እንዳልካቸው እንዳስረክብ አዘዙኝ፡፡ የተሸጡትንም መጻፎች እየፈለጉ እንዲያዙ አዘዙ፡፡ እኔም ከሦስት ሺህ መጻፎች 300 ብቻ ሲቀሩ ሁሉንም ለልጅ መኮንን እንዳልካቸው አቀረብኩ፡፡ (ገፅ 123)

ንግሥት ካረፉ በኃላ ግን ቴያትሩ እንደገና እንዲታይ ስለተፈቀደ መታየቱን ይናገራሉ ይህንን ቴያትር ለመድረስ ያነሣሣቸው አንድ ጊዜ ቴያትር እንዲያዩ ተጋብዘው ቢሄዱ ቴያትር የተባለው አዝማሪዎች ዘፋኞች /ወንዶችም ሴቶችም/ ተሰብስበው አታሞ መሰንቆ ክራር እየመቱ ሲዘፍኑ ሲጨፍሩ አይተው ከመናደዳቸው የተነሣ መሆኑን ገልጠው "ይኸንኑ አሠራር ማቃናት አስፈላጊ መሆኑን ያንጊዜውኑ ተገነዘብኩት፣ ወዲያው አንድ የቴአትር ጨዋታ ለምሳሌ ያህል ለማሰናዳት ተመኘሁ" ይላሉ፡፡ ጽሑፉ በግጥም መልክ የቀረበ ሲሆን ሁለት ክፍል አለው የመጀመሪያው በተውኔት መልክ የቀረበ አይደለም፡፡ ሁለኛው ግን በተውኔት መልከ የቀረበ ነው፡፡ ቴያትሩም ይኸኛው ክፍል ነው፡፡ ከዚህ ከሁለተኛው ክፍል የሚከተለው እንመልከት፣

**ተ ኩ ላ**

እረግ እረግ እረግ
እኔ ጥሩ ውሃ ሞያዬን ስፈልግ
ለካ አንተ ኖረሀል ያደፈረስክብኝ
ምንኛ ጠግበሀል እንዲህ የምትባልግ
ቆይ አንተን ሳልቀጣ እንዳላገጥክብኝ፡፡

**ግ ል ገ ል**

እረ ክብር ጌታ እግዜር ያሳይዎ
እርስዎን ሲመጡ ከወደ ላይ አየሁ
እኔ የነበርኩሁት ከወደ  ታችዎ
እስቲ እንዴት አባቴ አደፈርሳለሁ

**ተ ኩ ላ**

ሆ ይሆ ደግሞ ተማጥፉቱ የማስተባበሉ
እንዲህ ያለ ጥጋብ አሁን እስቲ በሎ
እንዲያውስ አንተማ አምና አልሰደብከኝም?
አረ እንደምን ችየ አምና ሰደብኩዎ?
እኔ ከተወለድኩ ዓመት አልሞላኝም?
እናቴ እንኳ ጡትዋን አላስጣለችኝም
ስለ እግዜሐር ብለው ይተው እባክዎ

**ተ ኩ ላ**

አንተም ባትሰድበኝ ወንድምህ ሰድቦኛል
ተንኮላችሁ ሁሉ እጅግ ሰልችቶኛል፡፡

**ግ ል ገ ል**

እኔ የባህር ልጅ አንድ ወንድም የሌለኝ
ተንኮል የማልሰራ ገና እምር ታህል ነኝ
ልጅነቴ ዓይተው የዛሬን ይማሩኝ
ባልሰራሁት ሥራ በከንቱ እያማሩኝ

ዳግመኛ አይለምደኝም አንድ ጊዜ ወቀሱኝ
የዳኝነትዎን የውነት ፍርድ አይንሱኝ

**ተ ኩ ላ**

ወንድም ባይኖርህ ዘመዶችህ ሁሉ
እኔን ባዩ ጊዜ አገር ያስጮሀሉ
ዘወትር እነሱ ደግሞ እረኞቻቸው
በሩቅ ያበሩኛል ተነውሾቻቸው
አንተን ዛሬ ድንገት እግዜር ቢያጋጥመኝ
እውነት ፍርድ እያልህ በከንቱ አታድክመኝ
ተውነቱስ ታስ ቱስ ለኔ ምን ተርፎኛል?
ሌትና ቀን ችጋር ይዞ ይግጠኛል
ዳሩ ምን ቸገረህ ለራስህ ደልቶሀል
ጥንቱን ስትፈጠር እግዜር አድሎሀል
ሳር ቅጠሉን ሁሉ ምግብ እርጐልሀል
አጐምብሶ መጋጥ ምንኛ ጐድቶሀል?
ድንገት እንኳ አደጋ ባንተ እንዳይወድቅብህ
ሰውን ያህል ጋሻ መከታ ሰጥቶሀል
ተኝቶ መብላት ነው ምን አሳብ አለብህ?
እኔ ነኝ ጥንቱንም ስፈጠር ያልታደልሁ
እግዜር ሲበድለኝ አደረገኝ ተኩላ
ተስጋ በስተቀር ሳር ቅጠል አልበላ
ነጋ ጠባ ሰግቶ አስቦ አዳሪ ነኝ
እንቅልፍ የሚወስደኝ ቁርጥ ትዳር የለኝ
ዘወትር ለማደን እንከራተታለሁ
እናንተ አትዘንጉ ሰርክ ጦም አድራለሁ
አንተ የተዳላህ ትንደላቀቃለህ
እውነት ፍርድ እያልህ ትሞላቀቃለህ
ፍርድ እንደ ችግሩ ይፈረዳል እንጂ
ለውነትና ላሰት አላቸውን ቅጂ?
መጀመሪያውን ሐሳብ ለራብተኛ ዳኛ
ችግሩን ማስታገስ ያሰኛል ዘዴኛ
ኋላ ግን በርጋታ ፍርድ ተመርምሮ
ውሉ ተፈልጐ ይገኛል ቀስብሎ
አሁንም ወዳጄ በውነት ፍርድ ካልከኝ
ነፍሴንም ፈርጄ እንዳወጣት ያርገኝ
በሐሰት አልፈርድም ሞቴስ ይፍረድብኝ
ለራሴ አላደላም ባደላም ያድላብኝ
ትችት አላበዛም ነገር ሰልችቶኛል
ምሳዬን ስበላ አንተን ይታየኛል
ምሳዬን ተበላሁ ቁጭቴም ይበርዳል
እውነትም ሐሰቱም ኋላ ይፈረዳል
ብትወድም ብትጠላም ይኸን ፈርጃለሁ።

እኝ ዝም በል እንግዲህ በራብ ነድጃለሁ።

**ግ ል ገ ል**

ቢያ ሚያ ወይ እኔ ተበላሽሁ
ሳልበላ ሳልጠጣ አንድ አዱኛ ሰላይ
ገና በልጅነት የተኩላ አፍ አሙዋሽሁ
ደህና ሰንብች ዓለም የፍጥረት አታላይ
ደርሶ ተኃይለኛ ላና ገኝ መዳኛ
በከንቱ እየኀን እንደክማለን እኛ።

## 2.2.2. የት/ቤቶች ቲያትር

ከመጀመሪያው ቲያትር በኋላ የተከተለው የት/ቤቶች ቲያትር ነበር። ተክለሀዋርያት ተክለማሪያምን ተከትለው ብዙ ፀሕፍት ተፈጥረው ነበር ከዚህም ዬፍታሄ ንጉሴ፣ መላኩ በጉሰው፣ ሐዲስ አለማየሁና ስንዱ ገብሩ ይጠቀሳሉ።

**ሀ. ዮፍታሔ ንጉሴ**

ዮፍታሄ ንጉሴ በ1894 በጐጃም ተወልደው ሃይማኖታዊ ት/ቶችን የተማሩ ሲሆን የቀኝጌታ እና በኋላም አጋፋሪ የሚል ማእረግ አግኝተዋል። በዳግማዊ ምንሊክ ት/ቤት ሃይማኖታዊ ህጐችንና አማርኛ ቋንቋን እንዲያስተምሩ ተጠርተው ነበር። በዛ ጊዜም የት/ቤቱ መምህራንና ዳይሬክተሮች ተማሪዎችን እንግሊዝኛ ቋንቋ ለማስተማር ትያትርን ይጠቀሙ ነበር ዮፍታሄም ለማስተማር ስራው የተለያዩ የእንግሊዝኛ ተውኔቶችን ይተረጉም ነበር። ከዚህም ጋር ተያይዞ "ተአምራወ ዋሸንት" የሚለውን ተውኔቱን ለመፃፍ በቅቷል። ይህ ተውኔት በ1923 የተተወነ ሲሆን በኢትዮጵያ ሁለተኛው ተውኔት ለመሆን በቅቷል። በመቀጠልም ምስክር በ(1930)፣ ጥቅም ያለበት ጨዋታ (1931)፣ ሙሽሪት ሙሽራ በ(1932)፣ ያማረ ምላሽ በ(1932)፣ የሆድ አምላኩ ቅጣት በ(1932)፣ የህዝብ ፀፀት በ(1934)፣ ሙሾ በከንቱ በ1935)፣ አባት ንጉሳችን ጠረፍ ይጠብቅ በ(1935)፣ የደንቆሮ ቲያትር በ(1936)፣ ፅፏል።

ከዚያም የጣሊያን ወራሪን ተከትሎ ወደ ሱዳን ያቀና ሲሆን እዛም ሁለት ተውኔቶችን ፅፏል። አፋጀሽኝ በ(1936)፣ እና አለም አታላይ በ(1941)፣ ከነፃነት በኋላም ወደ ኢትዮጰያ ተመልሶ ሶስት የመጨረሻ ተውኔቶቹን ፅፉል በዚህ ወቅት ከንጉስ ጋር ጥሩ ግንኙነት አልነበረውም ተውኔቶቹም እያዩ ማዘን በ(1942)፣ እና ንጉስና ዘውዱ በ(1946)፣ ናቸው

ዮፍታሔ በ1947 አርፏል። የተውኔቶቹ ጭብጦችም ለንጉስ ታማኝነትን፣ የጤና አስፈላጊነትን የተመለከቱ ነበሩ። ከዚህ ሁሉ በላይም ዮፍታሔ ንጉሴ የማዘጋጃ ቤት ቲያትር በ1945 ዓ.ም እንዲቋቋም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

**ለ. መላኩ በጐ ሰው**

በ1889 በጐጃም ተወልዶ የቤተክርስቲያን ትምህርት የተማረ ሲሆን በቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ለማገልገል ወደ አዲስ አበባ መጥቷል። እንደ ዮፍታሔ ሁሉ በዳግማዊ ሚኒሊክ ት/ቤት የሀይማኖት ትምህርትና አማርኛ ቋንቋ እንዲያስተምር ተጠርቷል።

ከተውኔቶቹ "ታላቁ ዳኛ" የሚለው በዳግማዊ ሚኒልክ ትምህርት ቤት የትያትር ቤት ምረቃ በአል ላይ የተተወነ ሲሆን ሌሎቹ ተውኔቶች ግን ለትውልድ መተላለፍ አልቻሉም ነበር፡፡ ለዚህም አራት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡

1. የኢጣሊያን ወራሪ ተከትሎ በኢትዮጲያ ስነፅሁፍ ላይ የደረሰው ጥፋት (በኢጣሊያንኛ ቋንቋ ያልተፃፉ ፅሁፎች እንዲጠፉ በተላለፈው ትእዛዝ) በዚህም ምክንያት የመላኩ ፀሀፊ የነበረውና አስራት ዘገየ የተባለው ሰው ሁሉንም የመላኩን ስራዎች በፍርሀት ወደ ወንዝ በመወርወሩ
2. በመላኩ በጐ ሰው ስራዎች ዙሪያ ምንም አይነት ጥናት አለመኖሩ
3. በስራዎቹ ላይ ስሙን ባለማስፈሩ
4. ውጪ ግብፅ ሀገር መሞቱ

**ሐ. ሐዲስ አለማየሁ**

በ1911 እንዶዳም በተባለ ቦታ ጐጃም ተወለዱ፡፡ የቤተክርስቲያን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ለዘመናዊ ትምህርት ወደ አዲስ አበባ የስዋድን ሚስዮን ት/ቤት መጡ፡፡ በ1930 ሃበሻና የወደኋላ ጋብቻ የተባለ ተውኔት ፃፉ፡፡ ለንጉሳዊያን ቤተሰቦች የጋብቻ ስነስርአት ላይ የሚቀርብና አስደሳች መጨረሻ ያለው ተውኔት ከዮፍታሔና ከበጅሮንድ ሰብስብ ጋር እንዲያዘጋጅ ታዘዙ፡፡ "ከዛም የሆድ አምላኩ ቅጣት" የሚል ተውኔት በጋራ መፃፍ ቻሉ፡፡ በተውኔቱም ንጉሰ ነገስት ሀይለ ስላሴ ስለተደሰቱ ሶስቱንም ቤተ መንግስት ጠርተው ሸለሟቸው፡፡

**መ. ስንዱ ገብሩ**

በ1916 ሸዋ አዲሰ አለም በሚባል ቦታ ተወለደች፡፡ በስዊድን ሚስዮን ት/ቤት እስከ 8ተኛ ክፍል ከተማረች በኋላ ከእህቷ ጋር ወደ ሲዊዘርላንድ ሄደች ከዛም በፈረንሳይ ሞንትሮያል የሴቶች ት/ቤት ገባች የሁለተኛ ደረጃ ት/ቷን ከጨረሰች በኋላም ህግ ለማጥናት በሎንሰን ዩኒቨርሲቲ ገባች በኋላ ግን የት/ት መስኳን ወደ ስነፅሁፍ ቀየረች፡፡ በ1936 ወደ ሃገር ቤት በመመለስ የተውኔት ፅሁፍ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሂሣብ፣ ንፅህና ለማስተማር ቅዱስ ጊዮርጊስ ት/ቤት ተቀጠረች፡፡ በጣሊያን ወራራ ጊዜም አርበኛ ለመሆን በመወሰን የጥቁር አንበሳ ማህበርን ተቀላቀለች የቀይ መስቀል ማህበርን በማደራጀት የቆሰሉትን መርዳት ጀመረች፡፡

በ1927 የኢጣሊያኑን ጀነራል ግራዚያኒን ለመግደል ከተደረገው ሙከራ ጋር ተያይዞ ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር ተይዛ አዚናራ ታሰረች፡፡ ከነፃነት በኋላም 1947 የእቴጌ መነን ት/ቤት ዳይሬክተር የሆነች ሲሆን ተውኔትም መፃፍ ጀመራለች፡፡

"ኮከብህ ያውና ያብባል ገና" የሚለውን ተውኔት በ1947 ፅፋ አዘጋጅታለች፡፡ ከዛም የ1927ቱን የግራዚያን ጭፍጨፋ የተመለከተ "በግራዚያን ጊዜ የየካቲት ቀኖች" (1947) የሚል ተውኔት ፅፋለች፡፡

"የታደለች ህልም" (1948) ፣ "ርዕስ የሌለው ትዳር" (1948) "የኑሮ ስህተት" (1948) "ከማይጨው መልስ" (1949) እና "ፊት አውራሪ ጌታ አዳሙ" (1949) የሚሉ ተውኔቶችንም ፅፋለች፡፡ ከዮፍታሔ ንጉሴና ከሌሎች ጋር በመሆንም የማዘጋጃ ትያትር ቤት እንዲቋቋም ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች፡፡

**ሠ. ነርሲስ ናልቫንዲያን (Nersis Nalvandian)**

በ1989 የአርመኒያ የቀድሞ ግዛት በነበረችው ኤታብ "Aitav" በምትባል ቦታ ተወለደ፡፡ የቱርክ ወረራን ተከትሎ በሃገሩ ፖለቲካዊ ችግር ሲፈጠር ወደ ሶራያና ግብፅ የተላከ ሲሆን አፄ ሀይለ ስላሴ ከነፃነት በኋላ

ሲመለሱ ኔልቫንድያን “Nalvandian” ግብፅ ውስጥ ከነበሩ ሌሎች አርመኖች ጋር ከንጉስ ጋር መጣ፡፡ ኢትዮጵያ ከመጣም በኋላ በዳግማዊ ምንሊክ ት/ቤት ማስተማር ጀመረ እዛም የተለያዩ ተውኔቶችን መፃፍ ጀመረ፡፡

በ1934 “ጕንደሬው ገብረ ማሪያምን ” የፃፈ ሲሆን ከዛ በኋላ “እሺ ነገ”፣ “አቶ ማናሌ”፣ “እረኛው ተፈሪ” ፣ “የሺ”፣ “ዱቼ” እና “አብዮታዊያን” የሚሉ ተውኔቶችን ፅፏል፡፡

ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ የመጀመሪያው የኢትዮጲያ ብሔራዊ መዝሙር “ተፈሪ ማርሽን” ያቀናበረው እሱ ነው፡፡

## 2.2.3. ዘመናዊ ቲያትር

### 2.2.3.1 <u>የንጉስ ዘመን (1931 - 1974)</u>

የንጉስ ዘመን በኢትዮጲያ ቲያትር ወርቃማው ዘመን ሊባል ይችላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ

1. የንጉሳዉያን ቤተሰብ እና ንጉሱ ቲያትር ለማየት ጊዜ ይመደቡ እንዲሁም ለጉበዝ ፀሀፍትና ተዋናዮች ሽልማት ስለነበር
2. አሁን በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ከግማሽ በላይ ቲያትር ቤቶች በንጉስ ዘመን መሰራታቸው
3. የኢትዮጵያዊያንም ሆነ የውጭ ሀገር ሰዎች ተሳትፎ ስለነበር ነው፡፡

### 1.ትያትር ቤቶች

#### ሀ. <u>ሃገር ፍቅር ቲያትር</u>

በጣሊያንና በኢትዮጵያኖች መካከል ከተፈጠረው የ1930ው የወልወል ግጭት በኋላ የኢትዮጵያን ህዝቦች ለጦርነት ማነሳሳት አስፈላጊ ሆኖ ነበር፡፡ ስለዚህም ለኘሮፖጋንዳ የሚሆን ማህበር መቋቋም እንዳለበት መኮንን ሀብተወልድ የተባለ የንጉስ ቃል አቀባይ ለንጉስ አሳሰባቸው፡፡ ጥያቄውም በንጉስ ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ “ የሀገር ፍቅር ማህበር” በ1936 ተቋቋመ፡፡ ግን ከአጭር ጊዜ በኋላ ጣሊያኖች የበላይነት ስላገኙ ሀገር ፍቅር የኘሮፖጋንዳ ስራውን አቆመ፡፡

ከነፃነት በኋላም ማህበሩ በመኮንን ሀብተወልድ በድጋሚ ተቋቋመ፡፡ የተለያዩ ጥበባዊ ስራዎችን ለማቅረብ እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡ በ1943 የተለያዩ ጥበባዊ ትእይንቶችን ማስተናገድ ጀመረ በመጀመሪያዎቹ አመታት ይቀርቡ የነበሩ ተውኔቶችም ያለስክሪኘትና ቅድመ ዝግጅት ነበር፡፡ በኋላ ስክሪኘቶች መፃፍ ጀምረዋል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገር ፍቅር ቲያትር ስክሪኘት የፃፈው ላቀው ደስታ ሲሆን “የአባቶች ስርአት” “ብር ቀበሯ” ፣ የወይኔ ባለቤት” “የሀገር ልማት” ወዘተ የተባሉት ትያትሮቹም ይጠቀሳሉ፡፡ ሀገር ፍቅር ከዚህ በኋላ የትያትር እንቅስቃሴውን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ታላላቅ ፀሀፍትን አፍርቷል፡፡ ከነዚህም ፀሀፍት

1. <u>እዮኤል ዮሀንስ</u>

በአዲስ አበባ ካሳንቺስ በተባለው ቦታ በ1935 ተወልዶ ከቤተክርስቲያን በመኮንን ሀብተወልድ የተመረጠ ሲሆን በላቀው ደስታ “የወይኔ ባለቤት” በተባለው ቲያትር ለመጀመሪያ ጊዜ በትወና የተሳትፏል፡፡ ከመቶ በላይ

ተውኔቶች የፃፈ ሲሆን ከተውኔቶቹም ሙዚቃዊ ድራማዎች፣ አጫጭር ተውኔቶች እና የሙሉ ጊዜ ቲያትሮች ይገኙበታል፡፡

የመጀመሪያ ተውኔቱ "አቻ ጋብቻ" ሲሆን ከሙዚቃዊ ድራማዎቹ "ጊዜ ወርቅ ነው" ፣ "የሴት ፍርሀትዋ እስከመቀነትዋ" ፣ "የሀይማኖት መሰረት" ፣ "አስራሁለት ጠቅላይ ግዛት" እንዲሁም ከተውኔቶቹ "ሳይችግር ጤፍ ብድር" ፣ " ሁሉም ዜሮ ዜሮ "፣ "የልጃገረድ ፀሎት" ፣ "ቀይ ለሊት" ፣ "የሰው ክብሩ ግብሩ" ፣ "ካሜራው"፣ ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡

### 2 መላኩ አሻግሬ

በ1933 አዲስ አበባ ጉለሌ በተባለው አከባቢ የተወለደ ሲሆን በ1950 የማዘጋጃ ትያትርን ተቀላቅሏል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ "ስነ ስቅላት" በተባለው ተውኔተ በዘፋኝነት ተሳትፏል ከዛም የማቲዎስ በቀለን "አንድነት የቲያትር ቡድን" ተቀላቅሎ ወደ ሀረር ተዛውሮ ነበር፡፡ በ1957 ሀገር ፍቅርን በመልቀቅ "ክቡር ዘበኛ" የሙዚቃ ቡድንን የተቀላቀለ ሲሆን "ሴት አረዳችኝ" እና "ሠይጣን ለወዳጁ ቅርብ ነው" የሚሉ ትያትሮች ላይ ተውኗል፡፡

ሁለተኛውን ቲያትር ያለፍቃድ በመተወናቸው ብዙ ተዋናኞች ሲታሰሩ እሱ ግን ለማምለጥ ችሏል፡፡ በ1972 "ቴዎድሮስ የቲያትርና የሙዚቃ ቡድን" ሁለተኛውን የግል ቲያትር ድርጅት መሰረተ፡፡ ከዚህ ቡድን ጋርም በተለያዩ የኢትዮጰያ የገጠር ከተማ አካባቢዎች የተለያዩ ተውኔቶችን ተውኗል፡፡ በግል ማቴዎስ በቀለና መካሉ አሻግሬ በቲያትር ረገድ ያደረጉት እንቅስቃሴ በሀገራቱ ብዙ የትያትር ተመልካቾችን ያፈራ ሲሆን ቲያትር በስፋት እንዲታወቅ የጐላ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ድርጅቱ ከአራት አመት ቆይታ በኂላ በ1976 ፈርሷል፡፡ ከዚህም በኂላ መላኩ የሀገር ፍቅር ቲያትርን የተቀላቀለ ሲሆን እስከ 1989 ድረስ የሰራ ሲሆን ከ25 በላይ ተውኔቶችን ፅፏል፡፡ ከተውኔቶቹም " ድፍንፍን" "አይ ሰው" ምን አይነት መሬት ናት" ፣ "አለም ጊዜና ገንዘብ"፣ "ጉዶ ፈላ" ፣ "ህልም ነው" ፣ "ማሪኝ"፣ "ይቅርታሽን"፣ "ማጣትና ማግኘት"፣ክህደትና የኑሮ ስህተት" ፣ "የትም ወርቅ እንደሻው" ፣ "ነፍስ ይማር" ፣ "ባቡር"፣ "መጥረጊያ ያለው" ፣ እና "የሳት እራት" ይጠቀሳሉ፡፡

### 3. ከበደ ሚካኤል

በ1915 በአንኮበር ከተማ ተወልዱ ወደ አዲስ አበባ ከመጣም በኂላ በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሲስ በኂላም በላዛሬስ ሚሽን ት/ቤት ተምሯል፡፡ ለኢትዮጰያ ፀሀፍት የትርጉም ስራን "በሮሚዮና ጁለየት" ያስተዋወቀ ሲሆን የኤም ክሌይን "Beyond the Pardon" "ከይቅርታ በላይ" በሚል ተርጐሟል፡፡ "የትንቢት ቀጠሮ" ፣ "የቅጣት ማዕበል" ፣ ካሌብ እና ሃኒባል" የተባሉ ተውኔቶችንም ፅፏል፡፡ በኢትዮጰያ ስነፅሁፍ ታሪክ ትልቅ ቦታ ያለው ብዙ መፃህፍትን (በመጀመሪያ ልጆችን ለማስተማርያነት ብሎ ያዘጋጃቸው) ሌሎች የተለያዩ መፃህፍት ጥበባዊ ተውኔቶች ፣ ምክሮች፣ ስነ ግጥምን የያዘ መጽሀፍትን ያሳተመ ሁለገብ ፀሀፊ ነው፡፡

## ለ. የከተማ አስተዳደር ቲያትር ቤት

በተለምዶ የማዘጋጃ ቲያትር የሚባል ሲሆን በ1947 በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ተቋቁሟል፡፡

1. ፋሺስት ኢጣሊያን የተጋፈጡት አርበኞች ስሜታቸውን የሚገልፁበት ቦታ እንዲያገኙ

2. ለሀገራቸው ነፃነት ህይወታቸውን የሰው አርበኞች መታሰቢያ እንዲሆን
3. በኢትዮጵያ  ቲያትርን ለማሳደግ

ቲያትር ቤቱ መጀመሪያ ሲቋቋም "የአርበኞች ማስፋፊያ "የሚል ስም ነበረው መስራቾቹም ዮፍታሄ ንጉሴ፣ አፈወርቅ አዳፍሬ ፣Nersis N. Nalvandian ፣ ተስፋዬ ለማ ፣ እማእለፍ ህሩይ፣ ስንዱ ገብሩ፣ አበበ ረታ፣ ባለንባራስ እምዮ እና ልጅ አርአያ ስላሴ ይጠቀሳሉ፡፡ ለመጀመራያ ጊዜ የተከፈተው ቲያትር ቤት ለሁለት ጊዜያት ቦታ የቀየረ ሲሆን የመጨረሻውና ዘመናዊው ቲያትር ቤት የተከፈተው በ1975 በመንግስቱ ለማ "ባለ ካባ" እና "ባለ ዳባ" ትያትር ነበር፡፡

### ሐ. የኢትዮጰያ ብሔራዊ ቲያትር

በ1956 የቀድሞ "ሲኒማ ማልኮኒ" የተሰኘው የፋሽስት ኢጣሊያን ሲኒማ ቤት ወደ ትያትር ቤት በመቀየር ነው የተቋቋመው፡፡ ሲቋቋም አላማው

1. ባህላችንን ለማሳደግና የባህል ወረራን ለመከላከል
2. በትያትርና ሙዚቃ የሰዎችን እውቅና ለማሳደግ
3. እራስን ለመግለፅ ባህልን ለማሳደግ
4. የሙዚቃ ፣ ዳንስና ትያትር ባህልን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍ
5. ከሌሎች የአፍሪካና አለም ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙት ለማጠናከር በሚል ነበር፡፡

የተለያዩ የውጭ ሀገር ዜጐችም ለትያትር ቤቱ መመስረት እና እድገት አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ኦስትሪያዊው ፍራንሲስ ዙለቬር (Francis Zulvewer) በትያትር ቤቱ የቀረበውን የመኮንን እንዳልካቸውን "ዳዊት እና ኦርዮን" የተሰኘውን ተውኔት አዘጋጅቶ መርቷል፡፡

አሌክሳንደር አጋር (Alexander Agar) የተባለው ሰውም በትያትር ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ብርሃንና ዘመናዊ የድምፅ አጠቃቀሞችን  በመጠቀም "ማንም ሰው" የተሰኘው ተውኔት ዘመናዊነትና እውነታዊነት እንዲላበስ አድርጓል፡፡ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ እሰከ 1974 ድረስ 44 ተውኔቶች ቀርበውበታል፡፡

- የከበደ ሚካኤል "ሀኒባል" ፣ ካቤል እና "የቅጣት ማእበል"
- የግርማቸዉ ተክለ ሃዋርያት  "ቴዎድሮስ ታሪካዊው ድራማ"
- የዳኛቸው ወርቁ "ሰቀቀንሽ እሳት" እና "ትበልጭ"
- የመላኩ አሻግሬ "አለም ጊዜና ገንዘብ" እና "አንድ ጡት"
- የሙላቱ ገብሩ "ደመ መራር" እና "ስስታሙ መንጠቆ"
- የማሞ ውድነህ "አሉላ አባ ነጋ" ይጠቀሳሉ፡፡

## 2.2.3.2 <u>የደርግ ዘመን (1974 — 1991)</u>

በ1973 የዘውዳዊውን ስርአት በመቃወም በኢትዮጰያ አብዮት ሆነ አብዮቱንም ተከትሎ የንጉስ አገዛዝ አበቃ፡፡ አዲስ መንግስትም ተቋቋመ፡፡ ከወታደራዊው ሃይል የተዋቀሩት የደርግ አመራሮችም የሶሻሊስት ስርአት አወጁ፡፡ ከቲያትርና ከሌሎች ጥበባት ዕድገት ጋር በተያያዘ የደርግ ዘመን በአርቲስቶች ላይ ጥብቅና ቅርብ ክትትል ያደርግ ስለነበር አሉታዊ ተፅእኖ ነበረው፡፡ ፀሐፊ ተውኔቶቹም የፈለጉትን ያሰቡትን ለመፈፀም ምንም ነፃነት አልነበራቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ጊዜ ብዙ ታላላቅ የኢትዮጰያ ስነፅሁፍ ሰዎች በቀጥታም ሆነ

በተዘዋዋሪ ህይወታቸውን እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል፡፡ በአሉ ግርማ (ዝነኛ የረዥም ልብ ወለድ ፀሐፊ) ፣ አቤ ጉበኛ (የልቦለድና የተውኔት ፀሐፊ) እና ሌሎችም ተገለዋል፡፡ በዚህ ወቅት የቀረቡ ተውኔቶች ሁሉም ማለት ይቻላል የመንግስትን ርዕዮተ ዓለም የሚያንፀባርቅ ፖለቲክዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡

**ትያትር ቤት**

ሀ. **ራስ ቲያትር**

ትያትር ቤቱ የተገነባው በ1937 ቢሆንም እንደ ቲያትር ቤት ያገለገለው በ1979 ነበር፡፡ ትያትር ቤቱ የተከፈተው መንግስቱ ለማ "ጠያቂ" ብለው በተረጐሙት የጄ.ቢ.ኘሪስትሊ "An inspector calls" በተባለው ተውኔት ነው፡፡ በ1982 ሲቋቋም ራስ ትያትር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትያትሪካል አርት የመጀመሪያ ተመራቂዎች መካከል አራት ምሩቃንን ቀጥሯል፡፡ ከምስረታው በኋላ ከአርባ በላይ ተውኔቶች የቀረቡበት ሲሆን ከሁሉም ዝነኛ የነበረው ግን በተዋናዮቹ የተፃፈው "ላጤ" የተባለው ተውኔት ነው፡፡ ይህ ተውኔት በምስራቅ አፍሪካ የመጀመሪያው ዘጋቢ ቲያትር ነው፡፡ ይህ ትያትር ቤት ከሌሎቹ ቲያትር ቤቶች የሚለየውም በዚህ ነው፡፡

**የጊዜው ዝነኛ ፀሐፊ ተውኔቶች**

1. **ጌታቸው አብዲ**

ወሎ ደሴ አካባቢ 1947 ተወለደ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቱን ካጠናቀቀ በኋላ ብሔራዊ ትያትር ተቀጠረ፡፡ ነፃ የት/ት እድል ሩሲያ ስላገኘ ሉና ካርስኪ ቲያትር ተቋም (Lunacharisky theatre institute) ገባ፡፡ በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ ከተመረቀ በኋላም ወደ ኢትዮጲያ ተመልሶ ሃገር ፍቅር ቲያትር ስራ ጀመረ፡፡ ሃገር ፍቅርን ከ1980-84 ለ14 አመታት እና ብሔራዊ ትያትርን ከ1984-92 ለ9 አመታት አስተዳድሯል፡፡ "ስንታየሁ" ፣ "እናሸንፋለን" ፣ "መስታወት" ፣"ምሽት" እና "ቁልፍ" የሚሉ ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ተውኔቶችም ፅፏል፡፡

2. **አያልነህ ሙላቱ**

በ1949 በጐጃም የተወለደ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቱን ካጠናቀቀ በኋላ ጋዜጠኝነትን በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ እንዲያጠና ወደ ሩሲያ ተልኳል፡፡ ወደ ኢትዮጲያ ከተመለሰ በኋላም ብዙ ፖለቲካዊ ተውኔቶችን የፃፈ ሲሆን "እሳት ሲነድ" ፣ "ሻጥር በየፈርጁ" ፣ "የገጠርዋ ፋና" ፣ "የመንታ እናት" ፣ "ዱባ እና ቅል" ፣ "ትልቅ አይን" ፣ "ደሃ አደግ" ፣ "ሰባራ ዘንግ" ፣ "ከድኛ"፣ ሾተላይ" ይጠቀሳሉ ከተውኔቶቹም "ደሃ አደግ"፣ "ጥበበኛው ጋለሞታ" እና ሾተላይ የታተመ ሲሆን "የመንታ እናት" እና "ደሃ አደግ" ደግሞ ወደ ሩሲያና እንግሊዘኛ ተተርጐመዋል፡፡ የቤርቶልት ብሬችትን (Bertolt Brecht) የተራኪ ትያትሮች አመራር ቴክኒክን ተግባራዊ በማድረግም ይታወቃል፡፡

3. **ፀጋዬ ገብረመድህን (1937 — 2006)**

አምቦ አከባቢ በ1937 ተወለደ አዲስ አበባ ከመጣም በኋላ ወደተለያዩ የአውሮፖ ሃገሮች የሄደ ሲሆን በትያትርም አጭር ስልጠና አግኝቷል፡፡ የተለያዩ ተውኔቶችን በአማርኛና እንግሊዘኛ የፃፈ ሲሆን የሼክስፐር ፣ሞልየር እና ብሬችት ስራዎችን ተርጉሚል፡፡ የተለያዩ ግጥሞችን በአማርኛና እንግሊዝኛ ያሳተመ ሲሆን

የአፍሪካ ህብረት መዝሙርንም ከአንድ የኬንያ ገጣሚና አቀናባሪ ጋር በመሆን በ1986 ፅፏል፡፡ “ ሃሁ በስድስት ወር “፣ “እናት አለም ጠኑ” ፣ “መለከተ ወዛደር” ፣ “ሃሁ ወይም ፐፑ” በመሳሰሉት ፖለቲካዊ ተውኔቶችም ይታወቃል፡፡ “በልግ”፣ “የከርሞ ሰው” እና “የሾህ አክሊል” የተባሉት ትራጀዲዎቹም ዝነኛ ናቸው፡፡ ከትርጉም ስራዎቹም የሼክስፒር “ኦቴሎ”፣ “ማክቤዝ” እና “ሃምሌት” እንዲሁም የሞልዬር ኮሜዲዎች “አወናባጁ ደብተራ” (Tartuffe) እና የፊዝ ዶክተር (Doctor Faustus) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደ “ቴዎድሮስ“፣ “ጴጥሮስ ያቺን ሰአት” የሚሉ ታሪካዊ ተውኔቶችንና “ኦዳ ኦክ ኦራክል” (Oda ok oracle) የሚል ባህላዊ ተውኔት ፅፏል፡፡ በ1974ትም የብሔራዊ ትያትር ስራ አስኪያጅ ሆኖ ስርቷል፡፡

4. <u>አቤ ጉበኛ</u>

ጉጃም በኮረኮንች አቦ አካባቢ በ1933 ተወለደ፡፡ አዲስ አበባ ከመጣም በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቱን አጠናቆ ትንሽ የንግድ ስራ ጀምሮ ነበር፡፡ ከዛ በኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር በጋዜጠኝነት ማገልገል ጀመረ፡፡ ከስድስት አመት በኋላም ስራውን ለቆ ልቦለዶችን እና ተውኔቶችን መፃፍ ጀመረ “የደካሞች ወጥመድ” እና “ፖለቲካና ፖለቲከኞች” የሚሉ ሁለት ፖለቲካዊ ተውኔቶችን ፅፏል፡፡

5. <u>ተስፋዬ አበበ</u>

በ1940 በአዲስ አበባ ተወለደ፡፡ ተስፋዬ አበበ የትያትር ቡድን የሚል ቡድንም የመሰረተ ሲሆን ይህ ቡድን የማቴዎስ በቀለ እና መላኩ አሻግሬን ድርጅቶች ተከትሎ ሦስተኛው የግል ትያትር ድርጅት ነው፡፡ “የወሬ ፈላስፋ” ፣ “አስራ ሁለት እብዶች በከተማ”፣ “ፀረ መናፍስት” ፣ “የንጋት ኮከብ” ፣ “የጥቁር ድምፅ” ፣ ባሻ ደምጤ “፣ “ቀይ ማጭድ”፣ “ታጋይ ሲፋለም” ፣ እና “ቀይ መነፅር” ፣ የሚሉ ፖለቲካዊ ተውኔቶችንም ፅፏል፡፡

6. <u>መንግስቱ ለማ (1924 — 1988)</u>

በ1924 ሐረር ተወለደ፡፡ የቤተክህነት ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላም ከአባቱ አለቃ ለማ ኃይሉ ጋር ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡ ከዛ ኮተቤ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ ት/ቤት ገባ፡፡ በ1948 የሁለተኛ ደረጃ የእንግሊዝ መልቀቂያ ፈተናን በጥሩ ሁኔታ ስላለፈ ለንደን ሬጀንት ፖሊ- ቴክኒክ ት/ቤት ገባ (London Regent poly — Techinque School) ከዛም በለንደን የኢኮኖሚክሰ ት/ቤት ተመዘገበ፡፡ ለንደን በቆየባቸው ስድስት አመታትም ከእንግሊዛዊው ፀሐፊ ጆርጅ በርናንድ ሾው የኮሜዲ አፃፃፍና የእውናዊነት (Realism) እውቀትን አግኝቷል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላም ሲቪል አሽዬሽንን ጨምሮ በተለያዩ ደረጃዎች ሰርቷል፡፡ በ1958 እንደ የሚያገኘው የኢትዮጰያ ኢንበሲ ተላከ እዛም “ጠልፎ በኪሴ” የተባለውንና በኋላ marriage by Abdaction በሚል ወደ እንግሊዘኛ የተተረጐመውን ተውኔት ፅፏል በ1963 ወደ ኢትዮጰያ ተመልሶ መጥቶ በተለያዩ ሃላፊነቶች ሰርቷል፡፡ በ1979 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለትያትርና ጥበባት ት/ት ክፍል ሌክቸረር ሆኗል፡፡ “ያላቻ ጋርቻ” በኋላ እንግልዝኛ Marriage of Unequals” ተብሎ የተተረጐመ ፣ “ስለ ካባ እና ስለ ዳባ” ፣ “ፀረ ከሎኒያሊስት” እና “ሽሚያ” የተባሉ ተውኔቶችም ፅፏል፡፡ ከትርጉም ስራዎቹም “ጠያቂ” (የጄ.ቢ.ኘሪስሊ

“An inspectorcalls) ዳንዴው ጨቡዴ (ከአንቶን ቼኮብ “The Bear) እና “ግደይ ግደይ አለኝ” (የቶፊቅ አልሃሽም ተውኔት) ይጠቀሳሉ፡፡

7. <u>ተስፉዬ ገሰሰ</u>

በ1938 በሐረርጌ ክፍለሃገር ጉሮጉቱ እሚባል ቦታ ተወለደ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ በ1956 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገባ የአራተኛ አመት የህግ ተማሪ ሆኖ “ያዕቅብ” በተባለው ተውኔት ሲተውን ቀዳማዊ ሃይለስላሴ አይተው በሚቀጥለው ቀን በተ መንግስት ጠርተው ሸለሙት ከሸለማቱ በኋላም ንጉስ የት/ት መስኩን ቀይሮ ቲያትር እንዲያጠና መከሩት ተስፉዬም ምክሩን ስለተቀበለ ወደ አሜሪካ ተላከ በሰሜን ምዕራብ ዩኒቨርሲቲም ትያትርን አጥንቶ በአዘጋጅነት የሁለተኛ ደግሪ ይዞ መጣ ለብዙ ተውኔቶች ውስጥ በተዋናይነት የተሳተፈ ሲሆን :የሾህ አክሊል” ፤ “የሺ” ፤ “ቴዎድሮስ” “ሃምሌት” ጥቂቶቹ ናቸው “ጠልፎ በኪሴ” ፤ “ያላቻ ጋብቻ” እና የሊዮና ጅሊየት”፤ “ኦዳ አክ አራክል”፤ “ሁኢዝ አፍሬድ አፍ ቨርጅንያ ውልፍ”፤ “ዌይቲንግፎር ጉደት” የተባሉ ተውኔቶችንም አዘጋጅቷል፡፡ “ዕቃው”፤ ”የሺ”፤ “ፍርድን ለናንተው” የሚሉት ተውኔቶችም ከፃፉቸው ውስጥ ይመደባሉ

8. <u>ፍሰሃ በላይ ይማም</u>

በ1954 ደሴ ዳውዶ አካባቢ በ1954 ተወለደ በ1979 የተለያዩ ሙዚቅዋች ፣ ትያትርና ዳንስ የሚያቀርበው የላሊበላ ኪነት በአዲስ አበባ የኒቨርሲቲ ተቀላቀለ ፍሰሃ በላይ በባህላዊ ተውኔቶቹ የሚታወቅ ሲሆን ከዝነኞቹ ተውኔቶቹም “ስመኝ ስንት አየሁ” ፤ “ሆድ ይፍጀው” “በግተራ” አሻግሬ መሰረት ፣ “የወፍጉጆ” እና “የጨረቃ ቤት” ይጠቀሳሉ፡፡

## 2.2.3.3 <u>ከ1991 በኋላ</u>

በ1991 ወታደራዊው አገዛዝ አብቅቶ በፌደራል መንግስት ተተካ

### ሀ. ሜጋ አምፊ ቲያትር

ሜታ በ1995 በሁለት የጥበብ ቡድኖች ተቋቋመ አባላቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትያትር ጥበባት ተመራቂዎች ናቸው ቡድኖቹም “ደብረ ያሬድ ኢንተር ኘራይዝ” እና “ፖል ኢትዮጵያ ይባሉ ነበር፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ለመዋሀድ በመስማማት “የሜታ ጥበባት ማዕከልን” አቋቋመ ቡድኑ ከተመሰረተም በ኉ላም በመጀመሪያ ለመድረክ የበቃው “ሮሚዮና ጅሊየት” የተባለው ተውኔት ነው፡፡

ማዕከሉ ከተቋቋመ በኋላ “አንቲገን” (ትርጉም በሳህሉ ኪዳኔ) ስጦታ (ትርጉም በማንያዘዋል እንደሻውና በላይነህ አቡኔ) ፣ አብሮ አደግ (ትርጉም በዘካሪያስ መሃመድ) ይጠቀሳሉ፡፡ “የወፍ አፍ” (በደረሰ በላይነህ) እና “የሰማዩ ሰው” (በአቦነህ አሻግሬ) የሚሉ የልጆች ተውኔቶችም ቀርበዋል፡፡

### ለ. የህፃናትና ወጣቶች ቲያትር

ትያትር ቤቱ በመደበኛነት ከመቋቋሙ በፊት የተለያዩ የህፃናት ተውኔቶች በተለያዩ ቦታዎች ይቀርቡ ነበር ለአብነትም

- በሀገር ፍቅር ቲያትር፡- “አራቱ ሙዚቀኖች” እና “ጉበዙ ልብሰ ሰፊ”
- በብሔራዊ ቲያትር “ጥንቸል እና ጃርቲ “ እና “ድመቱ በከተማ
- በራስ ቲያትር “የተራራው ንጉስ” እና “ዶዬ” የሚሉ ትያትሮች ቀርበዋል፡፡

የህፃናትና ወጣቶች ትያትር ህጋዊ ባሆነ መንገድ ስራ የጀመረው በ1994 ነው፡፡ የታወቁት የህፃናት ተውኔት ፀሐፍትም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **አስፋው አስመሃት**

ብዙዎቹ ስራዎች የህፃናትና ወጣቶች ተውኔቶች ሲሆኑ “ራጅ” ፤ “ጉንቁል” ፤ “የምስራች” እና “ዶውል” የሚሉ ይገኑበታል፡፡

2. **አቦነህ አሻግሬ**

በ1951 በጉሬ ከተማ የተወለደ ሲሆን በ1983 በትያትር ጥበባት ተመርቋል ከዛም የሁለተኛ ደግሪውን ከኦሃዮ ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል፡፡ በፀሐፊነትና በአዘጋጅነት የሚታወቅ ሲሆን ከተውኔቶቹም “መስከቴ” ፤ “አባ ጉጉ” እና “የሰማዩ ሰው” የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

3. **ሞሲሳ ቀጃላ**

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቲያትር በመጀመሪያ ዲግሪ በ1986 ተመርቋል፡፡ ከተውኔቶቹም “ሁለቱ ወንድ ማማቶች” ፤ “ስንብት” “ውሸት” ፤ “ጫማው”፤ “ጉርፍ” እና “ማሩፍ” ይጠቀሳሉ

4. **አለማየሁ ገብረህይወት**

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትያትር በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ የተመረቁ ሲሆን የፃፉቸው ተውኔቶችም “ፈላስፋው” እና “የገንፎ ተራራ” የሚሉ ናቸው፡፡

5. **ኤፍሬም በቀለ**

ጦጣ አባ መላ የሚል የልጆች ተውኔት ፅፏል፡፡

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ ሁለትን ትምህርት እዚህ ላይ አጠናቀናል በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጥህን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦልሃል የተነሳውን ነጥብ የምታውቀው ከሆነ ይህን ምልክት አድርግ | √ | ነጥቡን ካላወቅከው ደግሞ የ | X |
ምልክት አድርግና እንደገና ተመልሰህ ትምህርቱን ከልስ

1. በአለም የተውኔትን አነሳስን በትክክል መግለፅ እችላለሁ። ........... ☐
2. በአለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የተውኔት ፀሃፍትንና ስራዎቻቸውን መዘርዘር እችላለሁ።------------------------------------------------------------------ ☐
3. በኢትዮያ የተውኔት አነሳስና እድገትን ማስረዳት እችላለሁ።--- ☐
4. በየዘመናቱ የተፃፉትን ተውኔቶች ጭብጦች መናገር እችላለሁ።----- ☐
5. በኢትዮጵያ ታዋቂ ፀሃፊ ተውኔቶችን ከነስራዎቻቸው መዘርዘር እችላለሁ።--- ☐

## ግለ ፈተና ሁለት

በምዕራፍ ሁለት ያቀረብነውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተለው ፈተና ተዘጋጅቷል።

በትምህርቱ ውስጥ የቀረበውን ገለፃ ሳትመለከት ጥያቄዎቹን መልስ። ጥያቄዎቹን ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ በሞጅዩሉ የመጨረሻ ገፆች ካቀረብንልህ መልሶች ጋር አመሳክር።

***መመሪያ አንድ*** ፡- *ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ።*

----------------1. በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ያሉት ትያትር ቤቶች ከግማሽ በላይ የተሰሩትበንጉሱ ዘመን ነው
----------------2. የተለያዩ ጥንታሃይማኖታዊ ስርአቶችና ስነቃላዊ በአላት የተውኔት መሰረቶች ናቸው
-----------------3. የምእራቡ አለም የተውኔት ምንጭ እንግሊዝ ናት
-----------------4. በስራዎቹ ላይ ስሙን ባለማስፈሩ ምክንያት መታወቅ ያልቻለው ፀሃፊ ተውኔት እዮኤል ዮሃንስ ነው
------------------5. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ትያትር ቀደም ሲል "ሲኒማ ማልኮኒ" በመባል ይታወቅ ነበር

***መመሪያ ሁለት***፡- *የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስፈላጊውን ዝርዝር ሳታስቀር ባጭሩ መልስ።*

1. ዮፍታሄ ንጉሴ ሱዳን ሃገር በስደት የፃፋቸው ተውኔቶች ---------------------እና -------------------- ናቸው
2. የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ተውኔት --------------------------ሲሆን የተፃፈውበ ------------------------- ነው
3. ከግሪክ ትራጀዲ ፀሃፊዎች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ

ሀ-------------------------------

ለ-------------------------------

4. በአለማችን ላይ የመጀመሪያው ድራማ ማን ይባላል?
5. በእስያ ቀዳሚው ድራማ የቱ ነው?

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የተውኔት አላባውያን

### መግቢያ

የዚህ ኮርስ ተከታዬ! በዚህ የሞጁዩሉ ሶስተኛ ምዕራፍ ላይ ስለተውኔት አላባዊያን እንነጋገራለን። ለተውኔት ጣራና ግድግዳ ሆነው የሚያገለግሉት የተውኔት አላባዊያን ቁጥር እንደየባለሙያው ቢለያይም፣ በዚህ ምዕራፍ የምንመለከታቸው አላባዊያን አምስት ይሆናሉ።

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከታቸው የተውኔት አላባዊያን መቼት፣ ገፀባህሪያት፣ ሴራ፣ ቃለ ተውኔት እና ጭብጥ ናቸው እነዚህ አምስት አላባዊያን በተናጠል የሚቃኙ ሲሆን ለእያንዳንዱም ተገቢ ምሳሌዎች ይቀርባሉ። በአምስቱ የተውኔት አላባዊያን ትንታኔ መነሻ ላይ የቀደመ እውቀትህን የምታንፀባርቅባቸው ጥያቄዎች የሚቀርቡ በመሆናቸው፣ እነሱን በመመለስ ወደ ንባብ መግባት እጅጉን ጠቃሚ ይሆናል። በምዕራፉ መጨረሻላይም ግለፈተናዎች ያሉ ሲሆን ፣ እነሱን በጥንቃቄ በመስራት ስለሙከራህ ትክክለኛነት እንድታጣራ በሞጅዩሉ መጨረሻ ላይ ምላሾቹ ተቀምጠውልሀል።

<u>አላማ</u>

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ

- ስለተውኔት አላባውያን ምንነት ታብራራለህ
- ስለ መቼት ምንነት ታብራራለህ
- ስለገፀባህሪያት አይነት እና ባህሪያት ታብራራለህ
- ቃለ ተውኔት በተውኔት ውስጥ በምን መልኩ መቅረብ እንዳለበት ትዘረዝራለህ
- ስለጭብጥ ምንነት ታብራራለህ
- ሴራ በተውኔት ውስጥ ስላለው ቦታ ትገልጻለህ

ከዚህ ቀደም ስለስነጽሁፍ በተማርከው ትምህርት ውስጥ ስለስነጽሑፍ አላባውያን በቂ እውቀት እንደቀሰምክ ተስፉ አደርጋለሁ። እናም አላባውያን ለሚለው ቃል ባዕድ አይደለህም ማለት ነው። ስለዚህም በዚህ ምዕራፍ “የተውኔት አላባውያን” ስንል እንደሌሎች የስነጽሁፍ አላባውያን ሁሉ ተውኔትን “ተውኔት” ያደረጉ ፤ የነሱ መኖር ተውኔት እንዲኖር ምክንያት የሆኑ አካላት እንደሆኑ መገመትህ አይቀርም አንድን

ቤት ለመስራት የግድ ቋሚና ጣሪያ ማበጀት ያለብንን ያህል አንድን ተውኔት ለመጻፍም የግድ የተወሰኑ አላባውያን ግድግዳና ጣሪያ ሊሆኑን ይገባል። የተጣመመ ግድግዳና የተበሳሳ ጣሪያ የበቱን ቤትነት ጥያቄ ውስጥ እንደሚጥል ሁሉ ፣ የተውኔት አላባውያን በሚገባ ተሳክቶው መቀመጥና አለመቀመጥ ተውኔቱን ሙሉዕ ወይም ጉደሎ ሊያደርገው ይችላል።

በዚህ ምዕራፍ የምናጠናቸው ተውኔትን ሙሉዕ ወይም ጉደሎ የሚያደርጉ አላባዉያንን በተመለከተ እንደበርካታ የስነጽሑፍ ብያኔዎችና የይዘት አደረጃጀቶች ሁሉ ወጥ የሆኑ ስምምነቶች የሉም፡፡ የተለያዩ የመስኩ ምሁራን የተውኔት አላባውያንን በቁጥር ከ3 እስከ 7 ያደርሷቸዋል፡፡ መቼት፣ ገፀባህራያት ፣ ሴራ፣ ቃለ-ተውኔት፣ ጭብጥ፣ ሃሳብ ፣ ቋንቋ፣ ሙዚቃ፣ ትዕይንት በተለያየ ዘመን እና ጊዜ በተውኔት አላባውያን ሲመረጡ ይስተዋላሉ (ፋንታሁን ፣2001)፡፡

| |
|---|
| ከላይ ከተጠቀሱት ዘጠኝ አላባውያን ውስጥ የበለጠ ተውኔትን ሊገልፁ ይችላሉ የምትላቸውን አምስት አላባውያንን ብቻ ዘርዝር፡፡<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------ |

በዝርዝር ውስጥ መቼት፣ ገፀባህራያት፣ ሴራ፣ ቃለ፣ ተውኔት እና ጭብጥን ማካተት ቻልክ?
ጥሩ ነው፡፡ ፋንታሁን (2001፣73) እንደሚለወጥ በዚህ ዘመን ያሉ የመስኩ ምሁራን የተውኔት አላባውያን እንደሆኑ የሚስማሙባቸው ከላይ የተጠቀሱትን አምስቱን አላባውያን ነው፡፡ በዚህ
ሞጁልም በዝርዝር የምንመለከታቸው እነዚህኑ አምስት አላባውያን ይሆናል፡፡ ከመቼት እንነሳ

## 3.1 መቼት

| |
|---|
| "መቼት" ምን ማለት ነው?<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------ |

መቼት የተውኔት ዋነኛ አላባ ነው፡፡ መቼት ስንልም የሚከተሉትን ሶስት መሰረታዊ ሀሳቦች በውስጡ ያቅፋል፡፡

ሀ. ተውኔት የሚከናወንበት ቦታ

ለ. ተውኔት የሚከናወንበት ጊዜ

ሐ. በተውኔት ክንውን ዘመን የነበረው ማህበራዊ እውነታ

በመጀመሪያው ላይ የተጠቀሰው ተውኔቱ የሚከናወንበት ቦታ የሚያመለክተው ፀሐፊ ተውኔቱ የተውኔቱ ታሪክ ተፈጽሞበታል ብሎ ያሰፈረውን የታሪኩ ክንውን ቦታ ነው፡፡ ለምሳሌ በሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን "የከርሞ ሰው" ተውኔት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ጉላ ሰፈር፣ እዛ ሰፈር ውስጥ የምትገኝ "… በጋዜጣ ወረቀትና በሳሙና ሳጥን የተለደበችና የተጠጋገነች ማዕድ ቤት የምታህለው አንድ ክፍል ጎጆ …" (ፀጋዬ ፣9) ተውኔቱ የሚከናወንበት ቦታ ነው፡፡

የፋንታሁን እንግዳ “ ሸርገጠ” ተውኔትን ስንመለከት ዳግም የተውኔቱ ቦታ አዲስ አበባ ውስጥ በሚገኝ በዋናው ገፀባህሪ በሸርገጤ መኖሪያ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ቤቱም “ በዘመን አመጣሾቹ የድንጋይ ቤቶች ዝነኝነቱን ከመነጠቁ በፊት በጥራትም ሆነ በስፋት ከቤተ - እግዚአብሔር አይተናነስም ነበር፡፡ … ቤቱ ብዙ የመኝታ ክፍሎች ከተንጣለለ ሳሎን ጋር ይዟል፡፡(ፋንታሁን፣ 74) እነዚህ ሁለት ቤቶች ከመቼት ክፍሎች ውስጥ የታሪኩን ቦታ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ተውኔቱ የሚከናወንበት ጊዜ ሌላው የመቼት አንድ አካል ሲሆን፣ የተውኔቱ ታሪክ የሚከናወንበት ጊዜ የሚያመለክት ነው፡፡ የተውኔቱ ታሪክ በየትኛውም ዘመን ፣ በየትኛው ስዓትና ደቂቃ እየተፈፀመ እንዳለ በሚያመለክተው በዚህ ክፍል ፀሐፊ ተውኔቱ ጊዜውን ፊት ለፊት ወይም ከገፀባህሪያቱ አጠቃላይ ሁኔታ ተነስተን እንድንገምት ያደርጋል፡፡ ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን “በከርሞ ሰው” ተውኔቱ የታሪኩን ጊዜ “ ቀኑ ቅዳሜ ነው፡፡ መጋረጃው ሲከፈት ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተሩብ ነው፡፡ “ ሲል ፊት ለፊት ይገልጸዋል፡፡ በዚህ ተውኔት ከላይ ከተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች ወረድ ብለው እንዲህ የሚሉ አረፍተነገሮች እናገኛለን “ሞገስ ካልጋው ተነስቶ ከበራፍ ጥግ በሚገኘው ጠርሙስ ውሀ ፊቱን ይታጠባል፡፡ አቶ ዘርፉ ከበስተ ግራ በሚገኘው የእንጨት አልጋ ላይ ተኝቷል፡፡…”

ከላይ የሰፈረው ሀሳብ ከገፀባህሪያቱ ሁኔታ ተነስተን ጊዜን ጠዎት እንደሆነ የምንገምትበት ነው፡፡ ባጠቃላይ ተውኔት የሚከናወንበት ጊዜ በተለያየ መንገድ ሊቀርብ የሚችል ቢሆንም፣ በየትኛውም መንገድ ይቅረብ የተውኔቱን ጊዜ በግልጽ መጠቆም ይጠበቅበታል፡፡

በተውኔቱ ክንውን ዘመን የነበረው ማህበራዊ እውነታ ሌላው መቼትን የሚገልጽልን ጉዳይ ነው፡፡ በታሪኩ ክንውን ቦታና ጊዜ የተፈፀመ ወይም የነበረ ማህበራዊ እውነታ የታሪኩን መቼት ሙሉ ያደርግልናል፡፡ ለማሳያነት ከጌትነት እንየው (2000 ፣ 2) “እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ተውኔት “ ጥቂት ቅንጫቢ እንውሰድ፡፡

> … ይህንኑ ሐቅ እኮ ነው ዛሬም በጣይቱ ብጡል የምናየው! … ስሜን ከሉስንዩስ ፣ የጁ ከወረሼኮች የተመዘዘች የዘር ሀረግ፣ ይኸው ፣ደብረ ታቦር -በጌምድር ተወልዳ፣ ጎጃም -ደብረ ማዊእ ታጭታ፣ አንኮበር - ሸዋ ተሠርጋ ፣ ፊንፊኔ የሀገር እምብርት ድረስ ተስባ፣ከንጉስ ምንሊክ ጎን ቆማ ሀገር አቁማ ልታቆይ ፣ ጣይቱ ብጡል ግብግብን ተያይዛ ኮነው የምናየው!!…የአውሮጳ ጋያላን አፍሪካን አንድ ፍሪዳ ቅርጫ ጥላው ፣ አፋቸውን ከፍተው ፣ ጥርሳቸውን ስለው ፣ አገር እንደብርንደ መቦጫቅ የጀመሩበት ፈታኝ የታሪክ ወቅት…1879 ዓመተምህረት! …በዚህ ፣ ታላቅ የአእምሮ ብልሃት፣ ብርቱ የመንፈስ ጽናት በመጠይቅ የትንቅንቅ ዘመን ነው፣ ጣይቱ ብጡል ከጣሊያን መሰሪ ተልዕኮ ጋር ግብግብ የገጠመችው

ከላይ የቀረቡት ሀሳቦች መቼት የሶስት አካላት ድምር ውጤት መሆኑን ይገልጽልናል፡፡

እነዚህ ሶስት አካላት በጥምርት የሚቀርቡና የሚተሳሰሩ ሲሆን በተለይ በተውኔታዊ መቼት ውስጥ ሰብሰብ ብለው ይቀርባሉ፡፡እንደተፈጥሮ ወይም እንደ ልብ ወለድ መቼቶች ልቅና ሰፊ ቦታዎችን የሚሸፍን አይደለም፡፡ የተውኔት መቼት የተመረጠ እና መድረክ ላይ ሊሰናዳ በሚችል መልኩ መጻፍ ይኖርበታል፡፡ በተለይ የተለየ አይነት መድረክ በማይገኝበት ሁኔታ ተውኔታዊ መቼቶች ሲጻፉ በተቻለ መጠን መድረኩ ላይ ሊተረጐሙ በሚችል መልኩ መቅረብ አለባቸው

የተውኔት መቼት በሚጻፍበት ወቅት አጠቃላይ ወይም ውስን መቼቶችን የያዘ ይሆናል፡፡ አጠቃላይ መቼት የታሪኩ መከወኛን ቦታ እና ጊዜን ሰፋ አድርገን የምናቀርብበት ሲሆን፣ ውስን መቼት ዳግም የታሪኩን ቦታና ጊዜ መጥነን የምናቀርብበት የመቼት አይነት ነው፡፡ ሆኖም በሁለቱም መልኩ የሚቀርቡ መቼቶች እንደልብ ወለድ መቼት ያልተገደበ አቀራረብ ሊኖራቸው አይገባም፡፡

ብዙውን ጊዜ በመድረክ ወይም በሌላ ቅርጽ ሲቀርብ /ሲመደረክ መቼቱን በማስመሰል ለመፍጠር ይሞክራል፡፡ ለምሳሌ ከዛሬ 1ሺ አመት በፊት ስለነበረ ታሪክ ስናቀርብ፣ ዘመኑንና ጊዜውን የሚወክል ነገር የማግኘት እድላችን ጠባብ በመሆኑ ያንን ዘመንና ቦታ ሊወክል የሚችል መቼት አስመስለን እንፈጥራለን፡፡ በተለይ መድረክ ላይ የሚቀርብ ከሆነ ዳግም ማስመሰል ግድ ይለናል፡፡ ስለሆነም በርካታ መቼቶችን እያለዋወጥን ለመስራት ቦታውም የዝግጅት ሂደቱም፣ ወጪውም ከባድ በመሆኑ መቼት ጠባብ ሆኖ እንዲሰራ ይመከራል፡፡ የተውኔት መቼት በፀሐፊ-ተውኔቱ ሲጻፍ ግልጽ እና በቂ በሆነ መንገድ መቅረብ አለበት፡፡ ይህም አዘጋጅ የታሪኩን አጠቃላይ ድባብ እንዲረዳውና ለመድረክ ወይም  በሌላ ቅርጽ ሲያቀርበው እንዳይቸገር ይረዳዋል፡፡ ተዋናዮቹም የገፀባህሪውን አጠቃላይ ሁኔታ እንዲረዱ ስለሚያግዛቸው መቼት በተውኔት ውስጥ ግልጽ ፣ ምጥንና በቂ በሆነ መልኩ መገለፁ እጅግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡
በተውኔት ውስጥ መቼት በአራት አይነት መልኩ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከዚህም አኳያ የመቼት አይነቶች (1) የቤት ውስጥ መቼት (2) የቤት ውጪ መቼት (3) ባዶ መቼት እና (4) ልዩ መቼት በመባል ይከፈላሉ (ፌንታሁን 1992፣ 16-27)፡፡

የቤት ውስጥ መቼት (Box setting) ብዙ ጊዜ በተውኔት ጽሑፍ እና መድረክ ላይ የሚቀርብ የመቼት አይነት ሲሆን በውስን ክፍሎች ውስጥ ታሪኩ የሚፈጸምበት የመቼት አይነት ነው፡፡ በመማሪያ ክፍል ፣ በመኝታ ቤት፣ በመጠጥ ቤት…ወዘተ. ውስጥ ታሪኩ የሚፈጽም ከሆነ መቼቱ የቤት ውስጥ መቼት ይባላል፡፡

የታሪኩ ክንውን የሚደረገው ተፈጥሮን ባማከለ መልኩ ከቤት ውጪ ከሆነ ፣ የተውኔት መቼጽ፣ የቤት ውጪ መቼት ይባላል፡፡ ብዙውን ጊዜ በዚህ የመቼት አይነት ዛፎች፣ በረንዳዎች ፣ ከርቀት የሚታዩ ቤቶች ወይም መንገዶች ይገለጻሉ፡፡ በተቻለ መጠንም ከቤት ውጭ ያለውን ድባብ ለማሳየት ይሞከርበታል፡፡

ሶስተኛው የመቼት አይነት ባዶ መቼት በመባል የሚጠራው ነው፡፡ በዚህ የመቼት አይነት ቦታዎችን ለማመልከት የሚደረግ ጥረት የለም፡፡ በተለይ ተውኔቱ መድረክ ላይ የሚቀርብ ከሆነ መድረኩ በፊት ከነበረው የሚጨምር ወይም የሚቀነስበት ነገር የለም፡፡ መድረኩ የተውኔቱን ጊዜና ቦታ ለማመልከት የተለየ ነገር አይደረግበትም፡፡
ልዩ መቼት በአራተኛ ደረጃ የሚገኝ የመቼት አይነት ሲሆን ከሶስቱ የመቼት አይነቶች ውጭ በሆኑ ቦታዎች ታሪኩ የሚፈጸምበት ነው፡፡ ለምሳሌ መኪና ውስጥ ድርጊቱ የሚፈፀም ከሆነ በልዩ መቼትነት ይታያል፡፡፡ ይህ አይነት መቼት መድረክ ላይ በሚቀርብ ተውኔት ላይ
ለመተግበር የሚያስቸግር ሲሆን፣ በሌላ ቅርጽ በሚቀርብ ተውኔቶች ላይ ግን ማቅረቡ እምብዛም አስቸጋሪ አይደለም፡፡

የሚከተሉት ቅንጫቢዎች ከተለያዩ ተውኔቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ እነዚህን ቅንጫቢዎች በማወዳደር የትኛው የተሻለና ሙሉ የተውኔት መቼት እንደሆነ ከነምክንያቱ አብራሩ፡፡

በአቶ ባንቲደሩ የተንጣለለ ቪላ የምግብ ክፍል ውስጥ፣ ከሐር መጋረጃውና ከስጋጃው ምንጣፍ አንስቶ እስከ ብርጭቆና መለኪያ ድረስ እቃው ሁሉ የባለቤቱን ባለፀጋነት ቱልቱላ ይነፊል፡፡ ጣሪያው በወረቀት አበባ ሰንሰለት አጊጧል፡፡

ባልና ሚስት ልጆችና እጮኛ ግሩም በሆነ ሶፋ ላይ ዙሪያው ክብ ተቀምጠዋል፡፡ ራት የበሉበት ጠረጴዛ ባንድ ጐን ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ቴሌፎን አለ፡፡ ከቴሌፎኑ በላይ የቀድሞው ንጉስ ስዕል በክብርና በጌጥ ተሰቅሏል፡፡ ተጋባዦቹ ተዝናንተዋል፣ ልጅ እግሮቹ ይሳሳቃሉ፡፡

… በአሁኑ ሰአት ሁሉም ጥሩ ራት በልተው በዚች አለም በመፈጠራቸው ተደስተዋል፡፡ እዚህ ላይ ሀብቴ ልዩልዩ የመጠጥ ጠርሙስ ከብርጭቆና ከመለኪያ ጋር የተሸከመ ተሽከርካሪ ጠረቤዛ እየገፋ ይመጣና ራቅ ብሎ እጁን አጣምሮ ይቆማል፡፡

(ጄ.ቢ. ኘሪስትሊ፣ አዛማጅ ትርጉም መንግስቱ ለማ 1975፣ 186፣ ጠያቂ)

÷ ÷ ÷

ጊዜው ሌሊት መሆኑን ለማስረዳት ከጣራው ላይ ክዋክብት የተሳሉበት ትልቅ ሰሌዳ ይታያል፡፡ ከመጋረጃው ውስጥ አንዲት ሴት ስትጨነቅ ድምጽዋ ይሰማል፤ አንድ ሰው ከደጅ ተቀምጧል፡፡ ከጓዳ ገረድ ወደ እሱ ትመጣለች፡፡(የትንቢት ቀጠሮ ፣ ከበደ ሚካኤል ፣ 1957፣ 25)

÷ ÷ ÷

ነጐድጓድና መብረቅ ሲያስተጋባ ሠለስቱ የቃልቾች ርኩስ መናፍስት ይሰማሉ፡፡ (ማክቤዝ፣ ዊልያም ሼክስፒር፣ ትርጉም ፀጋዬ ገብረመድህን ፣ 1964)

÷ ÷ ÷

በጐንደር ቤተ መንግስት በእቴጌ መነን እልፍኝ እቴጌ መነን ራስ አሊ፣ አንድ መነኩሴ፣ መኳንንቶች ፣ አንድ የልፍኝ አሽከር (ቴዎድሮስ ፣ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት 1960፣15)

÷ ÷ ÷

…ቀኑ ቅዳሜ ነው፡፡ መጋረጃው ሲከፈት ከጧቱ ሁለት ሰአት ተሩብ ነው፡፡ ሞገስ ካልጋው ተነስቶ ከበራፍ ጥግ በሚገኘው ጠርሙስ ውሃ ፊቱን ይታጠባል፡፡ አቶ ዘርፉ ከበስተግራ በሚገኘው የእንጨት አልጋ ላይ ተኝቷል፡፡ ከራስጌ አንድ ጩቤ ከነአሮጌ አፎቷ ተሰቅላለች፡፡ የቤቱ መግቢያ በር ከበስተግራ ነው፡፡ የበስተጀርባው ግድግዳ ከባለቤቱ ጓሮ የተቀጠለ በመሆኑ እንደበስተቀረው የሳሙና ሳጥን ዛኒጋባ ሳይሆን የጭቃ ማገር ነው፡፡ የሞገስ የቦንዳ ብረት አልጋ ከዚህ ግድግዳ ተደግፎ ቆሟል፡፡ ከዚህ አልጋ ግርጌ ከፍ ብሉ

የተሸነቆረው ቀዳዳ መጨቅጨቂት በመሰለ እራፊ ተወተፏል፡፡ ውታፊው ሲከፈት ከባሻ ተሊላ ቤት ውስጥ ጢሱ ወዲህ ይገባል፡፡ ከመግቢያወ በር ፊት ለፊት ካለው ጠረጴዛ ላይ ግማሽ የስሙኒ ዳቦ ፣ ሁለት የዲቴክቲቭ ልብ ወለድ የእንግሊዘኛ መጻህፍት ፣ አንድ ፔርሙዝ ምጅጃና ክብሪት፣ ከስሩም ጨርቁ የተበጣጠቀ ሶፋና አንድ የእንጨት ወምበር ባዶ ትሪይ የተቀመጠበት ይታያል፡፡ ከሶፋው ራስጌ ክራር ተሰቅሎአል፡፡ ተኮላ ጣቱን በመዳፉ ቀዳዳ አሾልኮ የበሩን መወርወርያ ከፍቶ ሲገባ ሞገስ ተነስቶ በማየቱ ቆም ይልና ወዲያው አንገቱን እንደ አባያ በሬ ቀልሶ ያልፍና ትሪውን መሬት አስቀምጦ ወምበሩ ላይ ተንፈራጥጦ ይወዘፋል፡፡ ሞገስ እንዳላየ ዝም ይላል፡፡ (ፀጋዬ ገብረመድህን፣ የከርሞ ሰው፣ 1958፣ 10-11)

÷ ÷ ÷

ከበረንዳው ባንደኛው ጫፍ ከሳጠራ የተሰራ ጠረጴዛ ቆሟል፡፡ ከጠረጴዛው ላይ ልዩልዩ የመድሃኒት ብልቃጦችና ጠርሙሶች ተቀምጠውበታል፡፡ ከሳጠራው ጠረጴዛ አለፍ ብሎ አንድ የእንጨት ወንበር አለ፡፡ በሽተኞችን አጋድሞ የሚመረምርበት አግዳሚ ወንበርም በመጋረጃ ከለል ተደርጎ ይታያል፡፡

÷ ÷ ÷

ለመንደሩ መርፌ ወጊ እንደ ዘበኛም እንደ ድሬሰርም የሚያገለግለው ገረመው በአሮጌ ቱታ ላይ ነጭ ካፖርት ደርቦ ከጠረጴዛው ላይ ያሉትን የመድሃኒት ብልቃጦችንና የመርፌ መውጊያ ስትሪንጋውን እየወለወለ በቦታ፣ በቦታው ያስቀምጣል፡፡ከቤቱ በስተጀርባ የተሰበሰቡት በሽተኞች ደግሞ ሲንጫጩ ይሰማሉ፡፡ (ፋንታሁን እንግዳ፣ የመንደሩ መርፌ ወጊ፣19፣87)

÷ ÷ ÷

| |
|---|
| ከዚህ በታች ታሳቢ ተደርጐ የተጻፈውን ሀሳብ መነሻ አድርገህ የመድረክ ተውኔት መቼት ጻፍ |

- ዲላ ዩኒቨርሲቲ ቤተመጽሐፋ ውስጥ እንደተቀመጥክ አስብ፡፡ ቤተመጽሃፍት ውስጥ ያለውን የወንበር ፣ የጠረጴዛ እና የመጽሐፍ መደርደሪያ አቀማመጥን ለማስታወስ ሞክርክ? ተማሪዎቹ የተቀመጡበት ሁኔታ፣የደብተር የመጽሃፍና የጋዜጦች በየቦታው መበታተን፣ምናልባት ጊዜው ዝናባማ ነበር ብለህ ገምተህ ያለውን አጠቃላይ ድባብም አስብ፡፡ ቤተመጽሃፉን በአይነ ህሊናህ ለመሳል ሞክርክ? ይህን እይታህን ሳትለቅ መድረክ ላይ ሊታይ የሚችል ተውኔት መቼት ጻፍ፡፡

## 3.2 ገፀባህሪ

ገፀባህሪ ከተውኔት አላባዊያን አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ማንኛውም የስነጽሑፍ ውጤት ካለ ገፀባህሪያት እውን እንደማይሆን ሁሉ ተውኔትም ያለገፀባህሪያት የሚታሰብ ጉዳይ አይደለም፡፡

ብዙውን ጊዜ የተውኔት ገፀባህሪያት እና ተዋንያን ያላቸው ግንኙነት ተተካኪ እየሆነ የሚያስቸግራቸዉ ተማሪዎች አሉ፡፡ ላንተ ገፀባህሪ እና ተዋናይ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------

ምላሽ ለመስጠት ሞከርክ? መልካም ነው፡፡የተውኔት ገፀባህሪያት ማለት በእውኑ አለም ያሉትን ሰዎች የሚወክሉ የምናብ አለም ወይም ታሪክን መሰረት ያደረጉ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ገፀባህራያት እንደሰው የሚናገሩ፣ የሚያዳምጡ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ …ባጠቃላይ ሰው ሰው የሚሸቱ ባህራያት ናቸዉ፡፡ ኖረውበታል ተብሎ የሚታሰበውን ጊዜና ቦታ እንዲሁም ማህበራዊ ሁኔታን ሊወክሉ የሚችሉ በመሆናቸዉ አንድ ወቅትና ቦታ የምናውቃቸው ሰዎች ይመስላሉ፡፡

ተዋንያን በበኩላቸው በምናብ አለም ያሉ ሰዎች ሳይሆኑ በእውን ያሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ሆኖም በመድረክ እና በሌላ ቅርጽ ተውኔቱ ሲመደረክ የራሳቸውን ባህሪ በመተው የገፀባህሪውን ባህሪ ተላብሰው ይጫወታሉ፡፡ ስለሆነም ተውኔቱ ሲመደረክ እንጂ በጽህፈተ ተውኔት ውስጥ ተዋንያንን አናስብም፡፡

ገፀባህሪያት ከአይነት አኳያ በሁለት ምድብ ውስጥ ይካተታሉ፡፡ በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ የሚካተቱት አብይ ገፀባህሪያት የሚባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ገፀባህሪያት ከተለያየ አቅጣጫ የተሳሉ ሲሆን ስነልቦናዊ፣ ፣ አካላዊ ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ልንናገርላቸው የምንችል፣ ሆኖም ግን በቀላሉ ልንረዳቸው የማንችላቸው ገፀባህሪያት ናቸው፡፡ እነዚህ ገፀባህሪያት በተውኔቱ ውስጥ የተለያየ እንቅፋት የሚያጋጥማቸው ሲሆን፣ ታሪኩም እነርሱን ተከትሎ ይሄዳል፡፡

ዋና ገፀባህሪያት ታሪኩ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ብዙውን ጊዜ እስከመጨረሻው ድረስ ልናገኛቸው እንችላለን፡፡ ማንነታቸውንም ሙሉ ለሙሉ የምንረዳው በታሪኩ መጨረሻ አካባቢ ነው፡፡ እነዚህ ገፀባህሪያት ልክ እንደኳስ ናቸው አገላብጠን ካላየናቸው በስተቀር ፊትለፊት ባለው ገጽታቸው ብቻ አጠቃላይ ምንነትቸውን ልንረዳ አንችልም፡፡ ስለዚህም በአንዳንድ የመስኩ ባለሙያዎች ክብ ገፀባህሪያት እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ ፈርጀ ብዙ፣ ውስብስብ፣ ኢ-ውስን የሚል ተጨማሪ ስያሜም አላቸው፡፡

ሁለተኛው የገፀባህሪ ምድብ ንኡስ ገፀባህሪያትን ይይዛል፡፡ ንኡስ ገፀባህሪ በተውኔቱ ታሪክ ውስጥ ጐልተው የማይታዩ፣ ብቅ ብለው ሊጠፉ የሚችሉ እና አብይ ገፀባህሪውን ለማድመቅ የሚፈጠሩ ገፀባህሪያት ናቸው፡፡ ከባህሪያቸው በመነሳትም ዝርግ፣ ፈርጀ አንድ፣ ነጠላ፣ ውስን እና አስተኔ ገፀባህሪያት በሚሉ የተለያዩ ስየሜዎችም ይታወቃሉ፡፡

እነዚህ ንኡስ ገፀባህሪያት በተውኔቱ ውስጥ ብቅ ባሉ ቁጥር ወዲያው ማንነታቸውን የሚታወቅ ሲሆን፣ ማንነታቸውን ለማወቅ የታሪኩን መጠናቀቅ መጠበቅ ግድ አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ የጥበቃን፣ የቤት

ሠራተኛን፣ የሴተኛ አዳሪን ፣ የሀኪምንና መሰል ስማቸው ከግብራቸው ጋር የሚሄዱ አካላትን ወክለው ይሳላሉ፡፡ ስሙ ከያዘው ግብር በተለይም በተውኔቱ ውስጥ ሌላ ሚናን ወክለው አይሳተፉም፡፡

እነዚህ ሁለት የገፀባህሪ አይነቶች በተውኔቱ ውስጥ ቢኖሩም ፀሐፊ ተውኔቱ በአትኩሮት የሚስለው ዋናዎቹን ገፀባህሪያት ነው፡፡ የእነዚህ ገፀባህሪያት አሳሳል (አቀራረብም) ብዙውን ጊዜ ሁለት መልክ ይኖረዋል?

| |
|---|
| ሁለቱን አብይ የገፀባህሪያት አሳሳል (አቀራረብ) መንገድ ዘርዝር፡፡<br>ሀ. ……………………………………………………………………………………<br>ለ. …………………………………………………………………………………… |

ሁለቱን መንገዶች ለመዘርዘር ሞከርክ? መልካም በሙከራህ የገጸባህርያት አሳሳል መንገዶች (1) ርቱዕ እና (2) ኢ-ርቱዕ ናቸው ማለት ከቻልክ ሙከራህ ትክክል ነው ማለት ነው፡፡

ገፀባህሪያት ሲሳሉ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱን መንገዶች መነሻ ያደርጋሉ፡፡ በተውኔት ውስጥ ያሉ ገፀባህሪያት በአብዛኛው የሚሳሉት በኢ-ርቱዕ መንገድ ነው፡፡ ገፀባህሪያቱን በደንብ የምንረዳውም ፣ የታሪኩን ፍሰት የሚጓዘውም በዚህ ኢ-ርቱዕ  መንገድ የተሳሉ እንደሆነ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን ከመቼት ገለጻው ጋር ተጣምሮ ዋናዎቹን ገፀባህሪያት በመጠኑ በርቱዕ መንገድ ለማሳየት የሚሞክሩ ፀሐፊ ተውኔቶች ያጋጥሙናል፡፡

| |
|---|
| ለመሆኑ ርቱዕ እና ኢ- ርቱዕ የገፀባህሪያት አሳሳል ስንል ምን ማለታችን ነው፡፡<br>……………………………………………………………………………………<br>……………………………………………………………………………………<br>……………………………………………………………………………………<br>………………………… |

ርቱዕ የገፀባህሪ አሳሳል ስንል ከዳር ሆነን ስለገፀባህሪው የምንገልጽበት የአሳሳል ደረጃ ነው፡፡ የገፀባህሪውን ማንነት እና ምንነትን ከገፀባህሪው ድርጊት እና ንግግር ሳይሆን እኛን በጹሑፍ ውስጥ በመግለጽ እገሌ ማለት እንዲህ ነው ብለን የምናቀርብበት ሂደት ርቱዕ የገፀባህሪ አሳሳል ይባላል፡፡ ይህ ብዙ ጊዜ በተውኔት ውስጥ የተለመደ አይደለም፡፡

ከዚህ በታች የቀረበው ምሳሌ ለርቱዕ የገፀባህሪያት አሳሳል ምሳሌ ሊሆን የሚችልና ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን (1958፣9) በየከርሞ ሰው ተውኔታቸወ በገቢር አንድ ከመቼት ገለጻ ጋር አጣምረው ያቀረቡት ነው፡፡

…ሞገስ የውሃና የመብራት ችሎ በአስራ ሶስት ብር የተከራያት በጋዜጣ ወረቀትና በሳሙና ሳጥን የተለበደችና የተጠጋገነች ማዕድ ቤት የምታህለው አንድ ክፍል ጉጆ“ ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል“ ናት፡፡…

ሞገስ ተገባባት ሦስተኛው አመት ባለፈው ወር ጀመረ የመዝገብ ቤት ፀሐፊ ሆኖ በስድሳ አምስት ብር ከተቀጠረ አስራ አንድ አመት ሆነው፡፡ በዚች በአስራ አንድ አመቱ ውስጥ ከትጋት ይልቅ ጥንቃቄንና አንገት ማቀርቀርን አውቋል፡፡ ሰላሳ ሶስት አመቱ ነው፡፡ የዛሬ ሁለት አመት ነው ከሚስቱ የተለያየው፡፡ ነርብ በሚሉት የደም ስር ምክንያት አእምሮው ተነክቶ አማኑኤል ሆስፒታል ሁለት ወር በተኛበት ስሞን አራስ ልጅዋን በድንጋጤ እንዳይሞትባት በማለት ሞገስን ከሆስፒትል ሳይመለስ ይዛው ኮበለለች ይላሉ፡፡ ግን እሱን ለዚህ በሽታ ያበቃው ብስጭት አማርሮአት ስለነበር የመገላገየ ምክንይትና ጊዜ እስኪመቻች ትጠብቅ ነበርና በዚያን ሰሞን ቶሎ ሾልካ ነው እንጂ ወትሮም በቅቶአታል የሚል ወሬም አለ፡፡

የሞገስ ታናሽ ወንድም ተኮላም አብሮት ይኖራል፡፡ተኮላ በአካል ብቻ ሳይሆን በአእምሮም የጠጠረ የሀያ ሦስት አመት ጉርባ ነው፡፡ አጐታቸው አብዬ ዘርፉ የዘመድ አዝማድ መርዶ ይዞ ከመጣ አስር ቀን ሆነው፡፡ የአባታቸውንም የአንድ ጋሻ መሬት ውክልና ለልጆቹ መልሶ ለማስረከብ ወስኖአል፡፡ አቶ ዘርፋ በስድሳ ሰባተኛ ዘመኑ የአንጀት መቁሰል በሽታ ካደረበት ሰንብቶአል፡፡

ኢ-ርቱዕ የገፀባህሪያት አሳሳል የምንለው ዋነኛው በተውኔት ውስጥ ገፀባህሪያትን የምንስልበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ የገፀባህሪያት አሳሳል ገፀባህሪያትን እንዲህ ናቸዉ ብለን አንገልጽም፡፡ ከዛ ይልቅ ገንባህሪያቱ ከሚያደርጉት ድርጊት ፣ ከሚናገሩት እና ሌሎች ስለነሱ ከሚናገሩበት ሁኔታ ተነስተን ማንነታቸውን ለማሳየት የምንሞክርበት ነው፡፡ ይህ አይነት አሳሳል የገፀባህሪያት ማንነት እንዲ ተዘርግፎ እንዳይበቃ ከማድረጉም ባሻገር፣ ገጸባህሪያቱን በደንበ እንደምናውቃቸው እንዲሰማን ያደርገናል፡፡ ከዚህ በታች ያለው ምሳሌ “ ተጫኔ” የተሰኘው የመንግስቱ ለማ የባለካባና ባዳባ ተውኔት (1975፣147-9) ገፀባህሪን ለማሳያነት የቀረበ ሲሆን በኢ-ርቱዕ አቀራረጽ የተጫኔ ማንነት እንዴት እንደተሳለ እናስተውላለን፡፡

ዘበኛ፤ ጌታዬ አንድ ሽማግለ በቢት የመጡ እደጅ ተጉልተዋል። እርሶን ካላየሁ ይላሉ።
ተጫኔ፤ ማነኝ ይላሉ።
ዘበኛ፤ ስማቸውን አልነገሩኝም። ጌቶቹ ስሜን ያውቁታል ይላሉ።
ተጫኔ፤ (ይጮሀል )ወይ መከራ! የስንቱን ሽለግሌ ስም ላውቅ ነው እንግዲህ? መልኩ ምን ይመስላል?
ዘበኛ ፤ ረዘም ቀጠን ያሉ ናቸው፤ ሽበቶ።
ተጫኔ፤ እደሜውስ?
ዘበኛ ፤ ጠና ያሉ ናቸው። ከሰባ ያንሳል? ከሩቅ አገር መጣሁ ይላሉ። ከባላገር።
ተጫኔ፤ ጉዳዩ ምንድን ነው?
ዘበኛ ፤ ጉዳይ የለኝም አሉ። የርስዎን የጌቶችን አይኖን ለማየት ብቻ ነው አሉ። መንገድ መቷቸዋል ጌታዬ፤ እግራቸው አቧራ ለብሷል፤ ተሰነጣጥቋል።
ተጫኔ፤ ወዲያ አባርልኝ። ለስራ ፈት ጊዜ የለኝም። የለም በል ፤ ናዝሬት ሄደዋል በል።
ዘበኛ ፤ ብዬአቸው! አሁን በመኪና ሲገባ አይቼዋለሁ እያሉ ድርቅ አሉብኝ። ደግሞ የቸገረኝ ነገር አለ
ተጫኔ፤ ምን?
ዘበኛ ፤ ከፈቀዱልኝ ልንገርዎ - ሽማግሌው የሚሉትን።
ተጫኔ፤ ወይ ጣጣ! ምንድንነው ነገሩ? ተንፍሰው ይውጣልህ።
ዘበኛ ፤ ኸረ ከበድ ያለ ነገር ነው የሚናገሩት -
ተጫኔ፤ ምን ይላሉ?
ዘበኛ ፤ አባት - አባትዎ - ነኝ ይላሉ።
ተጫኔ፤ (ብው ይላል በቁጣ) ቀጣፊ ነው። አባት የለኝም። አባቴ ገና ድሮ ሞቷል፤ ለባንዲራው ለነፃነቱ ሲዎጋ ደሙን አፍሷል ፣ አጥንቱን ከስክሷል:: የማንንም አጭበርባሪ ስብከት ወሬ ብለህ ማምጣትህ!:: አንተ ክፍኛ ደፈርከኝ - በወንጀል ላስቀፍድድህ እችላለሁ -ትሰማኛለህ? አባት የለኝም፣ ሞቷል ነው የምልህ። ያባባን ነፍሱን ይማረው።
ዘበኛ፤ (ሳይደነግጥ ይሽቆጠቆጣል) እኔም ለሽማግሌው ነግሬውአቸዋለሁ የጌቶች አባት በማይጨው ጦርነት ከጣሊያን ሲዋጉ ሞተዋል፣ታላቅ ፊታውራሪ ታላቅ አርበኝ ነበሩ ብዬ አስተባብያለሁ። ሽማግሌው አይሰሙም፣ ወንድሜ! አባቱ እኔ ነኝ፣ አለሁ ፣ ይኸው እዚህ በህይወት እገኛለሁ ይላሉ። ምናልባት፣ የጌቶች ክርስትና አባት እንደሆኑ?
ተጫኔ፤ የለኝም ስልህ! ክርስትና አባትም የለኝም። እሱም ሞቷል።
ዘበኛ፤ የንሰሐ አባትስ? ሻሽ ቢጤ አስረዋል።
ተጫኔ፤ (ብድግ ይልና ያፈጥበታል) የንሰሐ አባት ይኁኔ አላውቅም።
ዘበኛ፤ እንግዲያ ጌታዬ ይቅርታ ያድርጉልኝ። ሽማግሌው አጠራጥረውኝ ነው።
ተጫኔ፤ ስማኝ፣ አሁን ስለቀባጠርከው ሁሉ ያንድ ወር ደሞዝ ቀጥቼሃለሁ። በል አሁን እያየሁህ ሂድና ቀስ ብለህ ሽማግሌውን ከዚህ ግቢ አስወጣ። እምቢ ካለህ በዱላ ነርተው። ሁለተኛ ዝር ቢል ካንተ ነው ጠቤ። ወየውልህ!

ተጫኔ ምን አይነት ሰው ነው? ሽማግሌውስ አባቱ ይመስሉሃል? ከሆኑስ ለምን አላመነም?

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………………

ምላሽህን አንተው ራስህ ደግመህ አንብበው፡፡ ትክክል ነህ? ጥሩ የሆነ ሆኖ ይህንን የሰጠኸኝን ምላሽ ለመስጠት መረጃህ ምን ነበር? እንዴት ስለተጫኔና ስለሽማግሌው አወቅክ? ምላሽህ የገጸባህሪውን ማንነት ከማወቅ የመነጨ ነው ይህ እውቀት ደግሞ ገጸባህሪው ኢ-ርቱእ በሆነ መንገድ ሲሳል ከመቻሉ የመነጨ ነው፡፡

ለመሆኑ ገፀባህሪያትን በሚገባ የምናውቀው በምን መነሻነት ነው?

………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………

የተለያየ ምላሽ እንደሰጠህ አምናለሁ፡፡ በርቱዕ የገፀባህሪ አሳሳል የተሳሉ ገፀባህሪያት ደራሲው ከሚነግረን ነገር ተነስተን ማንነታቸውን ልናውቅ እንችላለን፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩልህ ግን የተውኔት ገፀባህሪያት በአብዛኛው የሚሳሉት በኢ-ርቱእ ገፀባህሪያት አሳሳል መንገድ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የተሳሉትን ገፀባህራያት የምንረዳቸው ደግሞ (1) ገፀባህራያቱ ከሚናገሯቸው ንግግሮች (2) ሌሎች ገፀባህራያት ስለገፀባህሪያቱ ከሚናገሩት ንግግር እና (3) ገፀባህራያቱ ከሚፈጸሙት ድርጊት ተነስተን ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ጉዳዮች ተጣጥሞሽ የአንድን ገፀባህሪ ማንነት በሚገባ ልንረዳ እንችላለን፡፡ በሳል ፀሐፊ - ተውኔትም በነዚህ ሶስት የመለኪያ መስፈርቶች የገፀባህሪየቱን ማንነት ልንረዳ እንደምንችል ስለሚያውቅ ገፀባህሪያቱን ሲቀርጽ በጥንቃቄ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ የየገፀባህራያት በአግባቡ መቀረጽና አለመቀረጽ የተውኔቱን አወራረድ ሊያቃናም ሆነ ሊያዛንፍ ስለሚችል፣ አንድ ፀሐፊ ተውኔት ለገፀባህሪያቱ አቀራረጽ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል፡፡

ገፀባህሪያት እንዴት ተደርገው መቀረጽ አለባቸው?

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

………………………………………………………………………

……………………………………………………………………

ገፀባህሪያት በተለያየ መልኩ ሊቀረጹ እንደሚገቡ ለመግለጽ ሞከርክ? ብዙ የስነጽሁፍ ባለሙያዎች ገፀባህሪያት በሚቀረጽበት ወቅት ቢያንሰ ቀጣዮቹን ስድስት መስፈርቶች ሊያሟሉ እንደሚገባ ያምናሉ፡፡ ቀዳሚው መስፈርት ተአማኒነት ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ የሚሳሉ ገፀባህሪያት በተደራሲው ዘንድ ሊታመኑ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ ተደራሲው የሚያደርጉትን ድርጊት እና ንግግር ከእውነተኛው አለም ጋር እያነፀረ ሊቀበለው በሚችል መልኩ መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡ የተሳሉበትን ማዕረግ፣ ዕድሜ ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ማህበራዊ

እና ኢኮኖሚያዊ ቦታ ወዘተ… ሊወክሉ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡ መምህር እንደመምህር፣ ተማሪውም እንደተማሪ ተደርገው መሳል አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ በተውኔቱ ውስጥ ከተሰጣቸው ሚና አኳያ እና ከእውነት አለም አኳያ ሊያሳምን በሚችል መልኩ መቀረጽ ይኖርባቸዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ገፀባህሪያት ዘላቂነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ፀሐፊ ተውኔቱ የሰጣቸው ባህሪ በተቻለ መጠን ከተውኔቱ መጀመሪያ እስከመጨረሻው ሊዘልቅ ይገባል፡፡ ባህሪ ውጪያዊ ወይም ውስጣዊ ቢሆንም መጀመሪያ በተቀረፀበት መልኩ ባህሪያቸውን ይዘው መጓዝ አለባቸው፡ የሚከወኑት ድርጊት ፣ ንግግራቸው ፣ ለሌላው ያላቸው አተያይ በደመነፍስ የሚቀያየር መሆን የለበትም፡፡ ሆኖም እንደእውኑ አለም ገፀባህራያቱ በደረሰባቸው ድንገተኛ አደጋ ወይም በሌላ አሳማኝ ምክንያት ይዘውት የነበረውን ባህሪ ሊያጡ ቢችሉም፣ አሳማኝነት የሌለው መቀያየር ዘላቂነታቸውን ያከስመዋል፡፡

ኢ- ፍፁምነት ሌላው በገፀባህሪያት ቀረጻ ዘንድ ታሳቢ የሚደረግ ነጥብ ነው፡፡ በእውኑ አለም በሁሉም ነገር የተሳካለት እና እንከን አልባ የሆነ ሰው ያለመኖሩን ያህል የተውኔት ገፀባህሪያትም ፍፁም ተደርገው መሳል የለባቸውም፡፡ ሰው በባህሪው ደካማም ጠንካራም ፣ ቸርም ስስታምም፣ አፍቃሪም ጠይም ወዘተ ነው፡፡ ቢያንስ ሰው ለራሱ ፣ ለባለቤቱ ፣ለልጆቹ ለጐረቤቱ ፣ ለመስሪያ ቤት ባልደረባዎቹ ተመሳሳይ አይደለም፡፡ እንደሰብአዊ ፍጡርነታችንም ፍፁም ደግና ቸር (የአምላክ /የመላልክት ባህሪያትን እንዳለ የተላበስን) አይደለንም፡፡ የተውኔት ገፀባህሪያትም በእውኑ አለም እንዳለነው ሰዎቹ ታሳቢ ስለሚደረጉ መልአክ ወይም ሰይጣን ሆነው መቀረጽ አይገባቸውም (ይህን መንፈስ ተላብሰው እንዲሳሉ ካልተደረጉ በቀር)፡፡ ስለዚህም ሰው ሰው ይሸቱ ዘንድ ኢ-ፍፂም ሆነው መሳል ይጠበቅባቸዋል፡፡

በገፀባህሪያት አቀራረጽ ረገድ በአራተኛነት የምናነሳው ግለወጥነትን ነው፡፡ ግለወጥነት ስንል ገፀባህሪያቱ በራሳቸው መንገድ ራሳቸውን ሆነው እንዲኖሩ ሁኔታዎችን የምናመቻችበት መንገድ ነው፡፡ ገፀባህሪያት በፀሐፊ ተውኔቱ ከተፈጠሩ በኋላ ከደራሲው እና ከሌሎች ገፀባህራያት ባህሪና ፍላጐት ተለይተው ፣ ራሳቸውን የሚመስሉ ሆነው መቀረጽ አለባቸው፡፡ አንድ ገፀባህሪ ከሌላው የተለየ በሚሆንበት ጊዜ የገፀባህሪው አመለካከት ድርጊት እና ቋንቋ የተለየ ይሆናል፡፡ ይህም በታሪኩ ውስጥ ያለው ግጭት የሰመረ እንዲሆን ይረዳል፡፡ ብዙውን ጊዜ ገፀባህሪያት በድርጊታቸው በተለይ ደግሞ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ተመሳሳይ የሆኑ እንደሆኑ

የፀሃፊ ተውኔቱን ጣልቃ ገብነት ከማሳየቱም ባሻገር በጽህፈተ ተውኔቱ ውስጥ ግለወጥነት እንደማይታይ ማሳያ ሆኖም ሊታይ ይችላል፡፡ ስለሆነም ፀሐፊ ተውኔቱ በጸህፈተ ተውኔት ሂደትም ሆነ ከተጠናቀቀ በኋላ በሚደረግ እርማት ገፀባህራያቱ ራሳቸውን ችለው የቆሙና ግለወጥ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

ምክንያታዊነት በገፀባህሪያት አቀራረጽ ረገድ ሊተኮርበት  የሚገባ ሌላው ነጥብ ነው፡፡ ገፀባህራያት የሚያከናውኑት ድርጊትም ሆነ ንግግራቸው ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ በግድየለሽነት የተቀረፀ ሆኖ የገፀባህራያትቱን ተአማኒነት ማሳጣት አይገባውም፡፡ በተውኔቱ ውስጥ ለሚሆነው ነገር ሁሉ በተቻለ መጠን ምክንያቶች ሊኖሩና አንዱ ነገር ከሌላው ጋር ተያይዞ ታሪኩን ሊያራምድ ይገባል፡፡ በእርግጥም እንደ ወለፈንድ አይነት የተውኔት ዘውጐች ውስጥ የሚቀርቡ ቃለ ተውኔቶች በባህሪያቸው ምክንያታዊነት የሌላቸው ቢመስሉም ፀሃፊ ተወኔቱ ግን ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የቀረጻቸው ናቸው፡፡

ገፀባህሪያት የኖሩትን ጊዜና ዘመን ማንፀባረቃቸውን ማረጋገጥ፣ ገፀባህሪያትን በምንቀርጽበት ጊዜ ማሰብ ያለብን ተጨማሪው ነጥብ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ የተቀረፁ  ገፀባህሪያት ከመቼቱ ጋር ስሙም መሆን አለባቸው፡፡ ይህም የሚሆነው እንደኖሩበት ጊዜና ዘመን መናገር ፣ ማሰብና ፣ መኖር ሲችሉ ነው፡፡ የገፀባህሪያቱን ማንነት በሚገባ ለማድመቅ እና ተአማኒነታቸውን ከፍ ለማድረግ እንደዘመናቸው እንዲኖሩ ማድረግ አለብን፡፡ አንድ ፀሐፊ ተውኔትም የገፀባህሪው አጠቃላይ አኳሃን ይሄድበታል ተብሎ ከሚታሰበው ዘመን ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

## 3.3 ሴራ

ሴራ ምንድን ነው? በተውኔት ውስጥ ምን ሚና አለው?
........................................................................................................................
........................................................................................................................
........................................................................................................................
........................................................................................................................
........................................................................................................................
.................................................

ሴራ ከተውኔት አላባውያኖች አንዱ ነው፡፡ እንደ ፋንታሁን እንግዳ (       ) አገላለጽ

ሴራ “ ታሪኩን፣ ግጭትን፣ ምክንያትና ውጤትን ጭምር በውስጡ ይዞ የሚገኝ የተውኔት አላባ ነው” በፋንታሁን አገላለጸ ውስጥ ከሴራ ጋር ታሪክን እና ግጭት ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን፡፡ እነዚህ ሁለት ነጥቦች ደግሞ በልቦለድ ዘርፍ ራሳቸውን የቻሉ አላባውያን ስለሆኑ ከሴራ ጋር ያለባቸውን አንድነትና ልዩነት ማየቱ የተቃና ሀሳብ ለማግኘት ስለሚረዳ ከዚህ በታች ታሪክን መነሻ አድርገን እንመለከታቸዋለን፡፡

ሴራ ታሪክን ጭምር በውስጡ የያዘ አላባ ነው ሲባል ሴራና ታሪክ የሚተካኩ እና ተመሳሳይ አላባ ናቸው ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ተቀራራቢነት ያላቸው ከመሆኑ የተነሳ አንድን በሌላው የመተካት ችግር ስላለ ይህን ክፍተት ለመሙላት  በፀሃፊ ተውኔቱ  ጊዲሞስ አዘወትራ የምትባል ጥቅስ በሴራና በታሪክ መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት መምህራን በየጊዘው ይጠቀሙባታል፡፡ እናም እሷኑ ለማሳያነት እንጠቀም፡፡

ከላይ የጠቀስነው ባለሙያ “ ንጉስ ሞተ ፡፡ ከንጉስ ሞት በኋላም ንግስቲቱ ሞተች” የሚለው ሀሳብ ታሪክ ነው ይለናል፡፡ ምክንያቱም የሁነቶች ቅድመ ተከተል ከመጠቀሳቸው ውጪ ከአንደኛውና በሁለተኛው አረፍተነገር መካከል ምክንያታዊ የሆነ ግንኙነት የለም፡፡ የምናውቀው ከንጉሱ ሞት በኋላ ንግስቲቱ መሞትዋን ብቻ ነው ውጤትን የማይገልጽ የሁነቶች ቅድም ተከተል ታሪክ በመባል ይተወቃል፡፡

ሴራ ከታሪክ ጋር የሚመሳሰልበት እና የሚለያይበት ጉን አለው፡፡ ከታሪክ ጋር የሚያመሳስለው ብቸኛ ጉዳይ ሁነቶች ቅደም ተከተል መሰደራቸው ነው፡፡ ያልተዛባና ያልተበታተነ ተለጣጥቆ ያላቸው ሁነቶችን በቅድም ተከተሉ ሴራን ከታሪክ ብያመሳስለውም ፣ እነዚህ ሁነቶች በምክንያትና ውጤት መተሳሰራቸው ግን ታሪክና ሴራ እንዲለያዩ ያደርጋል፡፡ ቀደም ብለን የጠቀስነው የስነጽሑፍ ባለሙያ ታሪኩን ለማሳየት ያሰፈረውን የንጉስ እና የንግስቷን ሞት በሚከተለው መልኩ በመቀየር ሴራ ከታሪኩ የሚለይበትን መንገድ ቀለል አድርጐ ያሳየናል፡፡

| |
|---|
| ታሪክ - “ ንጉሱ ሞተ፡፡ ከንጉሱ ሞት በኋላ ንግስቲቱ ሞተች፡<br>ሴራ - “ ንጉስ ሞቱ፡፡ <u>በንጉሱ ሞት ሀዘን የተነሳ</u> ፣ ንግስቲቷ ታማ ሞተች፡፡” |

በሁለቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ስናጤን ከላይ እንደተገለፀው በሴራ ውስጥ ምክንያትና፣ ምክንያትን ተከትሎ ደግሞ የተከሰተ ውጤት ሲኖር ፣ በታሪኩ ውስጥ ግን የሁነቶች ቅድመ ተከተል ብቻ ነው ያለው፡፡

ሴራ ከታሪኩ ጋር ብቻ ሳይሆን ከግጭት ጋርም ቁርኝት አለው፡፡ ግጭት ራሱን የቻል አላባ ቢሆንም ሴራው የተዋቀረና የተስተካከለ ይሆን ዘንድ ሚና ስላለው ሴራን በማጉልበት ደረጃ የሴራ አካል አድርገን እንወስደዋለን፡፡ እንደሚታወቀው በተውኔት ውስጥ የተሳሉ ገፀባህሪያት ወደ ግጭት ይገባሉ፡፡ ከግጭቱ ለመውጣት በሚያደርጉት ጥረትም ከአንድ ሁነት ወደሌላ ሁነት ምክንያት ላይ በተመሰረተ መልኩ ሽግግር ያደርጋሉ፡፡ እየተፈጸመ ያለው ታሪክም ምክንያታዊ በሆነ መልኩ እየተቀጣጠለ ይጓዛል፡፡ ይህ ሂደት ከላይ እንዳነሳነው የታሪክን የምክንያትና ውጤት ትስስር ስለሚያሳይ ሴራ ይፈጠራል፡፡

በአጠቃላይ ፍንታሁን እንግዳ (1992) እንደሚሉት “ በድርጊቶች መካከል ያለ የቅድመ ተከተል ቁርኝት ፣ የቁርኝቶች ተአማኒነት እና የሚያስከትሉት ውጤት ፣ የውጤታቸው ምክንያት ተገቢነት እና ይሁንታን ሴራ እንለዋለን”

የሴራ ምንነትን ይህን ያህል ካየን የምንቀጥለው ወደሴራ አይነቶች ነው፡፡

| |
|---|
| የሴራ አይነቶች ምን ያህል ናቸው? እስቲ ከዚህ በታች በሰፈረው ቦታ ላይ<br>አይነቶቹን ዘርዝርልኝ፡፡<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-----------------------------------------------------------------------------------------------------<br>---------------------------------------------------------------------------------------------------- |

የተለያዩ ዝርዝሮች እንዳስቀመጥክ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በዝርዝሮችህ ውስጥ ከሚከተሉት አራት ነጥቦች ቢያንስ ሁለቱ ሊኖሩ እንደሚችሉም እገምታለሁ፡፡ አይነቶቹን ላስፍርልህ፡፡

ሀ. ልቅ ሴራ

ለ. ጥብቅ ሴራ

ሐ. ነጠላ ሴራ

መ. ጥምር ሴራ

እነዚህ አራቱ አይነቶች በተናጠል ራሳቸውን ችለው ቢቆሙም በጥምርት ልናያቸው የሚገባበትም ሁኔታ አለ፡፡ ካላቸው ባህሪ የተነሳ ልቅ እና ጥብቅ ሴራዎች በአንድ ወገን፣ ነጠላና ጥምር ሴራዎች ደግሞ በሌላ ወገን ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ተውኔቶቹም ልቅ ወይም ጥብቅ ሴራ ይዘው ሊዋቀሩ ፤ በአወቃቀራቸውም ነጠላ ወይም ጥምር ሴራን የመያዝ ባህሪያት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ አልፎ አልፎ ከአራቱ ወጣ ባለ መልኩ ሴራ አልባ ተውኔቶችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በአብዛኛዉ የሚያጋጥሙን ተውኔቶች ከላይ ከተጠቀሱት አራት የሴራ አይቶች ውስጥ የተወሰኑትን ስለሚይዙ ከጥምር የጋራ ባህሪያቸው ተነስተን አራቱን የሴራ አይነቶች ለመተንተን እንሞክራለን፡፡

### 3.1.1 ልቅ እና ጥብቅሴራ

| |
|---|
| ልቅ እና ጥብቅ ሴራ ማለት ምን ማለት ነው<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-------------<br>በልቅ እና በጥብቅ ሴራ መካከል ምን አይነት ልዩነቶች አሉ?<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>-------------------------------------------------------------------------------------- |

ልቅ እና ጥብቅ ሴራዎች በአንድ ተውኔት ውስጥ የታሪኩ ምክንያትና ውጤት ደምቆ ከመታየቱ አኳያ የሚያጋጥመውን የሴራ መዋቅር የሚያመለክቱ የሴራ አይነቶች ናቸው፡፡

ልቅ ሴራ የሚባለው በብዛት በቧልታይ የተውኔት አይነት የተለመደ የሴራ አይነት ነው፡፡ በዚህ የሴራ አይነት በተዋቀረ ተውኔት ገፀባህሪያቱ የሚናገሩት ፣ የሚያደርጉት እና ሌላው ስለነሱ የሚናገረው የተአማኒነት ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ገፀባህሪያቱም በርከት ብለው ስለሚቀርቡ አሳማኝ በሆነ ሁኔታ እያንዳንዳቸውን ለመሳል አያመችም፡፡ አብዛኛውን ጊዜም በታሪኩ ውስጥ እነዚሁ በርካታ እና የዋናውን ገፀባህሪ ቦታ ሊይዙ የማይችሉ ገፀባህሪያት ጐልተው ስለሚወጡ የታሪኩ ምክንያታዊ ተያያዥነት የላላ ይሆናል፡፡ ሀሳቦች ይበታተናሉ፡ ወደ ማእከላዊ የታሪኩ ጭብጥ የሚያመሩ መንገዶችም ዝግ ይሆናሉ፡፡ እናም የታሪኩ አንድነት እና ትስስር የጠበቀ አይሆንም፡፡ ይህም ሴራውን ልቅ ያሰኘዋል፡፡

ልቅ ሴራ ጠንካራ የምክንያትና ውጤት ጣጣ የሌለበት የሴራ አይነት ነው፡፡ አንድ ነገር የተከሰተው በዚህ ምክንያት ነው ብለን እንዳናምን የሚያደርጉ በርካታ ነገሮችንም በውስጡ ይይዛል፡፡ ልቅ ሴራ ባለበት ተውኔት በተውኔቱ ውስጥ ያሉ ታሪኮች ብዙውን ጊዜ የተሳሰሩ አይሆኑም፡፡ ምናልባት እያንዳንዱ የተውኔቱ ንኡሳን ታሪኮች የመተሳሰር አጋጣሚ ቢኖራቸው እንኳን ትስስራቸው ልል ነው፡፡ አንባቢን /ተመልካቹን የሚያሳምንም አይሆንም፡፡

ልቅ ሴራ ያለው ተውኔት በመድረክ የቀረበ እንደሆነ ፈጣን የሆነ የትዕይንት ለውጥን እናስተውልበታለን፡፡ እያንዳንዱ ንኡስ ታሪክ የተፈፀመበት ቦታ እና ጊዜ በጣም የተለያየ ይሆናል፡፡ ወይም ጥቂት ቦታ ላይ የተፈጸመ ከሆነ ደግሞ በፍጥነት እየተቀያየረ የሚቀርብበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ይህም ታሪኩ እየተቆራረጠና አንዱ ከአንዱ ትዕይንት ሳይተሳሰር እንዲያልፍ ያደርገዋል፡፡ በአጠቃላይ ልቅ ሴራ በተውኔቱ ታሪክ ውስጥ ያሉ ትስስሮች በጠንካራ ምክንያት ላይ የተገነቡበት ፣ የታሪኮቹ ትስስር እጅጉን ልል የነበረ፣ በዚህም ምክንያት የታሪኩ ማብቂያ (የሚደረስበት ውጤት) አሳማኝ የማይሆንበት የሴራ አይነት ነው፡፡

ጥብቅ ሴራ ተቃራኒ ባህሪ ያለው የሴራ አይነት ነው፡፡ ይህ የሴራ አይነት በአሳማኝ የታሪክ ቁርኝት አሳማኝ የታሪክ ማብቂያን (ውጤትን) የምናይበት ነው፡፡ በዚህ የሴራ አይነት አንዱ ንኡስ ታሪክ ከሌሎቹ ንኡሳን ታሪኮች ጋር በጥብቅ የምክንያትና ውጤት ትስስሮሽ የተገመደ ነው፡፡ እያንዳንዱ ታሪክ ከሌሎች ታሪኮች ጋር በጥብቅ የሚተሳሰርበት መንገድ አለው፡፡ ያልተቆራኙ እና ብቻቸውን የተተዉ ንኡሳን ታሪኮች አናይበትም፡፡ ምክንያቱም በዚህ የሴራ አይነት በተዋቀረ ተውኔት ውስጥ እያንዳንዱ ታሪክ ከሌላው ጋር ተገምዶ አንድ ውጤትን ለማሳየት ይሞከርበታል፡፡

በጥብቅ ሴራ ወስጥ የሚገኙ ገፀባህሪያት በልቅ ሴራ እንደተዋቀረ ተውኔት ብዙ አይደሉም፡፡ እያንዳንዱ ገፀባህሪ የሚተገበረው አንዳች ነገር ስላለው ብቻ ነው በተውኔቱ ውስጥ የሚካተተው ስለሆነም ገፀባህሪው በተውኔቱ ውስጥ ባይኖር ክፍተት ከተፈጠረ ብቻ ነው የተውኔቱ አካል የሚሆነው፡፡ ያሉት ገፀባህሪያትም የሚፈጽሟቸው ተግባራት ሁሉ ለዋናው የታሪኩ ውጤት ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ ተአማኒነት ያላቸውን ገፀባህሪያት በበርካታው የምናገኘውም በዚህ የሴራ አይነት በተዋቀረ ተውኔት ውስጥ ነው፡፡

በዚህ የሴራ አይነት ተበዋቀረ ተውኔት የትዕይንት ለውጦች ፈጣን አይደሉም፡፡ በጣም የተደጋገመ የጊዜና የቦታ ለውጥ ብዙ ጊዜ አይታይም፡፡ ይህ ሆኖም ከተገኘ የታሪኩ ሁኔታ ሲያስገድድና ለታሪኩ አካሄድ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ የሚፈጸም ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ጥብቅ ሴራ በአሳማኝ የምክንያትና ውጤት ትስስር የተዋቀረና ተደራሲውን የማሳመን ብቃት ያለው የሴራ አይነት ነው፡፡

### 3.1.2 ነጠላ እና ድምር ሴራ

| |
|---|
| ነጠላ እና ድምር ሴራ ምን ማለት ነው?<br>----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>በነጠላ እና ድምር ሴራ መካከል ምን ልዩነቶች አሉ?<br>----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>----------------------------------------------------------------------------------------------------------------<br>---------------------------------------------------------------------------------------------------------------- |

ሴራ ነጠላ እና ድምር ተብሎ ለሁለት የሚከፈለው በውስጡ ከተካተቱ ታሪኮች የነጠላነት እና የብዙነት ባሀሪ በመነሳት ነው፡፡ ነጠላ ሴራ የሚባለው ስሙ እንደሚያመለክተው የተውኔት ታሪኮቹ በአንድ ውስን ጉዳይ ላይ ብቻ የሚያጠነጥኑ ሆነው ሲገኙ ነው፡፡ በተውኔቱ ውስጥ የሚደረጉ ማናቸውም አይነት እንቅስቃሴዎች ትኩረታቸው በታሪኩ ነጠላ ጉዳይ ላይ ብቻ ሲሆን፣ ገፀባህሪያቱ በታሪኩ ውስጥ ያላቸው ስፍራና፣ ስፍራቸውን ተከትለው የሚያደርጉት ጉዞ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ሲሆን ሴራው የነጠላ ሴራነት ባህሪ ይላበሳል፡፡

| |
|---|
| ቀደም ሲል ካየናቸው ልቅ ሴራና ጥብቅ ሴራ ውስጥ ለነጠላ ሴራ የሚቀርበው የትኛው የሴራ አይነት ነው?ለምን ?<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>------------------------------------------------------------------------------------------------<br>---------------------- |

ለጥያቄው ጥብቅ ሴራ ነው ብለህ ምላሽ በመስጠት ምክንያትህን በአግባቡ የደረደርህ ይመስለኛል፡ ትክክል ነህ፡፡ ብዙውን ጊዜ አንድ ሴራ ነጠላ የመሆን ባህሪ በኖረው ቁጥር ልቅ ከመሆን ይልቅ ጥብቅ ሴራ የመሆን እድሉ ከፍ ይላል፡፡ ደበበ (1973፣23) እንደሚለው "ይህ አይነቱ ሤራ (ነጠላ ሴራ) በተደራቢ አንዳንዴ ልቅ፣ ብዙ ጊዜ ግን ጥብቅ ሴራ ሊሆን ይችላል፡፡ ዋናው ነገር በተውኔቱ ዉስጥ የሚከናወኑት ታሪኮችና ድርጊቶች ስለአንድ የተወሰነ ነገር ወይም ሁኔታ መሆን አለባቸው፡፡"

ድምር ሴራ የነጠላ ሴራ ተቃራኒ ነው፡፡ ይህ የሴራ አይነት በባህሪው ከአንድ የበለጡ ሴራዎችን በውስጡ አቅፎ ይይዛል፡፡ በተውኔቱ ውስጥ አንድ አብይ ሁሌም ልናተኩርበት የሚገባና ታሪኩን በሚገባ የሚይዝልን ሴራ ይኖርና ይህንን አብይ ሴራ ፈር የሚያስይዝልን፣ የሚያጐለብቱልን ሌሎች ሴራዎች ሲኖሩ ተውኔቱን ባለ ድምር ሴራ ልንለው እንችላለን፡፡ ደበበ (1973፡24) ይህንን የሴራ አይነት በሚከተለው መልኩ ይገልፀዋል፡፡

> ይህ አይነቱ ሴራ በተደራቢ አንዳንዴ ጥብቅ ብዙ ጊዜ ግን ልቅ ሲሆን ይችላል፡፡ ይህ ሴራ ስሙ እንሚያመለክተው ሁለት ሴራዎችን ይይዛል አንድ አቢይ ሴራ ሌላ ንኡስ ሴራ አቢዩም ሆነ ንኡስ ሴራው በውስጣቸው ብዙ ታሪኮች ይኖራቸዋል፡፡ ንኡስ ሴራው ከአቢይ ሴራው ጋር ቁርኝነት አለው- አንድነት፡፡ የጠበቀ ግን አይደለም-የከረረ፡፡ አቢይ ሴራው በንኡስ ሴራው የሚደምቅበት ጊዜ አለ-የሚጐላበትም፡፡ የሚወደድርበትም ጊዜ አለ፤ የሚነጻጸርበት፡፡

ከላይ እንደ ተጠቀሰው ድምር ሴራዎች ባላቸው ተወኔቶች ውስጥ ያሉ አብይና ንኡስ ሴራዎች ትስስር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የትስስራቸው መጠን መላላትና መጥበቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሳሰሩ መሆናቸው ግን መዘንጋንት የለበትም፡፡ ይህም በመሆኑ ግንኙነት የሌላቸ ሴራዎች ተሰባስበው አንድ ተውኔት ሊፈጥሩ አይችሉም፡፡ በዚህ መልክ የተቀረፀ ተውኔትቶች በአንድ የአጭር ልብወለድ መድብል ውስጥ እንዳሉ የተለያዩ

ታሪኮች ብቻ ነው ልናያቸው የምንችለው፡፡ ተውኔቱን ወጥ እና አንድ ተውኔት ከሆነ የግድ አብይና ንኡስ ሴራዎቹ የተሳሰሩ መሆን እንዳለባቸው መረዳት ይገባል፡፡

ከላይ በሁለት ንኡሰ ክፍሎች ካየናቸው ልቅ ሴራ ጥብቅ ሴራ፣ ነጠላ ሴራ እና ድርም ሴራ ውጭ ሴራ አልባ የሆኑ ተውኔቶችም አሉ፡፡ ደበበ (1973) እና ፋንታሁን(1997) እንደሚጠቅሱትም የዚህ አይነት ሴራ አልባ ተውኔቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ከሚሆኑ ጉዳዩች አንደ ፀሐፊ ተውኔቶች የሚከተሉት የተፈጥአዊነት የአጻጻፍ ስልት ነው፡፡ ከላይ ከጠቀስናቸው የተውኔት ባለሙያዎች አንደ ፍንታሁን (1993፡78) እንደሚገልፁት ‹‹በተፈጥሯዊነት የአጻጻፍ ስልት ህይወት እንዳለ ተገልብጦ መቅረብ አለበት እንጂ ተመርጦና እንዲሁም ተጊጦ መቅረብ አይኖርበትም፡፡ ተውኔታዊ ሴራዉን በተመለከተም የጠበቀ መልኩ እንዲዋቀር አያስፈልገም፡››

የሴራ አልባ ተውኔት ተመልካቶችም የህይወት አንኳር ክፍሎች ተመርጠውና ተለይተው ስለማይቀርቡላቸዉ ፣ ትኩረት ነጥቡም የሚያሰፋርበት ቦታ ባለመኖራቸው ስለተወኔቱ ምንነት ጥያቄ ቢቀርብላቸው ምንም ምላሽ ሊሰጡ አይችሉም፡፡ ተውኔቱን ተመርኩዘው ሊገልጹ የሚችሉት ነገር ቢኖር ስለሌሎች አላባውያን ወይም መዋቅራዊ ጉዳይ ብቻ ሲሆን ይችላል (ደበበ፣1973)፡፡

## 4. ቃለተውኔት

ቃለተውኔት በአራተኛ ደረጀ የምናሳየው የተውኔት አላባ ነው፡፡ ቃለ ተውኔት ውስጥ ጉልህ ቦታ ያለው አላባ ከመሆኑ ባሻገር ከሌሎች የነጽሑፍ ዘውጐች ተውኒትን የምለይበት ነው፡፡

ቃለተውኔት ምንድን ነው?
________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________

ቃለ ተውኔት ስለምን የተውኔት አላባ ሆነ?

________________________________________________________
________________________________________________________
________________________________________________________

ቃለተውኔት በተወኔት ውስጥ ካሉት የቋንቋ አጠቃቅሞች አንደኛውና ዋነኛዋው እንደሆነ እንደገለጽክ ይሰማኛል፡፡ ትክክል ነኝ? በተውኔት ውስጥ በዋነኛነት ሁለት አይነት የቋንቋ አጠቃቀሞች አሉ አንደኛው ቃለተውኔት ሲሆን ሁለተኛው የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ቋንቋ ነው፡፡ በቅድሚያ ስለመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ጥቂት ብለን ወደ ስለ ቃለ ተውኔት እናነሳለን፡፡

የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ የፀሐፊ ተውኔቱ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት ፣ ተውኔት ሲመደረክ መቼቱን ባገናዘበ ሁኔታ ገፀባህርያቱ የሚያደርጉትን ሁኔታ የሚጠቁም፣ ከዛ በዘለለ ስለገፀባህርያቱ የተገን ባህሪያቱ አካባቢያዎ ሁኔታ ጥቁምታየሚሰጥበት ቋንቋ ነው፡፡ በዚህ የቋንቋ አጠቃቀም ፀሐፊ ተውኔቱ የራሱን የቋንቋ አጠቃቀም ሊያሳይ ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜም ይህ ጽሑፍ በተውኔቱ ጅማሬ ላይ ፣ ከዚህም በዘለለ

በቃለተውኔቱ መጀመሪያ፣ መካከል ወይም መጨረሻ ላይ የገፀ ባህሪያቱ እንቅስቃሴና ሌሎች ሁኔታዎች ለማሣየት በቅንፍ ሊቀመጥ ይችላል፡፡ ከዚህም ውጪ በተውኔቱ ውስጥ የምናገኛቸውን የቋንቋ አጠቃቀሞች ቃለ ተውኔት እንላቸዋለን፡፡

ቀጣዩ የተውኔት ቅንጫቢ የተወሰደው ከፋንታሁን እንግዳ **ሽርገጤ** ተውኔት ነው፡፡ ከተውኔት ቅንጫቢው ውስጥ የትኛው ቃለተውኔት የትኛውስ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ እንደሆነ እንመልከት፡፡

ሽርገጤ፡- እንዲህ የከፋ ንዴት ሲገጥመኝ ፣ ጥቃት ሲገባኝ ፣ ከጭንቅላቴ ወደ አንገቴ የሚመለሰው ደም እንደ ቧንቧ ውሃ እየተንዠቀዠቀ ሲወርድ የሚሰማኝ ይመስለኛል፡፡ ይኼኔ ታዲያ አይኔን ካሰፈጠጠኝ አይመለስም፡፡ ‹‹ፍም እስኪመስል የጋለን ቢላዋ ከሚንቀለቀል እሳት አውጥተህ ንከስ ንከስ›› ያሰኛል ወይም ‹‹ካርታ ሙሉ የጐረሰ መትረስ አንስተህ እንደ ውሃ ጥም ባንድ ትንፋሽ ሽምጥጥ አድገህ ጠጥተህ ክርትም›› በል ይለኛል፡፡ ሰው መደብደብ ከጀመርኩ ደግሞ እንደ ስጋ መትሬ መትሬ ካለቀኩት አርካታ አላገኝም፡፡ (ከአቻምየለሽ ላይ አፋጥጠው) ተናገሪ ያለፈው ቅዳሜ ከምሣ በኂላ ጉለሌ ሆቴል የገባሽው ከማን ጋር ነበር?… መቸም አያዩብኝም ወይም አይሰሙብኝም በሚል ፊሊጥ ልስሽ ተሸፍኖ ነው ወይም በስህተት የተደረገ አስቀያማ ድርጊት? /መልስ ባለማግ ኘታቸው ደጋግመው ይሸነቁጧታል፡፡/ ዛሬ ምድር ከፍ ሰማይ ዝቅ ብለው በገናኙ እውነቱን ሳትናገሪ አለቅሽም!!…

እርካብሽ - /ከንዳ የሻይ ጀበናና ብርጭቆዎች ይዛ ትገባለች/ ኸረ እባክዎን እርስዎ ሰውዬ በጧት አይበሳጩ፡ ልጅቱንም አያስቀይሞዋት፡፡

ሽርግጤ - /በሚያምባርቅ ጽምጽ /በልጄ ጉዳይ ጣልቃ እንዲተገቢብኝ የምፈቅድልሽ እንዳይመስልሽ!

እርከብሽ- እባክዎትን በስመአብ ይበሉና፣ ዳቦም ይቁረሱ ፣ ሻሂም ይቅመሱ፡

ሽርግጤ - የለም በቃኝ እግዜሐብር ይስጥልኝ፡፡ ዛሬ የጧት ቁርሴን የምቋደሰው የገዛ ልጄን በመግረፍ ነው፡፡ /ወገቧን ይዛ በመገረም ስታሰተውላቸው አይተው ይገላምጧትና/ በይ ያመጣሽውን መልስሽ ያኸና ዘወር በይልኝ፡…

ከተውኔት ቅንጫቢው ውስጥ የቱ ቃለተውኔተ የትኛው ደግሞ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ እንደሆነ ጠቆም? ጥሩ ነው፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጡት ብቻ በቅንጫቢው ውስጥ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ተደርገው ሲወሰዱ፣ ሌሎቹ ግን ቃለተውኔቶች ናቸው፡፡

በቅንጫቢው የተጠቀሱ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫዎች

- ከአቻምየለሽ ላይ አፍጥጠው
- መልስ ባለማግኘታቸው ደጋግመው ይሸነቁጧል
- ከንዳ የሻይ ጀበናና ብርጭቆ ይዛ ትገባለች
- በሚያምባርቅ ጽምጽ
- ወገቧን ይዛ በመገረመ ስታስተውላቸው አይተው ይገላምጧትና

ከላይ እንደተመለከትናቸው የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫወች ብዙውን ጊዜ በቅንፍ ውስጥ የሚቀመጡ ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ደግሞ የጽሑፍ አይነቱ ከቃለተውኔቱ በተለየ የጽሑፍ አይነት እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫዎች የገንባህሪያውን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከመግለጽ ባሻገር ‹‹ ጊዜ ቦታ፣ ድርጊት፣ እንስቅቃሴ፣ መውጣትና መግባት፣ ግባተ ፣ ድምጽና የመድረክ ቁሳቁስ ፣ አልባሳት፣ አካላዊ አቋም፣ ስነፍጥረታዊ ሁኔታን፣ ውስጣዊ አስተሳሰብን›› የመናለት አለማ አላቸው፡፡ በዚህም አላማቸው አንድ ተውኔቱ ሲመደረክ ተሳታፊ የሚሆኑ አባላተ በሙሉ ተውኔቱን በእነዴት ባለ ሁኔታእንደሚያዘጋጁ እንደሚተውኑትና መቼቱን እንደሚፈጥሩ መነሻ ይሰጣቸዋል፡፡ የመድረክ እንቅስቅሴ መግለጫው በተገቢ መልኩ የስፈረበት ተውኔትን ለመመድረክም ያን ያህል አስቸጋሪ የማይሆነው ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ነው፡፡

ቃለተውኔት በአንድ ተውኔት ውስጥ የተሳሉ ገፀባህርያት ከአንደበታቸው አፍልቀው የሚናገሩት ምልልስ ነው፡፡ የተውኔቱ አለም ሰዎች ወይም ሰው አከል አካላት በዝርው፣ በግጥም ወይም በግጥምና በዝርዉ የሚያደርጉት ንግግር ቃለተውኔት ይባላል፡፡ ምንም እንኳ በዚህ ዘመን የሚቀርቡ ተውኔቶች በዝርው የመቅረብ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ቃለተውኔቱ  ዝርው በሆነ መልኩ /ቀደም ሲል እንዳየናው ቅንጫቢ/ የሚቀርብ ቢሆንም ቀደም ባሉ ዘመናት የሚቀርቡ ተውኔቶች ላይ ግን ግጥማዊ ምልልሶችን እናስተውላለን፡፡ የሚከተለው ከ ከበደ ሚካኤል /1957፣42/ የትንቢት ቀጠሮ የተወሰደ የተውኔት ቅንጫቢ ለግጥማዊ ቃለተውኔት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡

ንጉስ
ትንቢቱን ሲናገር አፍ አንደበቱ
የገነነ ነበር ኃይለኛና ብርቱ፡፡
ወታደር
እንዲህ መለፍለፉ አፍን እንዲህ ከፍቶ
ምናልባት እንዳይሆን ምንምን ጠጥቶ
ንጉስ
ስካርስ አይደለም አፍ ያስታውቃል
እያዳር ሲያስቡት ይህ ነገር ይደንቃል
ወታደር
ከየት እንዳመጣው ይህንን ፈጠራ

ሊጠይቅ ይገባል በህግ ምርመራ
ንጉስ
ይህንን መመርመር ሞኝነት ነው ከንቱ
በኮከብ ብራና ተጽፏል ማለቱ
ለዚህ አይደለም ወይ? ሐሰት  የማለ ሰው
ይገባል ጥበቡን አውቆ  ሲመለሰው
ወታደር
የትንቢቱ ነገር ቢሆንም የከፋ
ውሸት ነው እላለሁ የዚህ ሰው ልፍለፋ

ቃለ ተውኔት የአንድ ተውኔት አንኳር ነጥብና የሌሎች ተውኔት አላባውያንም መገለጫ በመሆኑ ሲጻፍ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች /ደበብ፣ ፋንታሁን፣ 999፣ ብሩክ፣/ ቃለተውኔት ቀጣዮቹን ባህሪያት የተላበሰ ሊሆን እንደሚገባ ሀሳብ ያቀርባሉ ፡፡

1. **ቁጥብነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡**

ተወኔት በባህሪ ከግጥም ጋር የሚመሳሰልበት ባህሪ አለው፡፡ ይህም ቁጥብነት ነው፡፡ በአንድ ተውኔት ውስጥ የሚጻፍ ቃለተውኔት በጥቂት ቃለት ብዙ የመግለጽ አቅም ሊኖረው ይገባል፡፡ ለዚህም የተንዛዛ የቋንቋ አጠቃቀምን መጠቀም፣ አላስፈላጊ ሀሳቦችን ማጨቅ የለብንም፡፡ ተውኔት በጥቂት ጊዜ ብዙ የሚባልበት ጥበብ ስለሆነ ባይገለጽ የማያጉድል ሀሣብ ብቻ ይቀርብበታል፡፡

2. **ግልጽነት ሊኖረው ይገባል**

ግልጽነት የሌለው ሀሳብ እንዳልተጠቀሰ ሀሳብ ይቆጠራል፡፡ ለዚህ ደግሞ የቃለተውኔቱ ግልጽና ቀላል መሆን ይኖርበታል፡፡ አብዛኛው የተውኔቱ አንባቢ ወይም ሲመደረክ የሚያይ ተመልካች ሊረዳው በሚችል መልኩ ቃለተውኔቱ መቅረብ መቻል አለበት፡፡ ደበበ/1973፡4/ እንደሚለው መልኩ ‹‹ተደራሲያኑ ከባድና ጥልፍልፍ ያለ ቃለ ተውኔቶችን ሲሰሙ ገፀባህሪይውን /ተዋናዩን/ እስቲ አንደ ጊዜ ቆይ አሁን ያልከው አልገባኝ ሊሉት አይችሉም፡፡ ይህን የቲያትር ዘልማድ አይፈቅደውም በፍጹም፡፡... ስለዚህም ተውኔቱ ከተደራሲው የራቀ ይሆንና ፀሐፊ ተውኔቱ ራሱ ከራሱ ጋር ብቻ የሚነጋገርበት ሆኖ ያልፋል፡፡ ስለሆነም ተውኔቱ በወጉ ለተደራስያን እንዲደርስ የግድ ግልጽነት ሲኖረው ይገባል፡፡

> ከዚህ በታች የሰፈረው የተውኔት ቅንጣቤ ፀጋዬ ገብረ መድህን (1977፣79-80) ከተረጐመው ሀምሌት ተውኔት የተቀነጨበ ነው፡፡ ምልልሱን አንብበህ ምንም እንኳን ቅንጫቢ ተውኔት ቢሆንም ግልጽ ስለመሆኑ እና አለመሆኑ ሀሳብህን በማስረጀ አስደግፈህ አቅርብ

ሃምሌት
ለምንድነው ያሰፈለግሺኝ፣ እናት አለም? ይኸው መጣሁ፡፡
ንግስት
እቅጩን ልንገርህ ሃምሌት፣ አባትክን በድለኸዋል፡
ሃምሌት
እቅጩን ልንገርሽ አነቺም፣ አባቴን በድለሽዋል፡
ንግስት
ይህንኑ እኮ ነው የምልህ ፣ ምንድ ነው ይኸ አጉል መልስ?
ሃምሌት
ይህንኑ እኮ ነው የምልሽ ፡ምንድ ነው ይኸ አጉል ጥያቄ?
ንግስት
እንዴት ሃምሌት? እንዴት?

ሃምሌት
የምን እንዴት እንዴት ነው እሱ፡
ንግስት
እናትህ እኮ ነኝ እኔ ፡ ፡ እናትክ? ረሳሽኝ እንዴ/
ሃምሌት
እንዴት አባቴን አርጌ? ምን ባረግ ነወ እምረሳሽ? ንግስቲቱ  አይደለሽ እንዴ? ምን ቆርጦኝ ነው ምረሳሽ?
ንግስት
… አይ ተወው እንግዲያስ ተወው፡፡ ክነኝያው የሚያፋጡህ ይምሰልህና ያስወተወተህ… /ትነሣለች/
ሃምሌት
ነይ ፡ ፀጥ ብለሽ ተቀመጭ ፡፡ ከዚህ ውልፍጥ እንደትይ ጉዳሽ በመስተዋት እፈትሽ ፣ አፋጥጨሽ እስከታጡ፡
ንግስት
እኮ ምን ልትሆን?… ግደለኝ ፣ ግደለኝ  ኧረ፡
ጳሎኔዎስ
ኧረ ጉበዝ ኡ፡ኡ፡ኡ በሉ፣… ያገር ያለህ /ኡ/ኡ
ሃምሌት
… ውሻ ? ልክስክስ ውሻ አስረሻል፣ ውሻ ?ልክስክስ አልወድም፡
-ጳሎኔዎስን መጋረጀ ውስጥ ይወጋዋል
ንግስት
… ምንድ ነው እሱ ያረከው፡
ሃምሌት
አንቺ ንገሪኝ ምንድ ነው? ንጉስ ነው?
ንግስት
ኧረ ምንድ ነው ያረከው (የምን ጥድፊያ) የምን ሃጢያት፡
ሃምሌት
መቼም አይብስ ካንቺ ኃጢአት
ባል ገድሎ ወንድሙን ከማግባት፡

**3 በተቻለ መጠን አረፈተነገሮች አጫጭር መሆን አለባቸው**

በተውኔት ውስጥ ያለን ቃለ ተውኔት ተመልካች በቀላሉ ሊረዳው የሚችል መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አኳያ በተቻለ መጠን አረፍተነገሮቹ አጫጭር መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን ተዋናዩም በቀላሉ ሊያስተውሳቸውና በቀላሉ ሊናገራቸው ተደራሲውም ባለሰለቸ ስሜት ሊከታተላቸው ይችላል፡፡ የተውኔቱን ድርጊት በማፍጠን ረገድም አስዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡

በቃለተውኔት ውስጥ ያሉ አረፍተ ነገሮች በረዘሙ ቁጥር ቀድሞ የተጠቀሱ ሀሳቦች እየተዘነጉ ይመጣሉ፡፡ ጭብጦች ይረሳሉ፡፡ (የማይገባ ቢሆንም) ብቅ እያለ ገፀባህሪቱን ከባህሪያቸው የማውጣት እድሉ እየሰፋ

ይመጣል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተውኔቱ ደካማ እየሆነ ይመጣል፡፡ ስለሆነም በቃለተውኔት ውስጥ ያሉ አረፍተነገሮች አጫጭር እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**4 ከገፀ ባህሪያቱ ስብዕና ጋር የሚዋሀድ የቋንቋ አጠቃቀም ሊኖረው ይገባል**

ቃለተውኔት ገፀባህሪያቱ ከፀሐፊ ተውኔቱ የቋንቋ አጠቃቀም ተላቀው ራሳቸውን የሚገልፁበት ነው፡፡ እንደገፀባሪያቱ ስብዕና የቋንቋ አጠቃቀማቸውም የተለያ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

በእውኑ አለም ህጻንና ሽማግሌ ተመሳሳይ የቋንቋ አጠቃቀም እንደማይኖራቸው ሁሉ በተውኔት ውስጥም የተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ገበሬና ወታደር ምሁርና ያልተማረ፣ ሀኪምና ኢንጅነር፣ ከተማና ገጠሬ፣ ጨካኝና ሩህሩህ፣ ሞኝና ብልጥ.. የቋንቋ አጠቃቀማቸው የተለያየ እንደመሆኑ መጠን በተውኔት ውስጥ ያሉ ገፀባህሪያት ሁሉ ተመሣሣይ አይደሉምና የተለየ ንግግር እንዲናገሩ ያስፈልጋል፡፡ ፀሐፊው ተውኔቱም በተቻለ መጠን የሱን የቋንቋ አጠቃቀም ገፀባህሪያቱ ላይ መጣል የለበትም፡፡ እንደገፀ ባህሪያቱ ባህሪ እና ማንነት ሁሉም የየራሱ የቋንቋ አጠቃቀም በቃለተውኔቱ ላይ እንዲያንፀባርቅ ፀሐፊ ተውኔቱ በእጅጉ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ይህ ከጌትነት እንየው (200፣ 46-47) እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ተውኔት የተወሰደ የተውኔት ቅንጫቢ ከገፀባሪያቱ ስብዕና ጋር የተዋሀደ የቋንቋ አጠቃቀም አለው አንዴት? የተውኔት ቅንጫቢውን ካነበብህ በኃላ አስረዳ፡፡ ሳሊምቢኒ የተኘው ገፀባህሪ ጣልያናዊ መሆኑን ጠቆመ ላደርግህ እወዳለሁ፡፡

ሳሊምቢኒ- ኦ… ፈትልወርክ
ፈትሉ- (በፈገልታ እያየችው) አቤት ሲኞር ሳሊምቢኒ
ሳሊምቢኒ- ይሄ ብቻ ተታው ባክሽ
ፈትሉ- ኸረ እኔ ይቅርብኝ (በመሽኮርመም አየት አርጋው ትስቃለች) እስክራለሁ እባክዎ
ሳሊምቢኒ- ስከረው በካ (አገጯን ያዝ እያደረገ) ኖ ኘሮብሌም፣ ሽግር የለም ፈትልወርክ፡፡ ሲ?
ተኮላ- በቅናት ስሜት) የለም፣ ይበቃታል ሲኞር ሳሊምቢኒ
ሳሊምቢኒ - አቶ ተኮላ፣ አንተ ለምን ሁልጊዜ፣ ፈትልወርክ ቁትትር ያበዛል?
ፈትለ -አይ፣ ተኮላ እወነቱን ነው፡፡ መጠጥ ለሴት ልጅ በአገራችን ነውር ነወ ‹‹ የሴት ጠጪ
　　የግመል ፈንጪ›› ሲባል አልሰሙም?
ሳሊምቢኒ -እኔ አልሰመቶም ምን ማለት ነው?
ፈትሉ- ሰካር በእኛ በሴቶች ላይ አያምርብንም
ሳሊምቢኒ- (ተነስቶ እየተጠጋት) ምን ይወዳል አንቺ?
ፈትሉ- (ገድገድ ሲል) ኸረ በመድኒያለም ፣ እላይ ላይ እንዳይወድቁ ፡ ይቀመጡ እባክዎ…
ሳሊምቢኒ- (ብርጭቆዋን አንስቶ እየሰጣት) ባክዎ አንድ ብቻ፡ ይቺ ብቻ ተቺው … ባክዎ
　　ፈትልወርክ…

የሳሊምቢኒ የቋንቋ አጠቃቀም ከፈትለ ጋር ይመሳሰላል?

ሁለቱ የሚናገሩት ቋንቋ ቢያንስ በአማርኛ አፍን በመፈታት እና ባለመፍታት መካከል ያለውን ሁኔታ ያገናዘበ መሆኑን ሳታጤን አልቀረህም የቋንቋ ተናጋሪው ባህል ከማወቅና ካለማወቅ ጋር በተያያዘም ሁለቱም በተለያየ የቋንቋ አጠቃቀም እንደሚናገሩ ማየት ይቻላል፡፡

## 5. ለዛ ያላቸውን የቋንቋ አጠቃቀሞች መጠቀም

ገፀባህሪያቱ የሚመላለሱዋቸው ቃለተውኔቶች ሳቢ፣ አስደሣችና ያልተሰለቹ መሆን አለባቸው፡፡ አንዳንድ ቃላተውኔት፡ ሀረጋትና አባባሎች ለረጅም ጊዜያት በተለያዩ ሰዎች ከመነገራቸው የተነሳ ስንሰማቸው /ስናነባቸው ስልችት ይለናል፡፡ ብዙ ሰዎች ለብዙ ዘመናት የተጠቀሟቸው በመሆኑም ነትበዋል እነዚህን የነተቡ የቋንቋ አጠቃቀሞች በቃለተውኔት ውስጥ አላስፈላጊ በሆነ መልኩ ማስገባት የቃለ ተውኔቱን ለዛ ሊጠፋው ይችላል፡፡

> ከላይ በተጠቀሰው መሰረት የነተቡ የቋንቋ አጠቃቀሞችን መቼም መጠቀም የለብንም ማለት ነው? ሀሳብህን በአጭሩ አስፍር፡፡/
>
> ____________________________________________________________
>
> _______________________________________________________--
>
> ________________________________________________________

የነተቡ የቋንቋ አጠቃቀሞች በቃለተውኔቱ ውስጥ መካተት የሚችሉበት አንድ አማራጭ ብቻ አለ፡፡ በተውኔቱ ውስጥ የቀረጽነው ገፀባህሪ በአነጋገር ዘይቤው ወይም በባህሪው የነተበ የቋንቋ አጠቃቀም የመጠቀም ባህሪ የሚታይበት ከሆነ ይኸው ገጸባህሪ ብቻ በቃለተውኔቱ ውስጥ የነተበ የቋንቋ አጠቃቀም ሊኖረው ይችላል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀሙ የገፀባህሪው የተለየ ባህሪ መገለጫ ስለሆነ በዚህ ረገድ ፀሐፊ ተውኔቱ ይህንን የመጠቀም ነፃነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ገፀባህሪያቱ በሙሉ ካለ ባህሪያቸው ለዛ አልባ የቋንቋ አጠቃቀሞችን እንዲጠቀሙ ማድረግ አይገባም፡፡ እንዲያውም የገፀባህሪያቱ ባህሪ እስከፈቀደ ድረስ ዘይቤያዊ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በቃለ ተውኔቱ ውስጥ ማካተት ተውኔቱን ሳቢ በማድረግ ረገድ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## 6. የንግግር ቃና /ድምፅት/ ማሳየት

በተውኔት ውሰጥ ያለ ቃለተውኔት የደብዳቤ ጽሑፍ አይደለም፡፡ ሰዎች የሚናገሩት ነው፡፡ ሰዎች የሚናገሩት እስከሆነ ደግሞ እንደተናጋሪው ሁኔታ፣ እንደንግግሩ ጭብጥ እና ስሜት በተለይ ቃና/ደምፀት የሚነገር ነው የሚሆነው፡፡ ገፀባህሪው ሲደሰት፣ ሲያዝን፣ ሲቆጣ፡ ወዘተ.. ተመሳሳይ ቃና አይኖረውም፡፡ የድምጽ ቃናው ተለይቶ ሊካተት ይገባል፡፡ እንደዚህም ሲሆን ነው የገፀባህነያቱን ስሜት ልንረዳ የምንችለው፡፡

## 7. አድንአት የሚሰጥባቸውን ጉደዮች በተገቢው ቦታ ማድረግ

በቃለ ተውኔት ውስጥ ገፀባህሪያቱ የሚናገሯቸው ንግግሮች ሁሉ አድንኦት የሚሰጥባቸው አይደሉም፡፡ አብዛኞቹ የገፀ ባህሪያት ንግግር አድንኦት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች የሚያብራሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንድ ፀሐፊ ተውኔት ቃለተውኔቱን ሲጽፍ ዋነኛው ነጥብ በማብራሪያው እንዳይሸፈን ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ይህ እንዳይሆን የሚመከረውም አድንኦት የሚሰጥባቸውን አረፍተነገሮች በየቃለተውኔቱ መጀመሪው ወይም መጨረሻ አረፈተ ነገር ላይ ማስቀመጥ ነው፡፡

ከዚህ በታች ከጌትንት እንየው (200፣85) እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ተውኔት የተወሰደው ቅንጫቢ ስለ ውጫሌ ውል አስራሰባተኛ አንቀጽ የሚያወሳ ነው፡፡ በዚህ ተውኔት አድንኣት የተሠጠው የትኛው ሀሳብ ነው፡፡

አንቶኔሊ ፡- ያውካል እኔ፡፡ (ፈትለወርቅን አየት ያደርጋታል፡፡ ፈትለ አይኗን ሰበር አድርጋ፣ መሬት መሬት ታያለች፡፡ እቴጌ ጣይቱ አንቶኔሊን እያዩ ፈገል ይላሉ) ፣ … ጃንሆይ አንድ ስህተት ፣ ማታለለል ተፈትራል፡፡ ይሄ ውል የኢታሊያ መንግስት በፍፁም አይጠላውም፡፡

ምኒልክ- መቀበልህ ፣ በመንግስትና በንጉስህ አምቤርቶ ስም ፊርመህ ማህተምህን አኑረህበታል፡፡

አንቶኔሊ - (ዮሴፍን) ይሄ ከታፊ ነው.. እሱ እኮ ፣ ንጉስ

ኡምቤርቶ - ይሄ በአማርኛ የተሳፈ ውል አላውከውም፡፡ የኢታሊያ መንግስት ይሄ ውል አይቀበለውም፡፡

ጣይቱ - በንጉስ ኡምቤርቶ ስም የተዋዋልኸውን ይህን ሰነድ መንግስትህ ካለተቀበለው፡ እኛም የውጫ ሌውን ውል አንቀበለውም፡፡

አንቶኔሊ- እንዲት አይከበልም እቴጌ? የውጫ ሌውን ውል አንቀበለውም፡፡

ጣይቱ - አናውቀውም፣ አንቀበለውም፡ ውጫሌ ላይ ከጀንሆይ ጋር በተፈራረምበት የአማርኛ የውል ሰነድ ላይ ‹‹ ኢትዬጰያ በኢጣሊያ ስር ታደራለች› .የሚል ቃል አይገኝበትም፡፡ አለ የምትል ከሆነ ያው አሳየን፡፡

በዚህ ቅንጫቢ የበለጠ ትኩረት የተሠጠው ምንድ ነው ትኩረት ነጥቡን (አድንኦቱን) የያዘው ሀረግስ በየቃለተውኔቱ መነሻ ወይም መጨረሻ ላይ ተጠቁሟል?

## 8. ቃለተውኔት ስብከት መምሰል የለበትም

ቃለተውኔት የገፀባሪያት ምልልስ ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም የስብከት ባህሪ ሊኖረው አይገባም፡፡ አንዱ ገፀባህሪ ብቻ ለረጅም ጊዜ እየተናገር ሌላው አዳማጭ ብቻ ሆኖ መቅረት የለበትም፡፡ በተቻለ መጠን በቃለተውኔት ውስጥ ያሉ ምልልሶች ተቀራራቢ ምጣኔ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለምላሌ ከላይ ያየነው የተውኔት ቅንጫቢ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ አንቶኔሊ፣ ጣይቱ ወይም ምኒሊክ ለብቻቸው ንግግር ሲያደርጉ አናስተውልም፡፡ የሁሉም ንግግር ተቀራራቢ ምጣኔ ያለው በመሆኑ ታሪኩ ፈጣን አካሄድ እንዲኖረው አድርጓል፡፡

## 9 ቃለተውኔቱን ከድርጊተ ጋር የተቆራኘ ማድረግ

ቃለተውኔት ከላይ እንደተጠቀሰው ስብከት ማለት አይደለም፡፡ በተውኔቱ ውስጥ የተሳሉ ገፀባህሪያት ሀሳባቸውን የሚያንሸራሽሩበት መድረክ ነው፡፡ ሰው ደግሞ ሀሳብን ሲያንሸራሽር የሀሳብ አለመጣጣም፣ ንዴት፣ ግጭት ወዘተ ይከሰታል፡፡ በንግግር ውስጥ ልዩ ልዩ የፊት ገጽታ መለዋዋጥ ልዩ ልዩ ድርጊቶች ይኖራሉ፡፡ ስለሆነም በቃለተውኔት ውስጥ የንግግርን ሁኔታና በዛ ውስጥ የተፈጠረውን እንቅስቃሴ የሚያመለክቱ ድርጊቶች መጠቆም አለባቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በገፀባህሪው ንግግር ሊጠቆሙ እና በመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ደግሞ ሊጠናከሩ ይችላሉ፡፡

## 10. ቃለተውኔቱ ሴራውን የሚያራምድ መሆን አለበት

የተውኔት ታሪክ የሚራመደዉ በቃለተውኔት ነው፡፡ ስለሆነም ቃለተውኔት ሲጻፍ ሴራውን የሚራምድ መሆን አለበት፡፡ አብዛኛዎቹ ተውኔቶች ሴራ ያላቸው ከመሆኑ አንጻር ቃለተወኔቴችም ከሴራው ጋር የጠበቀ ዝምድና ሊኖራቸው ይገባል፡፡

በቃለተውኔቱ ውስጥ የሰፈሩ ሀሳቦች በተቻለ መጠን ታሪኩን እያወሳሰቡ ተደራሲውን ሊቆጣጠሩ ይገባል፡፡ በተለይ ቆም ብለው የታሪኩን ፍስት ሊገቱት አይገባም፡፡ እያንዳንዱ ቃለተውኔት ሴራውን ወደፊት እየገፋ ተደራሲን መቆጣጠር መቻል ይኖርበታል፡፡ ደበበ (1973) እንደሚለውም ይህን የማያደርግ ቃለተውኔት የተውኔትን ውድ ጊዜ ይበላል፡፡

ቀደም ባሉ ገጾች ከጠቀሰናቸው አስር ነጥቦች ባሻገር በፀሐፊ ተውኔትና መምህርነታቸው የሚታወቁት መንግስቱ ለማ (1964) የቲአትር ድርሰት የአጻጻፍ ብልሃት በተሰኘ ጽሑፍቸው አንድን ጥሩ ቃለ-ተውኔት ለመጻፍ ቀጣዮቹን አምስት ነጥቦች መገንዘብ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

1. ትርፍ፣ አጫፋሪ የሆነውን ቃል ሁሉ ማስወጣት፣ መሰረዝ
2. የማያስፈልገውን ዝርዝር ሁሉ መቁረጥ
3. የሚነገረው አንደ በደንብ እንዲነገር፣ ያንኑ ግን አለመድገም፣ አለመደጋገም
4. ንግግሩ አንባቢን የሚያስቸግር፣ ምላስን የሚያደናቅፍ እንዳይሆን የቃላቱ አሰካክ ለተመልካች ጆሮ እንዳይከብድ ማድረግ
5. የጸፈውን ግንግግር መቃናት ወይም አለመቃናት ሊያውቅ ሲፈልግ፣ ደራሲው ጽሁፍን ለአንድ ቅርብ ጓደኛው ያንብብለት ሲያነብለት ስህተቱንና ጉድለቱን እግረመንገዱን ደራሲው ራሱ ሊያገኘው ይችላል፡፡

ቃለተውኔት ከላይ በጠቀስናቸው ነጥቦች መነሻነት ሊጻፍ ይገባል፡፡ እንደየሁኔታውም ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ለሶስቱም የቃለተውኔተ አይነቶች) ምልልስ፣ ጎንታ እና ንባብ አዕምሮ) ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

ለመሆኑ በምልልስ፣ በጎንታ እና በንባብ አዕምሮ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ልታስረዳኝ ትችላለህ? እስቲ ልዩነታቸውን በአጭሩ ጥቀስልኝ፡፡
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
__________________________________________

ምልልስ ሁለት እና ከዛ በላይ የሆኑ ገፀባህሪያት የሚያደርጉት የእርስ በእርስ የሀሳብ ልውውጥ ነው፡፡ ይህ የቃለ ተውኔት አይነት ተዘውታሪ እና ብዙውን የቃለተውኔት ቦታ የሚሸፍን ነው፡፡ እስካሁን ያየናቸው ሁሉም የተውኔት ቅንጫቢዎች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ንባብ አምምሮ (soliloque) ከምልልስ የሚለይ የቃለ ተውኔት አይነት ነው፡፡ ንባብ አእምሮ አንድ ገፀባህሪ (ተዋናይ) ከሌሎች ሰዎች ጋር ወይም ሰዎች ባሉበት ቦታ የሚናገረው ንግግር አይደለም፡፡ ብቻውን ሆኖ ከራሱ ጋር የሚነጋገርበት ቅርጽ ሲሆን በውስጣቸው ያለውን ሀሳብ ለመግለጽ ፀሐፊ ተውኔቱ የሚጠቀምበት የቃለ ተውኔት አይነት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከሌሎች የቃለተውኔት ቅርጾች ተለይቶ የሚታሰብ ነው፡፡ ብዙ ጊዜም እንደምልልስ አጭርና በሁለትና ሶስት መስመሮች የሚያልቅ ሀሳብን አይዝም፡፡

ፋንታሁ እንግዳ (2001-86-87) ንባብ አዕምሮ ያለውን አጠቃላይ ባህሪ እንዲህ ይገልፀዋል፡፡ንባበ አዕምሮ አንድ ተዋናይ ብቻውን በመድረክ ላይ የሚያሰማው ንግግር ነው፡፡ ንባብ አዕምሮ ተዋንያን በጭንቅላታቸው ወይም በልቦናቸው ውስጥ የሚያሰላሰሉትን ውስጣዊ ሃሳቦች ማለትም ተንኮል፣ የዋህነትን፣ ምኞትን፣ ተስፍ ማድረግን ወይም ተስፍ ማጣትን በተመለከተ የሰውን ልጅ በሃሳብ አነውለው አጣብቂኝ ውስጥ የሚከቱትን ጉዳዮች በልቡና ውስጥ ታምቀው ለመያዝ ሳይችሉ ሲቀሩ ለተመልካች ወይም ለአድማጭ ይፋ የሚወጡበት የብቸኝነት የአነጋገር ስልት ነው፡፡

ይህ ቅንጫቢ የተወሰደው ከፀጋዬ ገብረመድህን (1958፣19-20) የኮርሞ ሰው ተውኔት ነው፡፡ በተውኔቱ ውስጥ ዋናው ገፀባህሪ ሞገስ ታናሽ ወንድሙ አሞኛል ብሎ ለመድሃኒት መግዣ ብር ተቀብሎት እንደወጣ የሚያቀርበው ቃለተውኔት ነው፡፡

> ትሁኔ ትታኝ ከመኮብለሏ በፊት ሚስቴ ከመሄድዋ በፊት ው-ወፊፌ ነው ብላ ጥላኝ ከመሄድዋ በፊት.. ለልጆቻችንና ለኛ አንገት ማስገቢያ የምትሆን ዛኒጋባ ቢጤ ሳልቀልስ ብዬ እታትር ነበር…. አሁንም ሀሞቴ ፈሰሰ እንጂ ተስፋ አልቆረጥኩም፡፡ … ያሁን ጥረቴ ዛኒገባ ለመቀለስ ሳይሆን ተስፋ ላለመቁርጥ ነው፡፡… አዎን አላማዬ ሁሉ ለመደርጀት ሳይሆን ተስፋ ላለመቁረጥ ብቻ ሆኖ ቀርቷል፡፡ ሀሞቴ እንኳ ቢፈስ የእማዬ ተግሳፅ ትዝ እያለኝ አየታዘብኩ እየሰገድኩት “ተኮላ ግን” ሴትና ይሎኘታ ያከበሩትን ነው እምታጠቃ አለም በአዘነች ቁጥር በልቦናህ የሌለብህን ጉድፍ በጥርጣሬ ውስጥህ በመፈለግ ነው እንዳይሆን አርጋ የምትጫወትብህ መፍጠጥና መጋተር ብቻ ነው እሚያዋጣ.›› ይላል፡፡…
> ያ-ያለተኮላ አይዞህ ያለኝ አልነበረም፡፡ እ-እግዚአብሔር እንኳ ጀርባውን ያዞረብኝ መሰለኝ፡፡ የ-የተጋለጥኩ መሰለኝ፡፡ ተ-ተኮላ ግን ”አይዞህ ጋሼ” አለኝ፡፡ ይሁንና ከዚያች እለት ጀምሮ ከኔ ልብ ይልቅ የሱ በጭካኔ ተዳፈነ፡፡ ከኔ ይልቅ እሱ ሰው ፈራ ፣ ሸሸ ሰው አውሬ ነው ብሎ ራሱ አውሬ ሆነ ፡፡ ተ-ተኮላ…

ከሞገስ ንግግር ተነስተህ ሞገስ ምን እንዳስጨነቀው መገንዘብ ችለሀል?

ከሞገስ ንግግር ተነስተህ ሞገስ ምን እንደሰጨነቀው መንገንዘብ ችለሀል? ንባብ አእምሮው የሚነግርህስ ነገር ምንድን ነው? የታሪኩን ሴራስ ለማራመድ የሚበጀ ይመስልሀል? ከራስህ ጋር ተወያይበት፡፡

ጎንታ (aside) ሌላው የቃለ ተውኔት አይነት ነው፡፡ አንድ ገፀባህሪ (ተዋናይ) ሌላው ገፀባህሪ (ተዋናይ) ሊሰማው በማይችል ቦታ እንደቆመ ታዛቢ ተደርጐ ስለሌላው ወይም ስለሌሎቹ የሚናገረውና ተደራሲው ብቻ እንዳደመጠወ ተቆጥሮ የሚቀርብ የቃለ ተውኔት አይነት ነው፡፡

> ጐንታ … አንድ ገፀባህሪ ወይም በመድረክ ሲተረጐም አንድ ተዋናይ በመድረክ ላይ አብረው የሚተውኑት ተዋንያን እንዳላዳመጡት ተቆጥሮ ተዋናዩ ሌላውን ተዋናይ ወይም ሌሎችን ተዋንያን በማሳጣት፣ በመታዘብ፣ በመንቀፍ እና በአጠቃላይ በመቃወም ለተመልካች የሚነግርበት ወይም የሚያሳውቅበት ዘልማድ ነው..?በዘመነ--ተሃድሶ ይህ ተውኔታዊ ዘልማድ ጥቅም ላይ ይውል የነበረው የገፀ ባህሪን ወይም የተዋናይ ውስጣዊ ስሜትን ለታዳሚው ለማሳወቅ ነበር፡፡ ከአስራ ከዘጠኛው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ አሁን እስከምንገኝበት ዘመን ግን ዘልማዱ በጽንቃይና በቧልታዩ ተውኔቶች ውስጥ በተመልካች እና እንዲሁም በአንባቢ ዘንድ ሳቅ ለመጨመር ሲባል ጥቅም ላይ ይውላል (ፋንታሁን ፣2001-174)፡፡

## 5 ጭብጥ

በዚህ ምዕራፍ በመጨረሻ የምናነሳው እና አምስተኛ የተውኔት አላባ የሆነው ጭብጥ ነው፡፡

> በተለያዩ የስነጽሁፍ ትምህርቶች ውስጥ ስለጭብጥ በተደጋጋሚ እንደተማርክ ፣ እንደተወያየህ ይታወቃል፡፡ እነዛን ትምህርቶች በማስታወስ ስለጭብጥ ጠቅለል ያለ ሀሳብ አቅርብ፡፡
> ________________________________________________
> ________________________________________________
> ________________________________________________
> _______ ________________________________________

ጭብጥ አካባቢያዊ እና ሁለንተናዊ ተብሎ ለሁለት ይከፈሏል የሚለውን ሀሳብ የሚያቀርበው ፋንታሁን (2001-177) አካባቢያዊ ጭብጥ ወቅታዊ ሁኔታን መሠረት አድርጐ የሚጻፍ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ በአንድ ዘመን እና አካባቢ የተፈጠረን ነገር መነሻ በማድረግ የሚፃፍ የተውኔት ጭብጥ አካባቢያዊ ጭብጥ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ተውኔቱ ተቀባይ የሚሆነው፣ ተደራሲው በዛው ዘመን የኖረ እንደሆነ ነው፡፡ ተውኔቱ ከተጻፈበት ክልልና ዘመን ውጭ ያለ ተደራሲ በዚህ የተውኔት አይነት ብዙም አይደመምም ተውኔቱም ከዛ ወሰን ጊዜ በኃላ ይከሰማል፡፡ በሌላ ቦታ ወይም በቀጣይ ዘመናት የመታየት እድሉም እጅግ ጠባብ ነው፡፡ ስለሆነም ዘላቂነቱ አስተማማኝ ያልሆነ ተውኔት ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ በአንጻሩ ሁለንታዊ ጭብጥ የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡

ሁለንታናዊ ጭብጥ የአለማቀፋዊነት ባህሪ አለው፡፡ በየዘመኑ የተፈጠሩ ክስተቶች፣ ባህል፣ ጊዜ እና ቦታ ሳያግደው የሚታይ የተውኔት ጭብጥ፣ ሁለንተናዊ ጭብጥ ነው፡፡ ሁለንተናዊ ጭብጥ ባለበት ተውኔት የሚነሱ ርዕስ ጉዳዮች ሁሉንም (አብዛኛውን) የአለም ህዝብ በየትኛውም ቦታና ዘመን የሚያሳስቡ እና የሚያወያዩ ጉዳዩች ናቸው፡፡ እንደ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ክብር፣ ዝና ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዮች የዚህ የሁለንታናዊ ጭብጥ ማጠንጠኛዎች ናቸው፡፡

ሁለንተናዊ ጭብጥ ያላቸው ተውኔቶች በሰባዊ መሰረታዊ ባህሪያት ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ዘመናትን ተሻግረው ሲታዩ እንመለከታለን፡፡ በየሀገሩ ቋንቋ ተተርጉመው ሲቀርቡም ተቀባይነት አያጡም፡፡ ለዚህም በአማርኛ ቋንቋ የተተረጎሙትን እና ኤዲፕስ ንጉስ፣ ማክቤዜ እና ሐምሌትን በምሳሌትን ማንሳቱ በቂ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ ጭብጥ ፀሐፊዉ ያስተላለፈው አብይ መልክት ነው ወይስ ተደራሲው የተረዳው አብይ መልክት ነው? የሚለው ጥያቄ ሲያወዛግብ እንመለከታለን፡፡ አንተ የትኛውን ትደግፋለህ? ለምን? ወይስ የተለየ አተያይ አለህ?

ጭብጥ አዕምሮአዊ ጉዳይ እንደመሆኑና ጭብጥን ከአንደ ተውኔት ውስጥ ለማውጣት የቀደመ እውቀትና ልምድ ተፅእኖ ከመፍጠሩ አኳያ የአንድ ተውኔት ጭብጥ እከሌ ያለው ብቻ ነው ለማለት አያስችልም፡፡ እያንዳንዱ ወገን ጭብጥ ነው ላለው ጉዳይ ከተወኔቱ በቂ አስረጂዎችን ማሳየት ከተቻለው ፣ ከራሱ እውቀትና ልምድ ተያያዥ ሀሳቦችን እያጠቀሰ ማስረዳት ከቻለ፣ የመዘዘውን "ጭብጥ" እንደ ተውኔቱ ጭብጥ ልንቆጥርለት እንችላለን ቢያንስ ሌላ በአሳማኝ ሁኔታ ቀርቦ የነበረውን ማስረጃ የሚያጣጥል ወገን እኪመጣ፡፡

**መልመጃ**

ይህን ትእይንት ካነበብክ በኃላ ያሉትን ጥያቄዎች እንደጥያቄው አይነት በአግባቡ መልስ፡፡

**ትእይንት 4**

ተጫኔ በተከራየው ቤት አዲስ አበባ (ትዝታ)፡፡

የሚለጥቀው የትዝታ ትርኢት ነው፡፡ ተጫኔ ማዕድ ላይ ነው፡፡ በፈረንጅ ሥርዓት የፈረንጅ ምግብ እየበላ አሁንም ሰዓቱን ያያል፡፡ ኮት አልደረበም፣ ክራቫት አላሠረም፣ የቤት ጫማ ሰክቷል፡፡ ፊቱ ከሪዝና ከጢም ፈጽሞ ነፃ ነው፡፡

ተጫኔ፣ ያበሻ ቀጠሮ ማለት እገዘሙ ዘንድ አለች ምሳ እንበላ አልኩት ሰባት ሰዓት ተኩል ሆኗል፡ ገና አልመጣም፡፡ (በር ይነኳኳል) ግባ ገዝሙ ጊዜ አሳልፈሃል፡፡ ሳያልቅብህ ድረስ፡፡
ዘበኛው ይገባል በዕድሜ መሀከለኛ የሆነ ጥሬ ባለገር ነው ግን ብልጠት አያጣም፡፡

ዘበኛ፣ ጌታዬ አን ድ ሽማግሌ በጧት የመጡ ደጅ ተጉልተዋል እርስዎን ካላየሁ፡፡

ተጫኔ፣ ስማቸውን አልነገሩኝም፡፡ ጌቴቸ ስሜን ያውቁታል ይላሉ፡፡

ተጫኔ (ይጮሀል) ወይ መከራ ፡ የስንቱን ሽማግሌ ስም ላውቅ ነው እንግዲህ ፡ መልኩ ምን ይመስላል?

ዘበኛ፡ ረዘም ቀጠን ያሉ ናቸው፣ ሽበቶ፡፡

ተጫኔ ዕድሜውስ?

ዘበኛ፣ ጠና ያሉ ናቸው፡፡ ከሰባ ያንሣል? ከሩቅ አገር መጣሁ ይላሉ ከባለገር፡፡

ተጫኔ፡ ጉዳዩ ምንድ ነው?

ዘበና፣ ጉዳዩ የለኝም አሉ፡ የርስዎን የጌቶችን ዓይንዎን ለማየት ብቻ ነው አሉ፡፡ መንገድ መቷቸዋል ጌታዬ ፣ እግራቸው አቧራ ለብሷል ተሰነጣጥቋል፡፡

ተጫኔ፡ ወዲያ አባርልኝ፡፡ ለሥራ ፊት ጊዜ የለኝም፡፡ የለም በል ተጫኔ ናዝሬት ሄደዋል በል፡፡

ዘበኛ፡ ብዬአቸው፡ አሁን በመኪና ሲገባ አይቼዋልሁ እያሉ ድርቅ አሉብኝ፡፡ ደሞ የቸገረኝ ነገር አለ

ተጫኔ፡ ምን?

ዘበኛ፡ ከፈቀዱልኝ ልንገርዎ-- ሽማግሌው የሚሉትን፡፡

ተጫኔ ወይ ጠጣ ፡ ምንደነው ነገሩ ተንፍሰው ይውጣል፡፡

ዘበኛ፡ ኧረ ከበድ ያለ ነገር ነው የሚናገሩት

ተጫኔ ምን ይላል

ዘበኛ፣ አባት አባትም ነኝ ይላሉ፡፡

ተጫኔ (ብው ይላል በቁጣ) ቀጣፊ ነው፡፡ አባት የለኝም፡፡ አባቴ ገና ዱሮ ሞቷል፡፡ ለባንዲራው ለነፃነቱ ሲዋጋ ደሙን አፍሷል፡፡ አጥንቱን ከስክሷል የማንንም አጭበርባሪ ስብከት ወሬ ብለህ ማምጣትህ አንተ ክፉኛ ደፈርከኝ በወንጀል ላስቀፈድድህ እችላላሉ ትሰማኛለህ? አባት የለኝም ሞቷል ነው የምልህ ያባባን ነፍሱን ይማረው፡፡

ዘበኛው፡ (ሳይደነግጥ ይሽቆጠቆጣል) እኔም ለሽማግሌው ነገሬአቸዋለሁ፡፡ የጌቶች አባት በማይጨው ጦርነት ከጣልያን ሲዋጉ ሞተዋል ታላቅ ፊታውራሪ ታላቅ አርበኛ ነበሩ ብዬ አስተባብያለሁ፡፡ ሽማግሌው አይሰሙም ወንድሜ አባቱ እኔ ነኝ አለሁ ይኸው እዚህ በሕይወት እገኛለሁ ይላሉ፡፡ ምናልባም የጌቶች ክርስትና አባት እንደሆኑ?

ተጫኔ የለኝም ስልህ ክርስትና አባትም የለኝም፡፡ እሱም ሞቷል፡፡

ዘበኛ፣ የንስሐ አባትስ? ሻሽ ቢጤ ሽብ አርገዋል፡፡

ተጫኔ፣ (ብድግ ይልና ያፈጥበታል) የንሰሐ አባት ይዤ አላውቅም፡፡

ዘበኛ፣ እንግዲያስ ጌታዬ ይቅርታ ያደርጉልኝ ሽማግሌው አጠራጥረውኝ ነው፡፡

ተጫኔ፣ ሰማኝ፡፡ አሁን ስለቀባጠርከው ሁሉ ያንድ ወር ደሞዝ ቀጥቼሃለሁ፡፡ በል አሁን እያየሁህ ሂደና ቀስ ብለህ ሽማግሌውን ከዚህ ግቢ አስወጣ፡፡ እምቢ ካለህ በዱላ ነርተው፡፡ ሁለተኛ ዝር ቢል ካንተ ነው ጠቤ፡፡ ወዬውልህ

ዘበኛ፣ (ደንገጥ ይላል) ኧረ ምን ገዶኝ ጌታዬ?አላደርሳቸውም፡፡ (እየተነጫነጨ ይወጣል)
መዘዘኛ ሽማግሌ የሰው ደሞዝ ሊያስቆርጡ ነው ሳይ ጨንቃቸው በሰው እንጀራ ይገባሉ?
ተጫኔ ለጥቂት ሴኮንድ በመስኮቱ ወደ ውጭ ያይና ተመልሶ ምሳ መብላቱን ይቀጥላል፡፡ ወዲያው በር ይመታል፡፡ ገዝሙ ይገባል፡፡ የገዝሙ ጠቅላላ አኳኋኑ በመጀመሪያው ትርኢት እንዳየነው ያለ ነው ብቻ ልጅነት አለው፡፡

ተጫኔ እስካሁን ምን አዘገየህ? ቅረብ፡፡ ምን የመሰለ የዶሮ አሮስቶ እንደሚጠብቅህ አታውቅም፡፡ ያውልህ ወንበር፡፡

ገዝሙ፣" አልቀመጥም፣ መብል አላሰኝም፡፡ እቢሮ ሳለሁ ርቦኝ ነበር፣ እዚህ ስደርስ አንጀቴ ቁልፍ አለብኝ፡፡ (በክፍሉ እየተዘዋወረ የግድግዳ ሥዕል ይመለከታል)

ተጫኔ፣ ተው ይሻልሃል፡ ሆድ ባዶ አይወድም፡፡

ገዝሙ፣ በንዳዬ ጉዳይ ገባ አትለኝም፡ ዘበኛህን ተቆጣው፡፡ ምን የመሰሉትን አረጋዊ ሲያንገላታ ደረስኩበት፡፡ ባልደርስልቸው ባፍጢማቸው ተደፍተው ነበር፡፡

ተጫኔ፣ ተወው እባክህ ደግ አደረገ፡፡ ለማኙ አስቸግሯል፡፡

ገዝሙ፤ ‹‹ ልጄ ነው ልጄ ነው ፡ ሠው አንድዬ ያውቀዋል አንድ ልጄ ነው፡ ›› እያሉ ሲጮሁ ነበር፡፡

ተጫኔ (ወዲያው አይመልስም አጥንት ይግጣል) ስሙን ጠይቀኸውዋል?

ገዝሙ አቶ ሳህሉ እባላለሁ አሉኝ፡፡

ተጫኔ፣ አውቀዋለሁ፣ ድሮ ከጣልያን በፊት ያባቴ በቅሎ ያዥ ነበር፡፡
አሁን ይኸው እንደምታየው፣ እልም ያለ ሰካራም ሆኗል፣ አልኮሊስት፡፡ ለመጠጫ ገንዘብ ካልወለድክ ነው የሚለው ነጋ ገንዘብ ጠባ ገንዝብ ነው፡፡ ሰልችት ይልሃል፡፡ ፊት ፊት እሰጠው ነበር፡ የዱሮውን እያስታወስኩኝ፡፡ አሁን ግን ገና ደጃፌን ሲረግጥ በዘበኛ አባርራለሁ፡፡ ይህ ጭካኔ አይምስልህ፡፡ ለራሱ ብዬ ነው፡፡ ገንዘብ ብሰጠው ካቲካላ ይጋተበታል፡፡ ለራሴው ብዬ ነው

ለነፍሴስ፣ በሰማይ ቤት መጠየቅ አለ፣ ፍርድ አለ። ለአልኮሊስት ገንዘብ መስገሥ ለታመመ ሰው መርዝ ማቅመስ ነው። (አፉን በጠረጴዛ መሃረብ ጠርጎ ገበታ ይነሳል)

‹‹ለተባባሰው ማጭድ አታውሰው›› የሚለው ያባቶቻችን ምሳሌ ትልቅ ቁም ነገር ያዘለ መሆኑ መረዳት አለብህ።

ገዝሙ፣ (በምፀት ጥርሱን ብልጭ በማድረግ) ታዲያ መልካችሁን ምን እንዲህ አማሰለው?

ተጫኔ፣ ምን ማለትህ ነው ? አይገባኝም። የሚማሰል ወጥ ነው።

ገዝሙ፣ ይቅርታ። መልካችሁን ምን አመሳሰለው? ማለቴ ነው። ሽማግሌው ቁርጥ አንተን ናቸው። አንተም ልክ አርጎ ላየህ የሳቸው ፎቶ ነህ።

ተጫኔ ይኸ ምኑ ያስገርማል? አንድ ቀን በለንደን ከተማ ልክ አንተን የሚመስል ሰው ዓይኑ ነው ጥርሱ፣ አፍንጫው ጆሮው ሳየቀር፣ ከነአሳሰቁ ከናረማመዱ ቁርጥ አንተን የሆነ ፈረንጅ አጋጥሞኝ ነበር። ልዩነቱ በቆዳ ቀለም ብቻ ነው፣ እሱ ነጭ አንተ ጥቁር።(ሶፋ ላይ ጎለል ይልና የጠገበ ሆዱን እየደባበሰ ቀበቶውን ፈታ ያረጋል ጥርሱን በሰንጥር ይነቃቅሳል) መልክ አታለይ ነው መመሳሰል መዛመድን አያስከትልም።

ገዝሙ፣ በዚህ አያያዝ ሽማግሌው በብስጭት ቢሞቱ አያስገርምም።

ተጫኔ እሺ፣ ምን አርግ ነው የምትለኝ?

ገዝሙ ለምን ላንዲት ደቂቃ አታነጋግራቸውም? ሲምሉ ሲገዘቱ በጆሮዬ ሰምቻቸዋለሁ። ‹‹አይኑን ብቻ ልየው ፣ ቤሣ ቤስቲን ብዬ አላስቸግረውም›› ነው የሚሉት።

ተጫኔ፣ ሽማግሌው ፋኖ ነው ተወው ። አንዳንዴ ደግ ለመሠራት ጨካኝ መሆን የሚያስፈልግበት ጊዜ አለ። ለሱ የሚሻለውን የማውቀው እኔ ነኝ፣ አንተ አይደለህም።

ገዝሙ፣ ምን እንዲህ ያስጨክንሃል? ሽማግሌው ሌላው ቢቀር ድኃ ናቸው።

ተጫኔ፣ (ካንገቱ ቀና ይልና ሶፋው ላይ ቁጭ ይላል። ብድግ ይላል) ድኃ ድኃ የሚሉ ሰዎች እንደሰለለቹኝ ያንገፈግፈኝ የለም። ብለህ ብለህ አንተም ከነዚህ ተደምረሃል። ድሃ ድሃ-ድሃ ይላሉ። ድህነት ምንድ ነው መልኩ ምን ይመስላል? ቢላቸው የሚመልሱትን ያጣሉ። ድህነትን አይተውት አያውቁም፡ እኔ አይቼዋልሁ፡ ቀምሼዋለሁ። አባቴ በማይጨው ከሞተ በኃላ እናቴም ተደገሙ። አንድ ዘመድ አልተፈረኝም። ድህነትን ብቻ አይደለም ጌትነትም በልጅ ነቴ አይቼዋልሁ፣ ከጠላት በፊት። ያባቴ ዋርዳ ሳሙና በቅሎ ከነመረሽቷ፣ ቡሎ ያባቴ ፈረስ፣ አባቴ የሚያሲዙት ብረት የሚያከትሎት ሰራዊት ፣ ያሽከሩ የባሪያው ብዛት ያ ሁሉ አሁን ትዝ ይለኛል።

ገዝሙ ፣ እሱን ተወዉና ይልቅ ሽማግሌው ርቧቸዋል መንገድ መቷቸዋል።

ተጫኔ ሰው ድሀ ድሀ እያለ ከንፈሩን ይመጣል። ሲያላግጥ ድሃውን “የኔ ቢጤ” ይለዋል የኔ ጋደኛ። አንጀቴን ያራሰው በርናንድሾ ብቻ ነው ፣ የእንግሊዙ ደራሲ። አንዷ ተመጻዳቂ ወይዘሮ ባጋጣሚ ታገኘዋለች። ፣ “ሚስተር በርናንሾ መጽሐፍትህን አንብቤ እጅግ ፈንድቄአለሁ። ድሆችን ምንኛ ብትወዳቸው እንደዚህ አድርገህ አሳምረህ ስለነሱ ችግር ስለነሱ ጭንቅ መጻፍህ? ”አለችው።” ነገሩ እንደዚያም አይደል፣ እሜቴ›› አለ ቢርናንድሾ። “ድሀ አልወድም። እንዲያውም እንደ ድሀ የምጠላ ነገር በዓለም የለም። ድሆችን ጥልት አድርጌ ስለምጣላ አንዳቸው ሳይቀሩ ከገፀ ምድር እንደጠረጉ ነው ልፋቴ” አላት ይባላል በርናንድ። አልተሳሳተም።

ገዝሙ፣ (በምፀት ሳቅ ራሱን ይወዘውዛል) አይ ሌላ ወዮ ሌላ። ያለነውን ታሰኘዋለህ። እሱ ያለው ድህነት ካለም ላይ ይጥፋ። አንተ የምትለው ድሀ ይጥፋ፡ (በር ይመታል ዘበኛው ይገባል።)

ዘበኛ፣ ጌታዬ፡ በስንትና ስንት ትግል ከያኔ ሽማግሌ ተገላገልኩኝ። እንዳፋቸው ቢደረግልን ዳግመኛ ዝር አልልም ብለዋል፡

**መ ጋ ረ ጃ፡**

**የማገናዘቢያ ነጥቦች**

የሚከተሉትን የማገናዘቢያ ነጥቦች በመመርመር በምታውቀው ላይ የ /✓/ ምልክት አድርግ፡በማታውቀው ደግሞ የ /ጨ/ ምልክት አድርግና ነጥቡን ወደኃላ ተመልሰህ አንብበው፡፡

- ስለተውኔት አለባውያን አስፈላጊነት አብራራለሁ...................................... ☐
- ስለተውኔት ገፀባህሪያት ቀረጻ ማብራራት እችላለሁ................................ ☐
- ቃለ-ተውኔት ሲጻፍ መከተል ስለላብኝ ጉዳዮች መግለጽ እችላለሁ............... ☐
- በምልልስ እና በንባብ አፅምሮ መካከል ያለውን ልዩነት ማብራራት እችላለሁ........ ☐
- በጎንታ እና በንባብ አፅምሮ መካከል ያለውን ልዩነት አብራራለሁ.................. ☐
- የአንድ ተውኔት ጭብጥ በማን ሊታወቅ እንደሚችል አስረዳለሁ.................. ☐
- በሴራና በታሪክ መካከለ ያለውን ልዩነት አብራራለሁ................................. ☐
- የተውኔት መቼት ከልቦለድ መቼት የሚለይበትን ባህሪ እገልጻለሁ.................. ☐
- በድርጊት መግለጫ እና በቃለተውኔት ቋንቋ መካከል ያለውን ልዩነት አብራራለሁ... ☐

## ግለ ፈተና -ሶስት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበብክ በኃላ ፣ ትክክለኛ ሃሳብ የያዘሱት "እውነት" ሀሰተኛ ሀሳብ ያየዙትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ፡፡

______1. የድርጊት መግለጫ ቋንቋ እና የቃለ-ተውኔት ቋንቋ አጠቃቀሞች የተለያዩ ናቸው

______2. ቃለ-ተውኔት ሲጻፍ በተቻለ መጠን ረዘመ ማለተ አለበት፡፡

_____3. የአንድን ተውኔት ጭብጥ ተመልካች ሲያውቀው ይችላል፡፡

___ 4. ሴራ የድርጌቶች ቅደም ተከተል ብቻ የሚገልጽበት የተውኔት አላበ ነው፡፡

______ 5. የተውኔት ገፀባህሪያት የእውነት አለም ሰው ባህሪ ሊይዙ አይገባም፡፡

________ 6. የተውኔት መቼት በተቻለ መጠን ውስን የመሆን ባህሪ ሊኖረው ይገባል፡፡

_______ 7. አስተኔ ግፀባህሪያት ብቻ ባሉበት ተውኔት ፣ የተውኔቱን ሴራ ልል ይሆናል

________ 8. ተውኔት በግጥም ቅርጽ ሊቀርብ ይችላል፡፡

_______ 9. አካባቢያዊ ጭብጥ ያላቸው ተውኔቶች ዘመን ተሻግረው ሊታዩ ይችላሉ፡፡

_______ 10. በቃለተውኔት ውሰጥ አንድኣት የሚሰጠው ጉዳይ በአርፍተ ነገሩ መካከል ይቀመጣል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የተውኔት መዋቅር

### መግቢያ

ውድ የዚህ ኮርስ ተከታታይ በዚህ ምዕራፍ ላይ የምንነጋገረው ተውኔቶች ስለሚከፋፈሉበት መዋቅር ነው፡፡ በቅርጽ ደረጃ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሰፋ ያለ ስለሚሆን ልቦለዶች በምዕራፍ እንደሚከፋፍሉት ሁሉ ተከፋፍሎ ይቀመጣል፡፡ ይህንንም የተውኔት መዋቅር በሚለው በዚህ ምዕራፍ እንመለከተዋለን፡፡

የተውኔት ዋነኛ የመዋቅር ክፍሎች ገቢር እና ትዕይንት በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ገቢር በውስጡ ትዕይንቶችን ያቅፋል አንድ የተውኔት ክፍል በገቢር እና በትዕይንት የሚከፋፍልበት ምክንያት ያለ ሲሆን በዚህ ምዕራፍም ትኩረት የሚደረግበት ይኸው ጉዳይ ይሆናል፡፡ በምዕራፍ በቅድሚያ ስለገቢር ምንነት እና አከፋፈል የሚነሳ ሲሆን እሱን ተከትሎ ስለትዕይነት ምንነት እና አከፋፈል ሀሳብ ይቀርባል፡፡

ውድ የዚህ ኮርስ ተከታታይ እንደቀደሙት ምዕራፎች ሁሉ በዚህ ምዕራፍ ውስጥም ወደገለጻ የሚወስዱ ጥያቄዎች፣ ገለጻዎች፣ መልመጃዎች እንዲሁም በስተመጨረሻ ላይ የማገናዘቢያ ነጥቦችና ግለፈተናዎች ይኖራሉ፡፡ እነሱን በሚገባ በማንበብ እና በመስራት ትምህርቱን በሚገባ እንደምትከታተል ተስፋ እንጥልብሃለን፡፡

<table><tr><td>
አላማ<br>
ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኃላ<br>
- ስለገቢር ምንነት ታብራራለህ<br>
- ተውኔቶች በገቢር የሚከፋፈሉበት ምክንያቶች ትዘረዝራለህ<br>
- ስለትዕይንት ምንነት ታብራራለህ<br>
- ገቢሮች በትዕይንት የሚከፋፈሉበትን ምክንያቶች ትዘረዝራለህ
</td></tr></table>

## 4.1. የተውኔት መዋቅራዊ ክፍሎች ምንነት

የተውኔት መዋቅራዊ ክፍል ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ ያስፈልጋል? በአጭሩ አብራራ

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

የተውኔቱ መዋቅራዊ ክፍል ማለት አንድ ተውኔት በመልክ በመልኩ የሚከፋፈልበት የተውኔቱ ምዕራፍ፣ ክፍሎች ማለት ነው፡፡ አንድ መጽሀፍ በምዕራፍ እና በክፍሎች እንደሚከፋፈል ሁሉ ተውኔትም እንዲሁ ተከፋፍሎ መቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ተውኔቱን ከተለያዩ ነጥቦች አካያ ከፋፍለን የምንለያይባቸው አካላትም የተውኔት መዋቅራዊ ክፍሎች ይባላሉ፡፡ እነዚህ መዋቅራዊ ክፍሎችም ገቢር እና ትእይንት በሚል ስያሜ ይጠራሉ፡፡

ሁሉም መጽሐፎች በርካታ ክፍሎችና ምዕራፎች እንደማይኖራቸው ሁሉ፣ ሁሉም ተውኔትም በርካታ ገቢርና ትዕይንቶች አይኖሩትም፡፡ ደበበ (1973፡26) እንደሚጠቅሰው " የገቢሮችና የትዕይንቶችን ቁጥር የሚወስነው የተውኔቱ ይትበሀል፣ ተውኔቱ እሚያቅፈው የመድረክ ጊዜና ስፍራ መጠን ነው፡፡" ይኸው የስነ ተውኔት ትዕይንት ባለሙያ ጨምሮ እንደሚገልጸው "የጥንታውያን ግሪኮች የነሶፎክልስ ተውኔቶች ትዕይንት የማይበዛባቸው ባለአምስት ገቢሮች ሲሆኑ፣ የሼክሲፒር ተውኔት አያሌ ትዕይንቶችን በያዙ አምስት ታላላቅ ገቢሮች የተከፈሉ ናቸው" በአንጻሩ ከነዚህ ዘመናት በኋላ ብቅ እያሉ ያሉ "አያሌ ተውኔቶች ብዙ ትዕይንቶች የሌለባቸው ባለሶስት ገቢሮች ወይም ብዙ ትዕይንቶችን የያዙ ባለ አንድ ገቢር ናቸው፡፡" (እንደላይኛው)

ለመሆኑ ገቢር እና ትዕይንት ምን ማለት ነው ?የትኛው የየትኛው አካልስ ነው?

ገቢር እና ትዕይንት የተውኔት መዋቅራዊ ክፍሎች እንደሆኑ፣ ትዕይንትም በገቢር ውስጥ ያለ ንኡስ ክፍል እንደሆነ ከላይ ከተሰጠው መንደርደሪያ በመነሳት የሚከለስ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ በታች ባሉ ሁለት ንዑሳን ርዕሶች የምንመለከተውም ስለነዚሁ ሁለት የተውኔት መዋቅራዊ ክፍሎች ስለሆነ ስለምንነታቸው ተጨማሪ ሀሳቦችን ታገኛለህ፡፡

## 4.2. ገቢር

ገቢር በአንድ ተውኔት ውስጥ ያለ ዋነኛው ክፍል ነው፡፡ አንድ ተውኔት አንድ እና ከዛ በላይ ገቢሮች ሊኖሩት የሚችል ሲሆን እያንዳንዱ ገቢር የተውኔቱ አብይ ክፍል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ገቢር አብዛኛውን ጊዜ በተውኔት ታሪኩ ውስጥ የቦታና የጊዜ መለወጥ የሚያመለክት የተውኔት መዋቅራዊ ክፍል ነው አልፎ አልፎ ደግሞ የቦታ ወይም የጊዜ ለውጦች ሲኖሩ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ገቢር ከላይ የተጠቀሰው ባህሪ ስላለው ከአንድ ገቢር እና በሌላው ገቢር መካከል የቦታና የጊዜ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ይህም በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ተውኔቶች በመድረክ ሲመደረኩ የገቢር ልዩነቶችን ለማሳየት መጋረጃ ይጣላል፣ ቁሳቁሶች ቦታቸውን ይቀያይራሉ፡፡ የአልባሳትና የሌሎች ግብአቶች ለውጥም ይከሰታል፡፡ መጋረጃው ሲገለጥም የቀጣዩ ገቢር አዲስ የታሪክ ቦታ እና /ወይም ጊዜ ይተካል፡፡

ገቢር በራሱ ምሉዕነት ያለው የተውኔት መዋቅር ነው፡፡ አንድ ገቢር በተናጠል ሙሉ ተውኔት ሊሆን ይችላል፡፡ ፋንታሁን እንግዳ አብዛኛዎቹ ተውኔቶችም ባለአንድ ገቢር ናቸው፡፡ ከአንድ በላይ ገቢሮች ባላቸው ተውኔቶች ውስጥ የሚሰፍሩ የተለያዩ ገቢሮች አንዱ ከሌላው ጋር ከሚኖራቸው ቁርኝት ባሻገር በራሳቸው ምሉዕ ናቸው፡፡ አንድ ድርጊት እና ክንውን ሲጠናቀቅ፣ ሆኖም ተከታይ ነገር ሲኖረው የሚደመደሙ ናቸው፡፡ ደበበ (1973፣26) እንደሚለውም የገቢር ለውጥ ከምሉዕነት ውጪ በሆነ መልኩ ከተመልካቾች እይታ "ድንገት ቁርጥ ብሎ ወይ ምነው! እሚያሰኛቸው አይነት መሆን የለበትም"

የአንድ ተውኔት ገቢር አንድና ከአንድ በላይ ቢሆንም መጨረሻው በጣም ውስን ነው፡፡ እንዳሻን አስር እና ሀያ ገቢሮችን በአንድ ተውኔት ውስጥ መደርደር አንችልም፡፡ ቢሆንም የገቢር ብዛት እንደተውኔቱ ሴራ እና እንደታሪኩ አረማመድ የሚወሰን ቢሆንም በየዘመናቱ የተነሱ የተውኔት ልማዶች በገቢር ቁጥር ብዛት ረገድ የራሳቸውን ተጽእኖ አሳድረዋል፡፡ ለምሳሌ ፋንታሁን እንግዳ (2001፣167-168) እንደሚጠቀሰው

“በኤልሳቤጣዊያን ዘመን አንድ የሙሉ ጊዜ ተውኔት በአምስት ገቢሮች መከፋፈሉ እየተለመደ” የመጣ ቢሆን “በምንገኝበት ዘመን ያሉ ጸሃፊ - ተውኔቶች ግን አዘውትረው ባለሁለት ገቢር እና ባለሶስት ገቢር ተውኔቶችን ይጽፋሉ”

ከዚህ በታች አይነ - ሞራ ከተሰኘው የፋንታሁን እንግዳ (1998፣ 9 እና 25-26) ጊዜ ተውኔት ሁለት ገቢሮች የተወሰዱ፣ የገቢሮቹ መጀመሪያ ሁለት የመቼት ገለጻዎች አሉ፡፡ እነዚህን የመቼት ገለጻዎች በማየት ገቢሩ የተለያየው በምን ለውጥ እንደሆነ አስረዳ

-1-

> የችሎቱ አዳራሽ የመጨረሻ ፍርድ በሚበየንላቸውና በሚበየንባቸው ቤተ - ዘመዶችና ሌሎች ተመልካቾች ተሞልቷል፡፡ ጉዳያቸው በተራቸው መሰረት ለመሃል ዳኛው እንደቀረበ ባለጉዳዩ ከፍ ባለ ድምጽ ተጠርቶ ተራው የሱ መሆኑ ይነገረዋል፡፡ አሁን የተገለጠው ፋይል የወይዘሮ አቲና ተርዚያን ነው፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ግለሰቦች የአዳራሹን መሃል እየሰነጠቁ በመግባት ከዳኞች ፊት በግራና በቀኝ ይቆማሉ፡፡

-2-

> የወይዘሮ አቲና ተርዚያን ቤት በጣሊያን ወረራና ከዚያም ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ግሪኮችና አርመኖች አዘውትረው ይሰሯቸው የነበሩትን የመኖሪያ ቤቶች የአሰራር ቅርጽ የተከተለ ነው፡፡ ቤቱ ሶስት ትውልዶች ተፈራርቀውበታል፡፡ በአጭሩ ቤቱ ዕድሜያማ ሲሆን በየጊዜው በእርጅና ምክንያት እንዳይፈርስ ዕድሳት ተደርጎለታል፡፡ ቤቱ የሰውን መንፈስ የመጫን ድባብ ይነበብበታል፡፡የቤቱ አሰራር ከእንጨት ሆኖ የምድርና የፎቅ ክፍሎች አሉት፡፡ ፊት ለፊት የሚታየው ሳሎን ሲሆን ዘመን አመጣሽ ሶፋ ወንበርና ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ቴሌቪዥንን ጨምሮ ይዟል፡፡ ከሳሎኑ ጀርባ ራቅ ራቅ ብለው የተሰሩ የመኝታ ክፍሎች መግቢያ በሮች ተዘግተው ይታያሉ፡፡በዚያው በሳሎኑ አንድ ጎን ወደፎቅ የሚያስወጣው ደረጃ ወደ ፎቅ ያወጣንና ወደመታጠቢያ ቤት እንዲሁም ወደ እንግዳ ማደሪያ ክፍል ይወስደናል፡፡ ፎቁ ቁጭ ብሎ አየር መቀበያና መነጋገሪያ እንዲሆን የተሰራ መናፈሻ በረንዳ አለው፡፡የእስር አለቃ ወደፎቁ ከሚያስወጣውና ከሚያስወርደው ደረጃ ጀምረው ወደ ሳሎኑ ያለውን ሲጠርጉ ቆይተው መልሰው ይወለውላሉ፡፡ ወይዘሮ አቲናና ነገረፈጅዋ አቶ አንተነህ ደግሞ ከሳሎኑ ውስጥ ተቀምጠው ንግግር ይዘዋል፡፡

## 4.3. ትዕይንት

ትዕይንት በገቢር ውስጥ የሚገኙ የአንድ ተውኔት ንኡሳን ክፍሎች ናቸው፡፡ ባለአንድ ገቢርም ሆነ ባለአምስት ገቢር ተውኔቶች ውስጥ ትዕይንቶች ይኖራሉ፡፡ ገቢር ከላይ በስፋት እንዳየነው ሰፊ የአንድ ተውኔት ክፍል ሲሆን፣ ትዕይንቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ንዑሳን ክፍሎች ናቸው፡፡

በትዕይንቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች በገቢር መካከል እንዳሉ ልዩነቶች የጊዜና የቦታን ለውጥ አይፈልጉም፡፡ የጊዜና የቦታ ለውጥ ሳይከሰት ወይም የቦታ ለውጥ ሳይኖር በጊዜ ለውጥ ላይ ብቻ በመመስረት የትዕይንት ለውጥ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን በአንድ ትዕይንት እና በሌላ ትዕይንት መካከል የየራስ ምሉዕነት አይታይም ማለት አይደለም፡፡ እንደገቢር የጠበቀ ባይሆንም እያንዳንዱ ትዕይንት የራሱ ባህሪ እና ከሌላው ትዕይንት ጋር ደግሞ እጅጉን የጠበቀ ትስስር ይኖረዋል፡፡

ደበበ (1973፣25) እንደሚለው "ትዕይንቶች መጋረጃዎች ሳይጣሉ፣ የተደራሲያኑም አይኖች ከመድረኩ ላይ ሳይነቀሉ ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡" ይህም የሚሆነው ብዙውን ጊዜ የቦታ ለውጦች ስለማይኖሩ የአልባሳት፣ የቁሳቁሶች እና መሰል ከፍተኛ እንቅስቃሴን የሚጠይቁ ለውጦች ስለማይኖሩ ነው፡፡ በማጥፋትና በማብራት የትዕይንት ለውጥ አነስተኛ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ በመሆኑ መጋረጃ ሳይጣል የትዕይንት ለውጥ ማምጣት የሚቻል ሲሆን እንደተውኔቱ ዘልማድ ግን መጋረጃ ሊጣል የሚችልበት አጋጣሚ እንደሚኖር መረዳት ይገባል፡፡ ከዚህም ባሻገር በፈረንሳይ እና በእንግሊዝ የተውኔት ሃያሲያን ንደፈ ሀሳብ መሰረት የትዕይንት ለውጥ በተለያየ መልኩ ሊከሰት ይችላል፡፡ የፈረንሳይ ንድፈ ሀሳብውያን የትዕይንት ለውጥ መጣ ብለው የሚያምኑት ታሪኩ ተጨማሪ ገጸ ባህሪያት በተውኔት ታሪኩ ተሳታፊ ሆነው ሲገቡ ወይም ሲወጡ ነው፡፡ እንግሊዛውያኑ ደግሞ ይህን አይቀበሉትም እንደነሱ አመለካከት የትዕይንት ለውጥ የሚመጣው በመድረኩ ላይ ያለው ክንዋኔ አልቆ ሌላ ትዕይንት ለማስተናገድ መድረኩ ባዶ ሲሆን ነው (ፋንታሁን 2001-85-86)፡፡

ትዕይንት በተለያዩ ወገኖች በልዩ ልዩ ለውጦች መንስኤ የሚፈጠር የገቢር ንዑስ ክፍል ተደርጎ ቢወሰድም በዋነኛነት በራሱ ምሉዕ እንደሆነ ግን ይታሰባል፡፡ ከዚህ በዘለለ በአንዱና በሌላው ትዕይንት መካከል የተጠባባቂነት ባሕሪ ያለ በመሆኑ አንዱ ከሌላው ጋር ያለው ቁርኝት ጥብቅ ነው፡፡

ትዕይንት በአንድ ተውኔት ውስጥ ቁጥሩ የተገደበ አይደለም የተውኔት ገቢሮች በበዙ ቁጥር የትዕይንት ቁጥሮችም በዛው መልክ የመብዛት ባህሪ ቢኖራቸውም ከተውኔት የቁጥብነት ባህሪ የተነሳ በርካታ ትዕይንቶች በአንድ ተውኔት ውስጥ ማስተናገዱ አይመከርም፡፡

ቀደም ሲል ከፋንታሁን እንግዳ አይነ — ሞራ ተውኔት ሁለት ገቢሮችን የሚያመለክቱ የመቼት መግለጫዎች መቅረባቸውን ላስታውስህ ሁለተኛውና የወይዘሮ አቲና ተርዚያን መኖሪያ ቤትን የያዘውን የመቼት መግለጫ አስታወስክ? ጥሩ ቀጣዩቹ የመቼት መግለጫዎች እሱን የተከተሉ ናቸው፡፡ ለማያያዝ 3 እና 4 ብለን ርዕስ እንስጣቸው፡፡ እነዚህ የሶስተኛው አራተኛው የመቼት መግለጫዎች ከተራ ቁጥር 1 እና 2 ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድነው? በሌላ አገላለጽ 1 እና 3 ወይም 4 የገቢር ልዩነቶች ናቸው ወይስ የትዕይንት? ይህንን ገለጻ በማንበብ ከቀድሞው ጋር አነጻጽረህ መልስ፡፡

-3-

ቦታው --- በዚያው በወ/ሮ አቲና ሳሎን ነው፡፡ ሲሳይና አቲና ብቻቸውን የሳሎንን ክፍል በስፋት ይዘው ተቀምጠውበታል፡፡ ሲሳይ የሌሊት ፒጃማውን እንደለበሰ ነው፡፡ (1998:38)

ቦታው --- በወይዘሮ አቲና ቤት ሳሎን ውስጥ ነው፡፡ ሰዓቱ ከከሲያት ወደምሽት አዛብታል፡፡ ወይዘሮ አቲና እንደማንኛውም ቀን ሁሉ ወደቤታ የምትገባው ምሽት ላይ ነው፡፡ መብራት እንደበራ በሳሎን ውስጥ አይናችን የሚያርፈው ሶስት ሰዎች ላይ ነው፡፡ ከአስር አለቃ ከፈለኝ፤ ከአቶ ሲሳይና ከአሰር አለቃ በላይ፡፡
አቶ ሲሳይ እጁ ከእግሩ — ጉልበቱ ከአገነቱ ጋር ተያይዞ ታስሮ ወለሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ የአስር አለቃ ከፈለኝ በምርመራ ወቅት የሚለብሱትን ከአይን በስተቀር ሌላውን ሰውነታቸውን የሚሸፍነውን ቱታ መሰለ ልብስ ለብሰው መንታ አለንጋቸውን ጨብጠው እያወናጨፉ ይንጎራደዳሉ (1998:51)

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የሚከተሉትን የማገናዘቢያ ነጥቦች በመመርመር በምታውቀው ላይ የ (√) ምልክት አድርግ። በማታውቀው ላይ ደግሞ የ (×) ምልክት አድርግና ነጥቡን ወደኃላ ተመልሰህ አንብበው።

- ስለገቢር ምንነት መግለጽ እችላለሁ----------------------------------------▢
- ተውኔት በገቢር ስለሚከፈልበት ምክንያት ማብራራት እችላለሁ ------▢
- ስለትዕይንት ምንነት መግለጽ እችላለሁ ------------------------------------▢
- በገቢር እና በትዕይንት መካከል ያለውን ልዩነት ማብራራት እችላለሁ -▢
- በየዘመኑ ተውኔቶች በገቢር የሚከፋፈሉባቸውን መጠኖች መግለጽ እችላለሁ ----▢

## ግለ ፈተና - አራት

የሚከተሉትን ጥያቆዎች ካነብብክ በኃላ ትክክለኛ ሀሳብ የያዙትን "አውነት" ሀሰተኛ ሀሳብ የያዙትን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ።

_____1. ተውኔቶች ከ10 ትዕይንት በላይ ሊይዙ አይገባም

_____2. በዚህ ዘመን ተውኔቶችን ከ5 — 7 ባሉ ገቢሮች መከፋፈል የተለመደ ነው።

____ 3. ትዕይንት በገቢር ውስጥ ያለ ክፍል ነው።

____ 4. የጊዜና የቦታ ለውጥ ተውኔቱ ተጨማሪ ትዕይንት ብቻ እንዲጨምር ያስገድደዋል።

___ 5. ባለአንድ ገቢር ተውኔት ሊኖር ይችላል።

___ 6. በተውኔት ውስጥ መጋረጃን ደጋግሞ መጣል የተውኔቱን ታሪክ በአግባቡ ለመከታተል እንቅፋት ይፍጥራል።

# ምዕራፍ አምስት

## የተውኔት ዘውጐች

### መግቢያ

ዘወግ የስነፅሁፍ ስራዎች በጋራ በሚኖራቸው ጭብጥ ወይም አወቃቀር ባህሪ አንፃር የሚገለፅ ቃል ነው፡፡ ስነፅሁፍን በዘውግ  መክፈል የተጀመረውም አሪስቶትል ፖለቲክስ በተባለው ስራዉ ስነፅሁፍን ትራጀዲ ፣ ኤፒክ እና ኮሜዲ ብሎ ከከፋፈለና መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶችን በድራማ፣ በኤፒክና በሊሪክ ፖይትሪ መካከል ካስቀመጠ በኂላ ነው፡፡ እኛም በዚህ ምዕራፍ የተለያዩ የተውኔት አይነቶችን እንመለከታለን፡፡ ወደ ምዕራፍ ከመዝለቃችን በፊት እስቲ እናንተ የሚከተሉትን ጥያቄዋች መልሱ፡፡

> ተውኔቶች ሲከፈሉ መሰረት የሚደረጉ ነገሮች ምን ምን ይመስሏችኂል፡፡
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………………………………
> ……………………………………………………………

ውድ ተማሪዎች ተውኔትን በአይነት በአይነት ስንፈረጅ መሰረት የሞናደርገው ቅርፅን ፣ ጭብጡንና ድባቡን በማየት ነው ካላችሁ ትክክል ናችሁ፡፡ እነዚህን ነጥቦች አድርገን ስንከፋፈልም በጣም በርካታ የሆኑ የተውኔት አይነቶችን እናገኛለን፡፡

ለምሳሌ ቅርፅን መሰረት አድርገን ስንከፋፈል የምናተኩረው የሚቀርብበትን መድረክ ፣ ተደራሲያችንን ፣ እና የሚቀርብበትን መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ ከቅርፅ አንፃር ተውኔትን በዚህ መንገድ ልንከፋፍለው  እንችላለን፡፡

- የመድረክ ተውኔት ፣ የሬዲዮ ተውኔት ፣ የንባብ ተውኔት ፣ የቴሌቭዥን ተውኔት
- የህፃናት ተውኔት ፤ የአዋቂዎች
- ሙዚቃዊ ተውኔት ፣ ድምፅ አልባ ተውኔት ፣ ግጥማዊ ተውኔት
- ባለአንድ ገበር ተውኔት ፣ የሙሉ ጊዜ ተውኔት ፣ ባለአንድ ገፀባህሪ ተውኔት ወዘተ…

ጭብጥን ወይም ተውኔቱ  ይዞት የተነሳውን ማዕከላዊ ሐሳብ መሰረት አድርገንም ተውኔትን ታሪካዊ ተውኔት ፣ ግብረገባዊ ተውኔት ፣ ታምራዊ ተዉኔት ፣ ሃይማኖታዊ ፣ ፖለቲክዊ ወዘተ… ብለን መከፋፈል እንችላለን፡፡ ውድ ተማሪዎች የኛ ትምህርት ትኩረት ተውኔቶች የሚፃፉበትን ድባብ መሰረት አድርገን ስንከፋፈል የምናገኛቸው የተውኔት አይነቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ የተውኔት አይነቶች በተለያዩ ምሁራንና የትያትር ጥናቶች በተደጋጋሚ የሚነሱ ሲሆኑ ትራጅዲ ፣ ኮሜዲ ፣ ድንቃይና ቧልታይ ይባላሉ፡፡

## 1 ትራጀዲ (መሪር) ተውኔት

ውድ ተማሪዎች ወደ ትምህርታቸውን ከመግባታችን በፊት የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡

| |
|---|
| ትራጀዲ ምንድ ነው? |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------ |

በጣም ጥሩ፡፡ አሁን ደግሞ የእኔን ላስፍር

ትራጀዲ በጣም ጥንታዊ የሆነና በ6 መ.ክ.ዘ በግሪኮች የተፈጠረ ነው፡፡ ትራጀዲ የሚለውን ቃል በቀጥታ የፍየል ዘፈን (goat song) የሚል ትርጓሜ ሲኖረው ይህም ዳይኖሲየስ ለተባለው ጣኦት መስዋት ፍየል ይቀርብለት ስለነበርና ከዚህ ተግባር ጋር በተያያዘ የተሰጠ ስያሜ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ከዚያም ትራጀዲ በጣም ጠንካራና አሳሳቢ የሆኑ ከሰው ልጆች ህልውና ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በሚያነሱ ገፀባህሪዎች ድራማዊ በሆነ መንገድ መቅረብ ጀመረ፡፡ ስለ ትራጀዲ ዘሪሁን አስፋው (1996 ፣ 277) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> የትራጀዲ ታሪክ አሳሳቢ በመሆኑና በማህበረሰቡ ትልቅ ግምት በሚሰጣቸው ጉዳዩች ላይ ይመሰረታል፡፡ በታሪኩ ውስጥ የሚፈፀሙት አበይት ድርጊቶች ማህበረሰቡን የሚነኩና ዘላቂነት ያላቸው ናቸው፡፡ በሰዎች ዘንድ ሊደርሱ የሚችሉ ከፍተኛና ላቅ ያለ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ አሳሳቢነታቸው ከፍ ያለ በመሆኑና የሁሉም ጉዳይ ስለሚሆን በሰዎች ስሜትም ላይ የሚያስከትሉት ተፅእኖ ከባድና አስጨናቂ ይሆናል፡፡ የሰውን ስሜት ጨቁነው በፍርሃትና በሰቀቀን እንዲዋጥ ያደርጋሉ፡፡ የተረጋጋ ህይወትን የሚያናጉ ሰላማዊውን እንቅስቃሴውን በሽብር የሚሞሉ ናቸው፡፡ እንዲህ በመሆናቸውም በተመልካቹ ላይ የሚጥሉት ድባብ የፍርሃት ፣ የሰቀቀንና የጭንቀት ነው፡፡ (1973 ፣ 47)

ደበበ ሰይፉም ትራጀዲን በተመለከተ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> ማንኛውም ትራጀዲ የያዘው ቁምነገር (ሐሳብ) እጅግ ሰፊና የሰው ልጅን መሰረታዊ እና አሳሳቢ ጥያቄዎች (እንደ የኹይነት የኑረት ጥያቄዎች ዓይነት) ያካተተ ነው፡፡ ትራጀዲያዊ ገፀባህሪያት በገዛ ችግሮቻቸው ብቻ እሚናወዙ ፣ ለገዛ ችግሮቻቸው ብቻ መፍትሄ እሚፈልጉ አይደሉም፡፡ ምንም መጠኑ ቢለያይም ÷ ችግሮቻቸውን እሚያስተውሉት ከፍ አድርገው ነው - ሌሎችንም እንደሚጠቁም ÷ እንደሚቀነብብ አድርገው፡፡ አርቀው ነው - የጊዜንና የቦታን ድንበር እንደሚዘል አድርገው፡፡

ከነዚህ ትንታኔዎች የምንረዳዉ ትራጀዲ ድባቡ ጭፍን የሆነ፣ የሰውን ልቦና የሚያሳዝን ፣ልብ የሚሰብር ፣ የሚያሳቅቅ ፣ ፍርሃት የሚያጭር ፣ ዘግናኝና አስበርጋጊ መንፈስን የሚዘራ መሆኑን ነው፡፡ በትራጀዲ ተውኔት ውስጥ የሚቀርበው ታሪክ መሰረታዊ የሆነ የሰው ልጆችን ችግር የሚያነሳ ፣ ግራ አጋቢና መፍትሄ በሌላቸው ጉዳዮች ውስጥ ገፀባህርያቱን የሚዘፍቅ በመሆኑ ፣ በየትኛውም ጊዜና ዘመን በሚገኙ ሰዎች ባህሪ ላይ የሚቀነበብ በመሆኑ ዘመን ተሻግሮ የመደመጥ ዘላቂነት አለው፡

## 5.1 የትራጀዲ ባህሪያት

ውድ ተማሪዎች ስለትራጀዲ ተውኔት ምንነት በደንብ እንደተገነዘባችሁ እርግጠኛ ነን፡፡ ከዚህ በመቀጠል የትራጀዲ ተውኔት ባህርያትን እንመለከታለን፡፡ ወደ ትምህርታችን ከመግባታችን በፊት እስቲ የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ፡፡

| |
|---|
| ትራጀዲ ተውኔት ምን የተለዩ ባህሪያት አሉት? |
| ……………………………………………………………………………………… |
| ……………………………………………………………………………………… |
| ……………………………………………………………………………………… |
| ………. |

በጣም ጥሩ እስቲ እኛ ደግሞ የሚከተለውን እንበል፡፡

- ❖ ትራጀዲ በሰው ልጅ ህይወት ፣ ሞራል ፤ ስነልቦናና ማህበራዊ ግንኙነት ላይ የተመሰረቱ ፈታኝ ሃሳቦች ይነሱበታል፡፡
- ❖ አቀንቃኙ ገፀባህሪ መልካም ምግባር ያለው ሰው ነው ሆኖም አንድ አይነት ግድፈት ያለበት ሊሆን ይገባል ፤ ግድፈቱም ለግጭቱ መፈጠርና ለሽንፈቱ ምክንያት ይሆናል፡፡
- ❖ ይህ እንከን ከአጠቃላይ የገፀባህሪው ባህሪ አኳያ እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም ገፀባህሪውን ከማይወጣበት አዘቅት ውስጥ ይጥላል፡፡
- ❖ የአቀንቃኝ ገፀባህሪ እድል ከአስደሳች ወደ አሳዛኝ ገጠመኝ ተቀይሮ ተመልካቹን በስሜት እያሰመጠ ከተንዠ በኋላ በመደምደሚያው ላይ በተመልካቾች ዘንድ አስፈሪና አስደንጋጭ ትዝታ በመፍጠር ይፈፀማል፡፡
- ❖ በትራጀዲውስጥ እርቅ የለም፡፡ ሁልጊዜ አሸናፊና ተሸናፊ አለ፡፡
- ❖ ጭብጡ በዘመናት ብዛት አይሻርም ዘላቂ ነው፡፡

## 5.1.2 የትራጀዲ አይነቶች

ውድ ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ይዘት ከመዝለቃችን በፊት የሚከተለውን ጥያቄ መልሱ

| |
|---|
| የትራጀዲ ተውኔት አይነቶች ምን እና ምን ናቸው? |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------------------------------------------------------------------------ |
| ------------------------------ |

በጣም ጥሩ፡፡ ትራጀዲ ጥንታዊ ፣ ኤልሳቤጣዊና ዘመናዊ በመባል በሶት ይከፈላል፡፡

### ሀ. <u>ጥንታዊ ትራጀዲ</u>

በጥንትዊ ትራጀዲ ዋናው ገፀባህሪ ጀግና እና የላይኛው መደብ አባል ነው፡፡ ታሪኩ አንድ ሲሆን ሴራው ምሉእነት የሚታይበት መጀመሪያ ፣ መሀከልና መጨረሻ ያለው ነው፡፡ እንደ ታሪኩ ሁሉ ሴራውም ነጠላ ነው፡፡ በጥንታዊ ትራጀዲ አሰቃቂ ክንውኖች መድረክ ጀርባ ይፈፀማሉ፡፡ ቋንቋው የመጠቀ ሲሆን በግጥም መልክ ይቀርባል፡፡ ታሪኩ ተረታማነት ይበዛበታል፡፡ ገፀባህሪው ችግሩን ቶሎ ለመፍታት ይጥራል ግን ዕድሉማ

በአማልክት ወይም በእጣፈንታ ይወሰናል፡፡ ዋናው ገፀባህሪ ቅስሙ ተሰብሮ እንዲኖር ይደረጋል እንጂ አይሞትም፡፡

**ለ. <u>ኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ</u>**

ዋናው ገፀባህሪ እንደጥንታዊ ትራጀዲ ሁሉ ጀግናና የላይኛው መደብ አባል ነው፡፡ ኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ከጥንታዊ ትራጀዲ የሚለይበት ዋንኛ ጉዳይ ሴራ ነው፡፡ የጥንታዊ ትራጀዲ ሴራ ጥብቅና ነጠላ ነው፡፡ ኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ግን ብዙ ጊዜ ሴራው ልልና ድርበ ነው፡፡ ድምር ሴራ ላይ ይመሰረታል፡፡ በሴራዉ መጨረሻ በጥንታዊ ትራጀዲ ዋናው ገፀባህሪ ውድቀት ይገጥመዋል እንጂ አይሞትም በኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ግን በሴራው መጨረሻ ወይም ልቀቱ ላይ ገፀባህሪው ይሞታል፡፡

በኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ከጥንታዊ ትራጀዲ በተቃራኒ አሰቃቂ ነገሮች መድረክ ላይ ይፈፀማሉ፡፡ ገፀባህሪ መድረክ ላይ ሊሞት ፣ በጐራዴ ሊቆረጥ ፤ በመርዝ ሊገደል .. ወዘተ ይችላል፡፡ ኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ከተረታማነት ይልቅ ምናባዊነትና ሰብአዊነት አለው፡፡ ብዙ ጊዜም ታሪኩ በበቀል ላይ ይመሰረታል፡፡ ዋናው ገፀባህሪ በኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ብዙ ጊዜ ይሞታል፡

እንደጥንታዊ ትራጀዲ ፍፁም አስጨናቂ አይደለም በመሃከል ተደራሲውን ዘና የሚያደርጉ ኮሚክ እፎይታዎች ይገኛሉ፡፡ እንደጥንታዊ ትራጀዲ ቋንቋው የመጠቀ ሲሆን በግጥም ይቀርባል፡፡

**ሐ. <u>ዘመናዊ ትራጀዲ</u>**

ከሁለቱ የትራጀዲ አይነቶች በተቃራኒ ዋናው ገፀባህሪ ከተራዉ ወይም ከታችኛው መደብ ይቀረፃል፡፡ ወጥ የሆነ ሴራ የለውም፤ ድምር ሴራ ላይ ይመሰረታል፡፡ ከተረታማነት ይልቅ ምናባዊነትና ሰብአዊነት አለው፡፡ ብዙ ጊዜ ታሪኩ በስነልቦናዊ ቀውስ ላይ ይመሰረታል፡፡ አሰቃቂ ክንውኖች በመድረክ ላይ ይፈፀማሉ፡፡ ቋንቋው ዝውውርና ተራ ነው፡፡ ዋናው ገፀባህሪ ብዙ ጊዜ ይሞታል፡፡

## 2. ኮሜዲ (ኢ- መሪር፣ፍግ) ተውኔት

ኮሜዲ መንፈስን የማይጨነቁን ፣ የማይጫን ተውኔት ነው፡፡ በኮሜዲ እየተዝናናን ፣ እየተፍነከነክን ስለ ህይወት ብዙ እንማራለን፡፡ ብዙ ጊዜ በኮሜዲ ልማዳዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ይነሳሉ፡፡ ኮሜዲን በተመለከተ ፍንታሁን እንግዳ (1993 ፣ 70) “የሰውን ልጅ ማህበራዊ ወይም ግላዊ ህፀፅን እና አመልን እየተቸ ፣ እየነቀፈ ፣ እያሽሟጠጠ ለማረም ወይም ለማስተካከል የሚሞክር አስቂኝ የተውኔት ዘውግ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ ኮሜዲ ቁም ነገር የሚተላለፍበት የተውኔት አይነት ነው፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሚታዩ ማህበራዊ ድክመቶች ላይ ይመለከታል፡፡ ድክመቶቹ የሚቀረፍበትን መንገድ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

በኮሜዲ ግጭቶች ይፈጠራሉ ግን ምንግዜም እርቅ አለ፡፡ እርቁም በማንም ጥፋት (ውድቀት) የሚመጣ አይደለም፡፡ ኮሜዲ ቁምነገር የሚተላለፍበት የተውኔት አይነት ስለሆነ ፀሐፊ ተውኔቱ ከትራጀዲ ይልቅ ጥቅቃቄ ሊያደርግበት የሚገባና ከፍተኛ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በህብረተሰቡ ልማዳዊ ጉድለት ላይ እየተሳለቀ በዚህ ውስጥ ቁም ነገር ያስተላልፋል፡፡ ተደራሲው በዚህ በፌዝ በታጀበው መልዕክት ውስጥ ያለውን

ቁምነገር ፈልቅቆ ማውጣት ስለሚጠበቅበት ደራሲው እሚያስተላልፈው ጉዳይ በፌዝ እንዳይዋጥ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኮሜዲ ተውኔት ውስጥ እንደ ትራጀዲው ስርመሰረቱ የተናጋ ዓለም ስለማያጋጥም እና ግራ የሚያጋቡና መፍትሄ የሌላቸው የሚመስሉ የሚያስጨንቁ ችግሮች ስለማይቀርቡ ተደራሲው ትያትሩን የሚመለከተው ዘና ብሎ ነው፡፡ ኮሜዲ ብዙውን ጊዜ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ባሉ ወጎች ፣ ልምዶችና ባህሎች ላይ ስለሚያተኩር እነዚህ ወጎች ልምዶችና ባህሎች ደግሞ ቋሚ ሆነው ባለመዝለቃቸውና የስርዓት ለውጥ ሲያጋጥም አብረው በመለወጣቸውና በሌሎች ወጎች ልምዶችና ባህሎች በመተካታቸው መጀመሪያ ከታየበት ዘመንና ስፍራ ውጭ ሲቀርቡ ያላቸው ተሰሚነት እንደ ትራጀዲ አይጎላም፡፡ በተለያየ የዘመንና የቦታ መድረኮች ቀርበው የመጀመሪያ መልዕክታቸውን ማስተላለፍም አይችሉም፡፡ ኮሜዲ ቋንቋው እንደትራጀዲ ተውኔት የረቀቀና የመጠቀ አይደለም፡፡ ግልፅና ተራ ቋንቋን ይጠቀማል፤ በአብዛኛው የሚጠቀመው የስድ ወይም የሃተታ ፅሁፍን ነው፡፡

## 4. ባልታይ (ፋርስ) ተውኔት

ባልታይ ተውኔት አላማው ሳቅ ማጫር ነው፡፡ ይህ የተውኔት አይነት ሳቅ ለማጫር ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮችን ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ብዙ ጊዜ ገፀባህርያቱን ጅላጅል ስለሚያደርጓቸው ተደራሲውን ያዝናናሉ፡፡ የገፀባህሪያት ንግግር፣ አለባበስ ፣ ሳል ፣ ጩኸት ወ.ዘ.ተ … ሳቅ ያጭራሉ፡፡ ይህንን በተመለከተ ደበበ ሰይፉ (1973 ፣ 58) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> የባልታይ ተውኔት ዓላማው ÷ በሆነው ዘዴ ሳቅን መፍጠር ነው፡፡ በሆነው ዘዴ ሳቅን ለመፍጠር በመፈለጉ የገፀባህሪያት መታመን ወይ ጥልቀት ወይ የቃል ተውኔት ከገፀባህሪያትና ከሁኔታ ጋር መስማማት ለሚባሉት የተወኔት አፃፃፍ ሕግጋት አይገዛም፡፡ ከቶውንም ለብዙዎቹ የተውኔት አላባውያን መቀናበርና መልክ መያዝ ግድ የሌለው የተውኔት አይነት ነው፡፡

ውድ ተማሪዎች ባልታይ ተውኔት የማያስጨንቅ ግን የሚያስፈግግ ፣ የሚያዝናና ድባብ ያለው ሳቅ የገነነበት የተውኔት አይነት ነው፡፡ የሚቀርቡትም ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎች የተጋነኑ ናቸው፡፡ የማዝናናት የማስደሰት ባህሪው ከኮሜዲ ተውኔት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ሆኖም ሳቅ የማጫር አቅሙ ከኮሜዲ ተውኔት የላቀ ነው፡፡ የተውኔቱ ዋና አላማ ሳቅን መፍጠር በመሆኑ ድርጊቶች በፍጥነት ይከናወኑበታል፡፡ ያልተጠበቁ ክስተቶችና ድንገተኛ የሆኑ ድርጊቶች እንዲሁም ተደጋጋሚ የሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴዎች በመድረክ ይቀርባሉ፡፡ ገጸ ባህሪያቱ በአመዛኙ የሚገቡበት ግጭትም ቢሆን አካላዊ ነው፡፡ ገጸ ባህሪያቱም የሚያሳስቡ ጥያቄዎች ፣ የሚያስጨንቁ ሁኔታዎች አይገጥሟቸውም፡፡ ድርጊቶቻቸውም ቢሆኑ የሳቢያና የውጤት ጥያቄ የሚነሳባቸው አይደሉም፡፡ ሳቅን ለመፍጠር የሚከታተሉ ድርጊቶችና የሚፈጠሩ ሁኔታዎች ይበዙበታል፡፡ በአጠቃላይ በመድረኩ ትርምስ ይስተናገድበታል፡፡ ታዳሚውም ከድርጊቶቹ ፍጥነት የተነሳ የሚቀርበውን ነገር ለማስላሰል ፋታ አያገኝም፡፡ ዘሪሁን (1992፣ 276) ይህን ሲገልጽ

> በተውኔት ውስጥ ገጸ ባህሪያት እርስ በርስ ሲጣሉ ፣ ሲደባደቡ ከግድግዳ ጋር ሲላተሙ ዕቃ ሲሰብሩ ወንበር ጠረጴዛውን ሲያጋጩ በትእይንቱ ውስጥ ያለውን ቁሳቁስ ሲያተራምሱ

> ይታያሉ፡፡ ገፀባህሪያት ለማመን የሚያስቸግሩ ሁነቶች ውስጥ በመግባት ለማመን የሚያስቸግሩ ድርጊቶች ይፈፅማሉ፡፡ ገጸ ባህሪያቱ የለመድናቸው ሰዎች ናቸው፤ እንግዳ የሚሆንብን የሚፈጽሙት ድርጊት ነው፡፡

የቧልታይ ተውኔት ለተውኔት አላባውያን የማይገዛበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ ተውኔቱ ያለቃለ ተውኔት ሊዘጋጅ ይችላል፡፡ በገፀባህርያቱ ድርጊት እንቅስቃሴና ሁኔታ ብቻ ሳቅን መፍጠር ይችላል፡፡ "የቧልታይ ተውኔት ገፀ ባህሪያት ከቶም ቃለ ተወኔት የማያስፈልጋቸው ጊዜ አለ፡፡ በክዋኔዎቻቸው ብቻ የሳቅ መድረክ እሚፈጥሩበት ጊዜ ሞልቷል፡፡ የቻርሊን በእንቅስቃሴ በክዋኔ ብቻ እሚካሄድ ቃለ ተውኔት አልባ የሆነ ቧልታይ ተውኔት ብጤ በፊልም ተቀርጾ ያየን ብዙ ሳንሆን አንቀርም፡፡" (ደበበ 1973፣59) በቧልታይ ተውኔት ልክ እንደ ድንቃይ ተውኔት ሁሉ ከፀሐፊ ተውኔቱ ችሎታ ይልቅ የተዋንያኑ ችሎታ ተውኔቱን የተዋጣ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

<u>የቧልታይ ተውኔት ባህሪያት</u>

- ✓ ገጸ ባህሪያቱ በቀላሉ የሚለዩ ውስብስብነት የሌላቸው አስተኔ ናቸው፡፡
- ✓ ገጸ ባህሪያት የተጋነኑ ሁኔታዎች ውስጥ ይገባሉ፡፡
- ✓ ሴራው የተዋጣ አይደለም ፤ ለሳቢያና ውጤት ስምረት አይጨነቅም፡፡
- ✓ ድርጊቶች በፍጥነት ይከናወኑበታል፡፡

## 5. ድንቃይ ተውኔት

ድንቃይ ተውኔት የኢ-መሪር እና የመሪር እንዲሁም የቧልታይ ተውኔት ቅይጥ ነው፡፡ ከ19ኛው ክ.ዘ በኋላ እየተዘወተረ የመጣ ተውኔት ነው፡፡ አላማውም ስነምግባርን ማስተማር ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ደበበ ሰይፉ (1973 ፣ 60) የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> ድንቃይ ÷ ክንዋኔዋች እሚበዙበት ÷ እራሮት እሚገንበት አስተኔ ገፀባህሪያት እሚስፍኑበት ተውኔት ነው፡፡ ይህ የተውኔት ዓይነት ክንዋኔዎች ስለሚበዙበት አስተኔ ገፀ ባህሪያት ስለሚስፍኒበት ከቧልታይ ተውኔት ጋር ይመሳሰላል፡፡ " ሁሉም የየጁን አገኘ" በሚል ሁኔታም ስለሚፈፀም ከኮሜዲ ተውኔት ጋር ይቀራረባል፡፡ ከኮሜዲና ከቧልታይ ተውኔቶች ድባብ ይልቅ የድንቃይ ድባብ መንፈስን ጨቆን ስለሚያደርግ ከትራጅዲ ተውኔት ጋር የሚቀራረብበት ምክንያትም አለው፡፡

በድንቃይ ተውኔት በማህበረሰቡ ገናን የተባሉ እሴቶች ይቀርባሉ ፤ ጥሩና መጥፎ ፤ ሰናይና እኩይ ባህሪያት ለንፅፅር ስለሚቀርብበትም ብዙ ጊዜ ይህ ተውኔት ለኘሮፖጋንዳ ስራ አመቺ ነው፡፡

<u>የድንቃይ ተውኔት ባህሪያት</u>

- ✓ የተዋጣ ሴራና ገፀባህሪያት አይቀርጽም፡፡
- ✓ በድርጊያ የተሞላ በመሆኑ ከጸሀፊ ተውኔቱ ችሎታ ይልቅ የተዋናንያን ብቃት ይጠይቃል፡፡
- ✓ የገጸ ባህሪያቱ ድርጊትና ሐሳብ በተጠይቃዊነትና በምክንያታዊነት የተሳሰረ አይደለም፡፡
- ✓ ገጸ ባህሪያቱ ውስብስብ ህሊናዊ መልክ እንዲግራቸው ተደርገው አይሳሉም፡፡
- ✓ ከመጠን ባለፉ ድርጉቶች ፣ እምቢ ባይነትንና ልዩ ሀይልን በመጠቀም ተደራሲን በፍርሃት ፣ በእልህና በውጥረት እንዲዘፈቅ የሚደርግ ባህሪ አለው፡፡

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ አምስትን ትምህርት እዚህ ላይ አጠናቀናል በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጥህን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦልሃል የተነሳውን ነጥብ የምታውቀው ከሆነ ይህን ምልክት አድርግ [√] ነጥቡን ካላወቅከው ደግሞ የ [X] ምልክት አድርግና እንደገና ተመልሰህ ትምህርቱን ከልስ

1. ተውኔቶች የሚከፋፈሉበትን መስፈርት በዝርዝር ማስረዳት እችላለሁ፡፡ … [ ]
2. የተውኔት አይነቶችን መዘርዘር እችላለሁ፡፡ [ ]
3. የእያንዳንዱን የተውኔተ አይነት ምንነት መናገር እችላለሁ፡፡--- [ ]
4. በተውኔት አይነቶች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ማስረዳት እችላለሁ፡፡ [ ]
5. የእያንዳንዱ የተውኔት አይነት ይዘትና ድባብን ተንተኜ ማስረዳት እችላለሁ፡፡ [ ]

## ግለ ፈተና አምስት

በምዕራፍ አምስት ያቀረብነውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተለው ፈተና ተዘጋጅቷል፡፡ በትምህርቱ ውስጥ የቀረበውን ገለፃ ሳትመለከት ጥያቄዎቹን መልስ፡፡ ጥያቄዎቹን ሠርተህ ከጨረስክ በኋላ በሞጅዩሉ የመጨረሻ ገፆች ካቀረብንልህ መልሶች ጋር አመሳክር፡፡

***መመሪያ አንድ*** ፡- <u>ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ፡፡</u>

----------------1. የተውኔቶች በአይነት የሚከፋፈሉት በድባብ መሰረትነት ብቻ ነው

----------------2. ተውኔቶችን በአይነት ለመከፋፈል መሰረት የሆነው አሪስቶትል ነው

-----------------3. በጥንታዊ ትራጀዲ ገፀባህሪው ችግሩን ቶሎ ለመፍታት ይጥራል ዕድሉም በአማልክት ወይም በእጣፈንታ ይወሰናል፡፡

-----------------4. ድንቃይ ተውኔት የሁሉም የተውኔት አይነቶች ውህደት ነው

------------------5. ቧልታይ ተውኔተ ሳቅ ለማጫር ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮችን ይፈጥራል

-------------------6. በኮሜዲ ወቅታዊና ልማዳዊ ጉዳዮች ይነሳሉ

-------------------7. ድንቃይ ተውኔት የተዋጣ ሴራ እና ገፀባህርያት ይቀርፃል

-------------------8. ዘመናዊ ትራጀዲ ቋንቋው ዝርውርና ተራ ነው፡፡

-------------------9. ተውኔተ የህፃናት እና የአዋቂዎች በመባል የሚከፋፈለው ቅርፁ መሰረት ተደርጎ ነው

------------------10.ዋናው ገፀባህሪ በኤልሳቤጣዊ ትራጀዲ ብዙ ጊዜ ይሞታል፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የመድረክ አይነቶች

### መግቢያ

*የምዕራፉ አላማዎች*

*ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-*

- *የመድረክን ምንነት ትገልፃላችሁ፡፡*
- *የመድረክ ዓይነቶችን ትለያላችሁ፡፡*
- *የመድረክ አይነቶች ልዩነት ታስረዳላችሁ፡፡*

*ውደ ተማሪዎች፡- በዚህ ምዕራፍ ተውኔት የሚቀርብባቸውን የመድረክ አይነቶች እናያለን፡፡ ስለ መድረክ ምንነትና አይነቶች ገለፃ ከመደረጉ በፊት ግን ቀጥሎ የቀረበውን ጥያቄ ለመመሰስ ሞክሩ፡፡*

> *ውድ ተማሪዎች፡- መድረክ ምንድን ነው?*
>
> -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
>
> -----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
>
> ----------------

*መድረክ ተውኔት በሚገባ ከተዘጋጀ በኋላ ለተመልካች የሚቀርብበት ቦታ ነው፡፡ ተውኔት ለተመልካች በተለያዩ መድረኮች ይቀርባል፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው የተውኔት ማቅረቢያ መድረኮችን ከተመልካች ጋር ባላቸው ርቀት በሶስት ከፍለን ነው፡፡ እነዚህ ሶስት መድረኮችም ክብ መድረክ፣ ፊት ለፊት፣ መድረክና ሶስት ጎን መድረክ በመባል ይታወቃሉ፡፡*

*እነዚህን የመድረክ ዐይነቶች ስናነሳ ሌሎች የመድረክ አይነቶች የሉም ማለታችን አይደለም፡፡ እንደአመቺነቱ ለተውኔት ተብለው ባልተዘጋጁ ስፍራዎች በአዳራሾች ውስጥ ተውኔቶች ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ቀደም ሲል እንዳነሳነው በዚህ ምዕራፍ የምናያቸው ለተውኔት ማሳያነት ተብለው በባለሙያ ዲዛይን ወጥቶላቸው የሚሰሩ መድረኮችን ነው፡፡*

## 6.1 የፊት መድረክ (Proscenium stage)

*ተውኔቱ የሚቀርብበት መድረክ ከተመልካች ፊት ለፊት የሚሆንበት የመድረክ አይነት ነው፡፡ ይህ መድረክ በሀገራችን ባሉ ቲያትረ ቤቶች ውስጥ ይገኛል፡፡ ተዋንያን እና ተመልካቹ በተቃራኒ አቅጣጫ ይሆናሉ፡፡ ከመድረክ በስተጀርባ የተዋንያን አልባሳት መቀየሪያ ፣ የመዋቢያና የመዘጋጃ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ በመድረክ ተዋንያኑ በሚተወኑበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በግማሽ ፊታቸውን ወደ ተመልካቹ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተዋንያኑ ጀርባቸውን ሙሉ ለሙሉ ለታዳሚያን መስጠት የለባቸውም፡፡ የፊት ለፊት*

መድረክ ከተመልካቹ መቀመጫ ከፍ ብሎ የሚገነባ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ መድረክ በታዳሚያንና በተዋንያን መካከል ርቀት የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ተዋንያን ገዝፈው እንዲታዩ ምክንያት ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 6.2 ክብ መድረክ (arena stage)

ተውኔቱ የሚቀርብበት መድረክ ተመልካቹ በሚያይበት አዳራሽ መሐል ላይ ሲገነባ ክብ መድረክ ይባላ፡፡ የተውኔቱ ታዳሚያን በመድረኩ ዙሪያ ይጠቅማሉ፡፡ የወንበር አደራደሮቹ ልክ እንደ ቅርጫት ኳስ ወይም እግር ኳስ ያሉ ናቸው፡፡ ተዋናያኑና ተመልካቹ የሚቀራረቡበት የመድረክ አይነትም ነው፡፡ ከፊት ለፊት መድረክ በበለጠ መልኩ ታዳሚን ተዋንያንን ከነድርጊታቸው በቅርብ ያይዋቸዋል፡፡ ሌላው መድረኩ በተመልካች መሐል የተገነባ በመሆኑ በመድረኩ ዳራዊ ቅብ ማንጠልጠል አይቻልም፤ ይህ ከፊት ለፊት መድረክ ይለዋል፡፡ ዳራዊ ቅብን በክብ  መድረክ መጠቀም የማይቻለው የተውኔቱ ተመልካች በመድረኩ ዙሪያ የሚቀመጥ በመሆኑ አንዳች ነገር በመድረኩ ላይ መንጠልጠሉ እይታውን ስለሚሸፍን ነው፡፡

### የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ ስድስትን  ትምህርት እዚህ ላይ አጠናቀናል በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጥህን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦልሃል የተነሳውን ነጥብ የምታውቀው ከሆነ ይህን ምልክት አድርግ [ √ ] ነጥቡን ካላወቅከው ደግሞ የ[ X ] ምልክት አድርግና  እንደገና ተመልሰህ ትምህርቱን ከልስ

1. መድረክ ምን እንደሆነ ማስረዳት እችላለሁ፡፡ ......[ ]
2. የፊት መድረክ እንዴት እንደሚዘጋጅ ማሳየት እችላለሁ፡፡ [ ]
3. ክብ መድረክ እንዴት እንደሚዘጋጅ ማሳየት እችላለሁ፡፡ [ ]
4. ሶስት ጎን መድረክ እንዴት እንደሚዘጋጅ ማሳየት እችላለሁ፡፡ [ ]

# ዋቢ ፅሑፎች


ዊሊያም ሼክሲፒር (1977) ሃምሌት፡፡ (ተርጓሚ ፀጋዬ ገብረ መድህነ) አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት፡፡

_______________ (1977) ማክቤዝ፡፡ (ተርጓሚ ፀጋዬ ገብረ መድህን) አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ግርማቸው ተክለሐዋርያት (1960) ቴዎድሮስ ታሪካዊ ድራማ ፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ማተሚያ ቤት

መንግስቱ ለማ (1975) የተውኔት ጉባዔ፡፡ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ፋንታሁን እንግዳ (2001) ተውኔታዊ መዝገበ — ቃላት እና ብያኔዎቻቸው፡፡ አዲስ አበባ ፤ (ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰበት)፡፡

ከበደ ሚካኤል (1957) የትንቢት ቀጠሮ፡፡ አዲስ አበባ ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ጌትነት እንየው (2000) እቴጌ ጣይቱ ታሪካዊ ተውኔት በአዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፡፡

ፋንታሁን እንግዳ (1998) ዓይነ ሞራ እና ሽርገጤ፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስተክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፀጋዬ ገብረመድህን (1958) የከርሞ ሰው፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

የሻው ተሰማ (1998) የተውኔት አጽናፍ መነጽር፡፡ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ

ደበበ ሰይፉ (1977) የቲያትር ጥበብ ከጸሐፊ ተውኔቱ አንጻር፡፡ አዲስ አበባ ፤ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

መንግስቱ ለማ (1964) የቲያትር ድርሰት የአጻጻፍ ብልሃት፡፡አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ድርስትማህበር፡፡

**ከድሮ መጻሕፍት**

**ዳንዴው ጨቡዴ**

/ባለ አንድ ገበር ድራማ/

ደራሲ፡- አንቶ ቼኾቭ

ተርጓሚ፡- መንግስቱ ለማ

ከመዘጋጁ

ይህ ጹሑፍ "የቴአትር ድርሰት ያጻጻፉ ብልሐት" በሚል ርዕስ በ1964 ዓ.ም በደራሲ መንግስቱ ለማ ከተጻፈ መጻሐፍት የተወሰደ ነው፤ በመጽሐፉ ውስጥ "ዳንዴው ጨቡዴ" የተሰኘ ባለ አንድ ገቢር ኮሜዲ ድራማ ተካቷል፡፡ መጹሐፉ በአሁኑ ጊዜ ገበያ ላይ ባለወገኘቱ ብዙዎች ሲቸገሩ አይተናል፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለማስተማሪያነት ጭምርም ስለሚያገለግል ተፈላጊነቱም ከፍ እያለ መጥቷል፡፡

ደራሲው በመጻሐፉቸው መግቢያ ላይ እንዲ ብለው ነበር፡፡

"እትዮጵያ ድርሰት ማኅበር የተቋቋመበት ዓለማ በኢትዮጰያ ሥነ ጹሑፍ እንዲስፋፋ ማበረታታት ፣ እንዲሀም ለአንባቢያንና ለደራሲያን የሚጠቅሙ ምክር መስጠት መሆኑን ባለመዘንጋት ማኅበሩ በጀመረው የመርሐ ድርሰት ማሳተም ኘሮግራም መሰረት ይህችን መጽሐፍ በገዛ ገንዘቡ አሳትሞ ለደራሲዎችና የድርሰት ዝንባሌ ላላቸው አንባብያን አቅርቧል፡፡

**የታሪኩ ሰዎች**

ወይዘሮ አመንሸዋ፡- ባሏ የሞተባት ባለ ቀላድ እመቤት ሉቃስ፡ ሽማግሌ የእልፍኝ አሽከር

አቶ ጨቡዴ፡- ባለ ቀላድ ገብሬ፡ ሙሉ ሰው ቦታው ባላገር ነው

______________________ // ________________________

*መጋረጃው ሲገለጥ ወይዘሮ አመንሸዋ ከል ለብሳ ዓይኖችዋን እልች ባልዋ እግራዥማች ፎቶግራፍ ላይ ተክላ በኃዘን ተቀምጣለች፡፡ ሉቃስ አደግድጎ ቆማል፡፡*

**ሉቃስ፡-** እሜትዬ የኔ እመቤት! አይገባም በዛ፡፡ ባለ ሞቷልና እኔም ካልሞትኩት ማለትሽ ነው፡፡ ገረዶችሽና ወንድ አሽከሮችሽ በኮሽም ለቀማ እያሳበቡ ሽርሽር ሔደዋል፡፡ ውርዬ እንኳን ድመትዋ በአጥር ግቢው እየተንሽራሽረች ወፍ ታሳድዳለች - ትቦርቃለች፡፡ ብቻ እገዛ እልፍኝሽ ተዘግተሽ ገዳም የገባች መለኩሲት መስለሻል፡፡ አይገባም አሁንስ በዛ ከቤትሽ ሳትወጪ ድፍነ አመትሽ፡፡

**አመንሸዋ፡-** አሁንም ቢሆን ወደፊትም ቢሆን ከቤቴ ላልወጣ ቆርጫለሁ፡፡ ለየትኛው ዓለም ነው? ሕይወቴ እንደሆነ አንድ ጊዜ አልፏል፡፡ እሱም እመቃብር ገብቷል፡፡ እኔም ከእንግዲህ ወዲያ ደጃፌን አልረግጣት፡፡ እሲም፤ እኔም፤ ሁለታችንም ሞተናል፡፡

**ሉቃስ፡-** እንግዲህ ጀመርሽ! አሁንስ እኔንም ሰለቸኝ፡፡ ግነዝማች እንደሆኑ አንድየ ሞቷል፡፡ መልሰን ልናመጣው አንችልም፡፡ የዚጊሐር ፈቃድ ነው፡፡ መንግስተ ሰማያቱን ብቻ ያውርሰው እሱ በቸርነቱ፡፡ ሀዘኑ ይበቃል፡፡ ለሁሉም ልክ አለው፡፡ ሰው እስከመዌ ድረስ ከል ለብሶ ባለን ተኮማትሮ ይኖራል? ተምረሽ እንዳልተማረ ማይም ትሆናለሽ፡፡ የኔይቱ አሮጊት እንኳን ሚስቴ በአስም ሞታለች፡፡ አዘንኩ ፤ ድፍን ወር ሙሉ አለቀስኩላት፤ ይበቃታል፡፡ እድሜ ልኬን ሙሉ እዬዬ ካላልኩ ብል አይሆንም አይገባትም ይበዛባታል፡፡ /በትካዜ ይተነፍሳል/ወዳጅ ጎረቤትሽን ቢመጣ ረስተሻል፡፡ ሰው አትጠይቂ ፤ ሰው ሊጠይቅሽ ቡመጣ አትቀበይ፤ ዘግተሻል እነደ ባሕታዊ፡፡ የዙህ ቤት ኑሮ አሁንስ የኩሽሽላ ኑሮ ሆኗል፡፡ ጨለማ ዋሻ፤ ጣይ የማይገባው፡፡ የበቅሎውን ዕቃ አይጥ በልቶ ሊጨርሰው ነው፡፡ በዙሪያችን ጨዋ ሰው መቼ ጠፋና? ጥምቡን ጥሏል፡፡ ገጠሩ ሙሉውን የጨዋ ልጅ ነው፡፡ እዝህ አጠገባችን እንኳ በቀደም ለታ ምን የመሰለ መዘዞ የጦር ሠራዊት መኮንን አይቻለሁ፡፡ ስሚኝ፡፡ ገና አነድ ፍሬ ቅንጦት ሳለሽ ጀመረሽ ታውቂኛለሽ፡፡ ቆንጆ ነሽ፤ ማርና ወተት ነሽ ወለላ፡፡ ይህን የመሰለ መልክ ይዘሽ ይኽነየ ዓለምሽን ትጠግቢ ነበር በደስታ ኑሮ፡፡ ዓለም አላፊ ነው መልክ ረጋፊ ነው

ሲባል አልሰማሽም? ወደፊት የዛሬ አሥር ዓመት እንደ ቆቅ ልታስኮኪና ልትሽቀረቀሪ ፤ የጎልማሶችን ዓይን ልትማርኪ መክጀልሽ አይቀርም፤ ምናለበይኝ፤ ግን አይሆንልሽም ያልፍብሻል።

**አመንሽዋ፡-** {በቆራጥነት} እባክህን ሉቃስ ፤ ሁለተኛ እንዲህ ያለውን ነገር አታንሳብኝ። አንተ ራስህ ታውቃለህ፤ ግራዝማች ከሞተ ወዲያ የዚችን ዓለም ሕይወት ከጤፍ እንደማልቆጥራት ታውቃለህ። መስሎሐል፤ በሕይወት ያለሁ ይመስልሃል እንጂ፤ እኔስ የለሁትም እቴ! ምያለሁ፤ እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ ይችን የለበስኮትን ላላወልቃት ካጥር ጊቤዬ ላልወጣ ፤ መሐላ ገብቻለሁ። የግራዝማች ውቃቢ ይታዘበኝ። አትንገረኝ አውቃለሁ። ግራዝማች በብዙ ብዙ ነገር በድሎኛል። በኔ በሚስቱ ላይ ሌላ ሴት እስከ መወሸም ድረስ ግፍ ውሎብኛል። እኔ ግን ዓለሜን አልለውጣትም፤ እስከ መጨረሻው ድረስ ታማኝነቴን አሳየዋለሁ። በኋላም በዚያ በወዲያኛው ዓለም ስንገናኝ እሱ ቢሞትም እንኳን ከሞተም ወዲያ እን አለመለወጤን ይገነዘበዋል።

**ሉቃስ፡-** በዚህ ቁጭ ብለሽ እንዳህ ያለውን መራራ ነገር ከመናገር ይልቅ፤ ለምን ወደ ውጪ ወጣ አትዪና ነፍስ አትቀበይም? ወይንም ቡሊት ትጫንና ዘመድ ጠይቀሽ ተመለሺ

**አመንሽዋ፡-** /ታለቅሳለች/ ዋ! ዋ! ዋ!… ወይኔ ባለዬ! ወይኔ የኑሮ ጓደኛዬ!… ወይኔ… ወይኔ ወይኔ አንድ አካሌ… ወይኔ አንድ አምላኬ…

**ሉቃስ፡-** ምነው እሜትዬ ፤ ምን ሆንሽብኝ? የኔ እመቤት እባክሽ አታልቅሽ!

**አመንሽዋ፡-** እሱስ የሚወደው ጉራችን ነበር ሠንጋ ፈረሱን። ዘመድ ለመጠየቅ ሲሔድ ሁለዬ ጉራችን ነበርየሚጋልበው። አይ አረሰኛነት! ግራዝማችን የመሰለ ማን ይገኛል አሁን? ጉራችን በርካቡ ጉጥ ከርከር ያረገ ያስነሳና ፤ ሽምጥ ከለቀቀው በኋላ፤ ባለ በሌላ ኃይሉ ልጓሙን ሳብ አድርጎ ኀትቶ ፤ ጠብ ብሎ እንደሚወርደው ትዝ አይልሕም? ዋ ጉራች፤ ጉራች። እሱም ያሳዝነኛል። እንዲያ የሚወደውን የሚያፈቅረውን ጌታውን አጣ። ሰማኸኝ? ዛሬ ለጉራች ከገብሱ በርከት አድርገው እንዲሰጡት እንድትነግራቸው ላሽከሮቹ።

**ሉቃስ፡-** እሺ የኔ እመቤት፤ ለጉራች የቀለብ **ጭማሪ ይደረግለታል።**

**አመንሽዋ፡-** /ትደናገጣለች/ ማነው? እኔን እነደሆነ የለችም በል፤ ማንንም አልቀበልም።

**ሉቃስ፡-** እሺ የኔ እመቤት የለችም እላለሁ። /ይወጣል።

**አመንሽዋ፡** እስቲ ፎቶግራፍህን ልየው የኔ ግራዝማች። ታየኛለህ? እኔ ሚስትህ ይቅር ባይ ነኝ፤ ፍቅር ጥሩ ነኝ ላንተ ለባሌ ያለኝ ታማኝነት ስሞት ይሞታል። ግቢ መሬት ስባል አብሮኝ ይቀበራል። /በሃዘን ሳቅ ትላለች/ ታዲያ ግራዝማች፤ አንተስ ዕፍረት አይሰማህም አሁን? እኔ ይኸውልህ እንደምታየኝ ጥሩ ታማኝ ሚስት ነኝ። እንደ ባሕታ ዓለሙን መንኜ፤ ከል ለብሼ ፤ እስከ እለተ ወቴ ድረስ ሃሳቤ ካንተ አይለይም። አንተ ብቻ ግራዝማች፤ ያንተ ነገር፤ ምን ይደረጋል? አንተ ቀበጥ! አቶ ምንግዴ! አንተ ማ በኔ ላይ ሌላ ሴት ወሽመህ ነበር። ደሞ ንትርክህ ይባስ። መጥኔ!አንዳንዴማ ዙረትህ ትጀምርና ሳምንት ሁለት ሳምንት ሦስት ሳምንት ሙሉ እኔን ብቻዬን ባዶ ቤት ጥለህ የትም ከርመህ ትመለሰ ነበር። /ሉቃስ ይገባል/

**ሉቃስ፡-** እመቤቴ፤ የቸገረ ነገር ገጥሞኛል። አንድ ሰውዬ አንችነ ካላየሁ ይላል፤ ለብርቱ ጉዳይ ነው ይላል

**አመንሽዋ፡-** ባሌ ከሞተ ወዲህ ሰው አልቀበልም፤ አላነጋግርም። ይህንን ነግረኸው የለም?

**ሉቃስ፡-** አሳምሬ ነግሬዋለሁ፤ እሱ አልሰማም አለ። ፤ የማይውል የማያድር አስቸኳይ ጉዳይ ነው ይላል።

**አመንሽዋ፡-** ማንም ቢሆን እንግዳ አልቀበልም፤ አላነጋግርም።

**ሉቃስ፡-** ነግሬው፡ ሰውየው ሴጣናም ነው ወንድሜ፤ እየተሳደበ ዘው ብሎ ገብቶ አሁን እምግብ ቤት ነው ያለው።

**አመንሽዋ፡-** (ትበሳጫለች) ያንዳንድ በው ደፋርነትና ዓይን አውጣነት አይጣል ደጎና፡ አስገባው። (ሉቃስ ይወጣል)መጥኔ ደሞ ምነ አምጭ ነው የሚሉኝ የዚህ ዓለም ሰዎች እየመጡ ሰላም ቢነሱኝ ምን

ይጠቅማቸዋል እንግዲህ? (በትካዜ ትተነፍሳለች) መዳኒቱ አንድ ብቻ ነው፡ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገብቼ አርፈዋለሁ። (ታሰላስላለች) አዎ ገዳም ነው እሱ ብቻ ነው መዳኒቱ።

**ጨቡዴ፡-** ምን ያለው ከብት ነው እቦካችሁ፣ ያሙሰ ፍጥረት እንስሳ። መቀባጠር ታበዛለህ።

(አመንሸዋን በጨዋ ደምብ ያናርራል) እሜቴ ስሜ ጨቡዴ ኃይሉ ይባላል። እኔም ባለ ቀላድ ገበሬ ነኝ። የመጣሁት በሚያስቸኩል ጉዳይ ምክንያት ስለሆነ፡ የግድ እርስዎን ማነጋገር ሆነብኝ።

**አመንሸዋ፡** እዚህ ቤት ምን ይፈልጋሉ?

**ጨቡዴ፡-** ባለቤትዎ ግራዝማች እንደሻው በሕይወቱ ሳለ አንድ ሺ ሁለተ መቶ ጥሬ ብር የኔ ዕዳ ነበረበት። ለዚሁ ዋስትና ከመሞቱ ፊት የፈረመልኝን ሁለት ደረሰኝ ይዤ መጥቻለሁ። በበኩሌ ደሞ የእርሻ ባንክ ብድር ስላለብኝ ነገ ጧት ወለዱን መክፈል አለ። ስለዚህ ባልዎ የገባውን ዕዳ እርስዎ እሜቴ ዛሬ እንዲከፍሉኝ እጠይቅዎታለሁ።

**አመንሸዋ፡** አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር … ባለቤቴ ለርስዎ ዕዳ የገባው በምን ምክንያት ነው፡ ያውቃሉ?

ሉቃስ፡- እሺ እመቤቴ አሁን እንግራቸዋለሁ።

(ሉቃስ ይወጣል)

እግራዝማች ላይ ገንዘብ አለኝ ካሉ ምናለ እኔ እከፍሎታለሁ። ብቻ ለጊዜው ጥሬ ገንዘብ በእጅ የለም። መሬት ጠባቂዬ እህል ሸምቶ ተነገ ወዲያ ካዲስ አበባ ይመለሳል። እሱ እንደመጣ ገንዘቡን ይከፍሎታል። አሁን እንዳስረዳሁዎት ለጊዜው ልከፍልዎ አልቻልኩም። እንዲያውም ዛሬ ግራዝማች ከሞተ ልክ ሰባት ወሩ ሞልቷልና እኔ እሱን ከማስብ ለሱ ለባሌ ከመጸለይ በቀር በገንዘብ ወይም በሌላ ጉዳይ ራሴን ለማዞር አይቻለኝም አያሰኘኝም።

**ጨቡዴ፡-** እኔ ደሞ ነገ ጧት ለልማት ባንክ ወለዱን ካልከፈልኩ ራሴ መዞር ግልጥ ነው መሬቴን በወለዱ አግድ ይይዝብኛል። ቀላዴ ዋስትና አስይዤ ነው የተበደርኩት።

**አመንሸዋ፡-** ተነገ ወዲያ ገንዘብዎ ይከፈልዎታል።

**ጨቡዴ፡-** ገንዘቤን የምፈልገው ለዛሬ ነው ለተነገ ወዲያ አይደለም።

አዝናለሁ ለዛሬ ልከፍልዎ አልችልም።

**ጨቡዴ፡-** እኔ ደሞ እስከተነገ ወዲያ ድረስ መቆየት አይቻለኝም።

**አመንሸዋ፡-** ገንዘብ በጄ ከሌለ ምን አደርጊ ነው የሚሉት?

**ጨቡዴ፡-** እንግዲህ ልከፍል አልችልም ማለትዎ ነዋ?

**አመንሸዋ፡- አዎ አልዎልኩም።**

**ጨቡዴ፡-** እምምም … በቁጥር፣ አልችልም ማለትዎ ነው

እቅጩን ነው የነገርኩዎት።

**ጨቡዴ፡-** እኮ ቁርጠኛውን

**አመንሸዋ፡-** ጥርጥር የሌለው ነው።

**ጨቡዴ፡-** አመስግናለሁ። አሁን ያሉኝን በማስታወሻ አያይዘዋለሁ። (ትከሻውን ያራግፋል) ደሞ ሰዎቹ አትናደድ ይሉኛል። ጭቃ ሹምን አሁን እመንገድ ላይ አገኘሁትና ነጋ ብስጭት ጠባ ብስጭት ምን ነካህ ጨቡዴ ኃይሉ? ብሎ ይጠይቀኛል። እግዜር ያሳያችሁ? እኔስ እንደምን አልናደድ አልጭስ አልቃጠል? ይኸውና ገንዘብ ቸግሮኝ ጨንቆኝ ውጪ ነፋስ ግቢ ነፋስ ሆኗል በጭት አሥሣለሁ። ትናንትና ጧት በሌሊት ከቤቴ የወጣሁ። ገንዘብ የተበደሩኝን ሁሉ በየቤታቸው እየዞርኩ ስለ ወንድ ልጅ ብላችሁ ስለበለስ ክፈሉኝ በማለት ላይ አለሁ። አንዱ አልከፈ ለም አንድ እንኳን። ድቅቅ ብያለሁ በኩረት ከድካም ትዝ አይለኝም ካንዲ ከፈረደበት አልቤርጎ ሳይ ሆን አይቀርም። በመካያው ምናልቦት እዚሁ ቤት ይከፍሉኝ ይሆናል ብዬ በተስፋ ያንድ ቀን መንገድ ተጉዤ እመጣለሁ፡ ምን ይገጥመኝ ይመስላችኋል? እሜቴ መክፈል መክፈል አላላቸውም። አላሰኛቸውም አልቆጣስ!

**አመንሸዋ፡-** መሬት ጠባቂየ ካዲስ አባ ሲመለስ ገንዘብዎን ይከፍሎታል ብዬ ያስረዳሆት መስሎኝ ነበር።

**ጨቡዴ፡** የመጣሁት ከርስዎ ዘንድ ነው፡ ከመሬት ጠባቂዎ አይደለም፡፡ መሬት ጠባቂዎ ከእነ እክቱ ገደል ይግባ፡ ቁብ የለኝም!

**አመንሽዋ፡-** ይቅርታዎንና በዚህ ቤት እንደዚህ ያለ ኃይል ቃል እንዲህ ያለ አነጋገር መስማት አላስለመድኩም፡ ቢለፈልፍ የሚሰማዎ የለም፡ እኔ በቅቶኛል፡፡ (በመጣደፍ ትወጣለች)

**ጨቡዴ፡** ይኸውላችኋ! እንዲህ ነው ጨዋታ! አቶ ባል ከሞተ ሰባት ወሩ ዛሬ ነውና? እሜቴን መክፈል መክፈል አኸሏላቸውም፤ አላሰኛቸውም፡፡ ታዲያስ እኔሣ ምን ይዋጠኝ? ወለዱን ነገ መክፈል አለብኝ ወይስ የለብኝም? ነው የምላችሁ በኋላ (በፌዝ) አዎን እሜቴ፤ ባልዎ ሞቷል፡ እርስዎን አላሰኝዎችም … ደሞ መሬት ጠባቂዎ ዲያብሎስ ድራሹን ያጥፋውና፡ የት እነደ ገባ አይተወቅም፡፡ ምን አድርግ ነው የምባለው ታዲያ? እኔምእዳ አለብኝ፡፡ እኔም በእዳ ተወጥሬያለሁ፡፡ እነደ አቡነ አረጋይ በደመና ተጭኜ ላርግ ነው ወይስ እንዳቡነ ተክለ ሃይማኖት ስድስት ክንፍ አውጥቼ ላመልጥ ኑሮዋል? ወይንስ መሬት ተከፍታ ልትውጠኝ ነው? አዝብጤ ጋብሔድ በቤቱም የለ፡፡ በዳኔ ተደብቋል፡፡ ከወልደ ሩፌ ጋር ያው ምርር ብለን ዱላ ቀረሽ ተጣላንና በመስኮት አምዘግዝጌ ልወረውረው ነበር፡፡ እግዜር አወጣው፡፡ ጉሽሜ ታሟል፡፡ ተቅማጥ ይዞታል፡፡ እኒህ ወይዘሮ ደመሞ አላስተኛቸውም፡፡ ከዚህ ከወስላቶች ሁሉ አንዱ እንኳን አልከፈለም እዳውን፡፡ ምክንይቱም የኔ ጥፋት ነው፡፡ ምን ያድርጉ? አበላሸኋቸው፡፡ እን ደናት እንደ እህት ነው በለዘብታ በልስላሴ የምለምናዋቹ፡፡ የገዛ ገንዘቤን እንዲከፍለኝ እኮ … አዎ ምን ይበሉ? መልአክ ነኝ!/በዛቻ/ ቀይ ሁልሽንም ሳላሳይሽ ምን እጥረት እንደሆንኩ ታውቂኛለሽ ሁልሽም፡፡ እንደ በግ ስመኝላችሁ አልሃርም፤ የመጣው ይመጣል፡፡ ይች ሴትዮ ገንዘቤን እስክትከለክለኝ ድረስ ከዚች ከቆምኩባት ቦታ ንቅንቅ ብል እኔ አይደለሁም፡፡ እፎይ! ጭሻለሁ ነድጃለሁ ዛሬ፡፡ የደም ስሬ ሁሉ ተገተርትሮ ጅማቴ ይርገበገባል ይንዘፈዘፋል፡፡ መተንፈስ አቅቶኛል፡፡ ኦህ እፎይ አረ የፈጠሪ ያለህ ሊያቅለሸልሸኝ ነው … አንተ ማነህ ልጅ አሽከር /ሉቃስ ይገባል/

**ሉቃስ፡** ጌታው ምን ፈልገዋል?

**ጨቡዴ፡** ቅራሪ መሳይ ከሌለም ውሃ አምጣ፡፡

/ሉቃስ ይገባል/

ነገሩ ነው የሚገርመኝ፡፡ አንድ ሰው በገንዘብ ችግር ተወጥሮ በገመድ አንገቱን ሊታነቅ ምንም አልቀረው፡፡ እሜቴ ግን ምናለ ዕዳቸውን አልከፍልም ይሉታል፡፡ ምክንያቱም ቢሉ ክፊይ ክፊይ አላላቸውም! አላሰኛቸውም … የሰቶች ነገር ይኸውላችሁ! ከሴት ጋር ቁም ነገር መነጋገር የሚያብጠላኝ ለዚህ ነው፡፡ ምክንይቱም አላውቃቸውም ፤ ብቻ አልወድ ኩንታል ደማሚት ላይ ቁጭ ማለት እመርጣለሁ፡፡ … ኸኸኸ …ቸቸቸ… ጠጉሬ ቆሟል፤ ይች ከል ለባሽ አጭሳኛለች፡፡ እንድዚያ ያለትነ የሚራቀቁ ፍጥረቶች ገና ከሩቁ ሳያቸው ነው በኔ ደሜ የሚፈላው፡፡ እሪ በል ነው የሚሉኝ፡፡ /ሉቃስ ይገባል/

**ሉቃስ፡** ውሃው ይኸውልዎ፡፡ /በብርጭቆ ውሃ ይሰጠዋል/ እሜቴ ወይዘሮ አመንሸዋ ራስ ምታት አሟቸዋል! ሰውም አያዩ አያናግሩ፡፡

**ጨቡዴ፡** ውጣ ከዚህ ዓይንህ ይውጣና . . . /ሉቃስ ይወጣል/ ደሞ አሟቸዋል! ደሞ አያናግሩም! ምን ገደደኝ? አታነጋግሪኝ፡፡ ገንዘቤን እስክትከፍይኝ ድረስ እዚችው እቀመጣታለሁ፡፡ ሳምንት ብትታመሚ ሳምንት እቀመጣለሁ፡፡ አመት ብትታመሚ አመት እቀመጣለሁ፡፡ ብድሬን ሳልከፍል ብቀር ምናለ በይኝ እሜቲቱ፡፡ አዎ፤ ግራ ጉንጭሽ ላይ ማርያም የሳመችሽን አይቻለሁ፤ ከል ለብሻለሁ፤ እኔ ጨቡዴ ግን እምታለልልሽ አይመስልሽም፡፡ እናውቀዋለን መቼ አጣነውና ብልሀቱን፡፡

/በመስኮት ይጮሃል/ አንተ አረሩ፤ ፈረሴን አራግፈው፤ እዚሁ መቆየታችን ነው፤ አንሔድም፡፡ እጋጣ አስገባውና ገብስ እንዲሰጠው ንገራቸው፡፡ ደሞ ዛሬም ግላሱን ገልብጠኸዋል! ምን? ምናለ በት? አንተ ጭምብስብስ ጨምባሳ ጭምብስ!

**ዳንዴው…** ምን እንደ ሌለበት ቀይ አሳይህአለሁ፡፡ /ከመስኮቱ ይመስላል/ ይገርማል፡፡ በዚህ ባንጣር ጣይ ስንቃ ውዩ አንድ ሰው ገንዘቤን አለከፈለኝም፡፡ የትናቱንን መኝታ መኝታ አይበለው እዚህ እመጣለሁ ደሞ ፡ እሜቴ ከል ለብሰዋል አላሰኛችውም፡፡ ራስ ምታት ሊታገለኝ ነው፣ ጠላ ልጠላበት መሰለኝ፡፡ ብጠጣበት ይሻለኛል፡፡

/ይጮሃል/ ማነህ ልጅ አንተ፣ አሽከር፡
/ሉቃስ ይገባል/
**ሉቃስ፡-** ጌታው ምን ፈለጉ ደሞ
ጨቡዴ አንድ ብርሌ ጠላ ፡ ተሎ በል፡፡
/ሉቃስ ይወጣል፡፡ እፎይ እናት፡ ይቀመጥና ሁኔታውን ይመለከታል /ዛሬ ሙሽራ መስለሃል አትሉኝም እንዴ አቧራ ብቻ ጫማየ በጭቃ ተጨማልቆ ጠጉር አልተበጠረ ልብሴ በጭቃ ተለውሶ… ለዚች ለእሜቲቱ ወንበዴ ሽፍታ ሳልመስላት አልቀረምሁም፡፡
/ይዛጋል/ እርግጥ ነው ይህንን መስሎ ፣ እንደዚህ ሆኖ እሰው እልፍኝ አይገባም ነበር… ግደለም ለግበዥ ተጠርቶ የመጣ እንግዳ አደለሁም የገዛ ገንዘቤን ፍለጋ ነው፡፡ /ሉቃስ ይረባና ጠላውን ይሰጠዋለል/
**ሉቃስ፡-** ይኸውና ጠላው፡፡ ጌታው፣ አለቤትዎ በሰው ቤት አለመጠን ይዝናናሉ ልበል…
**ጨቡዴ፡** /በቁጣ/ ምን ምን አልክ ልበል
ሉቃስ ምንም፣ ምንም አላልኩም…ብቻ እንዲያው… ለማለት ነበር፡፡
**ጨቡዴ፡**/ በቁጣ/ ምን ምን አልክ ልበል
**ሉቃስ፡** ምንም ምንም አላልኩም .. ብቻ እንዲያው … ለማለት ነበር፡፡
**ጨቡዴ፡** ማን መስየሃለሁ በል ዝም በል፣ አፍህን ያዝ ብዬሃለሁ ዛሬ፡፡
ሉቃስ፡ በጎን/ ምናለ በሉኝ፡ እዚህ ቤት ዛሬ አንዳች የሚያህል ጤን ገብቷል፡፡ /ሉቃስ ይወጣል/
**ጨቡዴ፡** ወይ ንዴት፡ ወይ ቁጣ፡ በዛሬው ንዴቱ ይችን ዓለም በሙሉ ምድሯን ደቁስህ አመድ አድርጋር ቢሉኝ፣ እንደ መናደደ አያቅተኝም፡፡
/ይጮሃል/ ማነህ፣ ልጅ፣ አሽከር፣ አንተ
/ወይዘሮ አመንሽዋ ዓይሂን ደፍታ ትገባለች/
**አመንሽዋ፡** ጌታዬ፡ አቤቱ ተከትቼ በብቸኛነት መኖርን ከመረጥኩኝ ወዲህ የሰው ድምጥ የቤቱ ፀጥታ አይበጥብጡት እባክዎ፡፡
**ጨቡዴ፡** ገንዘቤን ይከፈሉኝና ልሐድዎት፡፡
**አመንሽዋ፡** አሁን በጄ ጥሬ ገንዘብ የለኝም ብዬ በግልጥ አማርኛ ነግራዎታለሁ፡ እስከ ተነገወዲያ ድረስ መታገስ አለብዎ፡፡
**ጨቡዴ፡** እኔ ደሞ ገንዘቡ የሚያስፈልገኝ ለዛሬ ነው፡፡ ለተነገወዲያ አይደለም፡፡ ብዬ በተጠራ አማርኛ አሰታውቄዎታለሁ፡፡ ዛሬ ገንዘቤን ካልከፈሉኝ፡ ነገ ታንቂ መሞቴ ነው፡፡
**አመንሽዋ**፡ ገንዘቡ በጄ ሳይኖር ምን አድርጊ ነው የሚሉት ምን ግራ የገባው ነገር ነው እቴ፡
**ጨቡዴ** እንግዲህ ዛሬ አልከፍልህም ማለትዎ ነዋ የሚሉት ምን ግራ የገባው ነገር ነው እቴ
**ጨቡዴ፡** ነገሩ እንደዚህ ከሆነ እኔም አልሔድ፡ ገንዘቤን እስከቀበል ድረስ እዚህ እቀመጣለሁ፡፡/ ይቀመጣል/ ተገገ ወዲያ እከፍልህ አለሁ ብለውኝ የለም መልካም ፡ ጥሩ እስከ ተነገ ወዲያ ድረስ እዚችው ቁጭ እላታለሁ፡፡ /ዘሎ ብድግ ይላል/ አይደለም፣ ነገ ወለዱን ለርሻ ባንክ መከፈል አለብኝ የለብኝም ወይስ የቀልዴን የመስልዎታል
**አመንሽዋ**፡ ጨዋ ሴት ወይዘሮ ፊት ቀርበው ጨዋ ሰው መሆን የሚችሉ ሰው አይደሉም ግልጥ ነው፡፡
**ጨቡዴ** ተሳስተዋል እሜቴ፡ ጨዋ ሴት ወይዘሮ ፊት ባለበት ነወ ታደያ፡
አመንሽዋ የለም አታውቁም፡፡ ባለጌ አሳዳጊ የበደለሁ ሰው ነዎች እርስዎስ ፡ጨዋ ሰው በዚህ ዓይነት ቋንቋ ከጨዋ ሴት ወይዘሮ ፊት አይናገርም፡፡
ጨቡዴ- ግሩም ነው ድንቅ ታዲያ በምን ዓይነት ቋንቋ ላነጋግርዎ በፈረንሣይ ነው በእንግሊዘኛ ማዳም ይቅርታ፡ አስቸግሬዎት እንደሆነ፡፡ አላላ፡ የዛሬው ቀን አየር ጣዕሙ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ሽቶ ሽቶ ይላል፡፡ የለበሱት ከል ምንኛ ያምርብዎታል /እግሩን ያካል/
አመንሽዋ ይኼ የባለጌ ፈሊጥ የጅል ዘዬ ይባላል፡፡ ድንቄም ጨዋ ሆናለች እቴ፡

ጨቡዴ፡ /ያሾፍባታል/ ይኼ የጅል ፌሊጥ የባለሄ ዘይ… ደሞ ጨዋ ሴት ወይዘሮ፡ እሜቴ እኔ ያኂቸውን ጨዋ ሴት ወይዛዝርት ያህል ድምቢጥ ወፍ አላዩም እርስዎ፡፡ በሴት ምክንያት ሶስት ጊዜ በጠብ ጋር ሽጉይ ተማዝዤለሁ ፣ አሥራ ሁለት ሴት ንቂ ትቻለሁ፣ ዘጠኝ ሴት ንቆ ትቶኛል፡፡ መርጠሩሳ ድሮ ባይጠና ሆድነቴ ዘመን በርግበነቱ ጊዜ ቃሌን እንደማር አጣፍጬ ዳስ ያስገኘሁ መስሎኝ ሳይጠሩኝ እቤት ሳይልኩኝ ወዴት ብዬ እኛ ነሰቼ ጫማ ሰሜ ሳይልኩኝ ወዴት ብዬ፡ እጅ ነሰቼ ጫማ ሰሜ ለሴት የተገዛሁበት የሞኝቴ ወራት አልፏል፡፡ ያን ጊዜ ሴት ስወድና ፍቅር ሲይዘኝ ነፍሴ ልትወጣ ትደርስና ጨሬቃን በኃዘን ፈዝዤ ዓይን ዓይኗን ሳስተውላት ብስጭት ስል ውሃ እሆንና እንደ በረዶ ኩምትርትር እል ነበር፡፡ ሳፈቅር እንደ እብድ ለስሜቱ ፈረስ ልጓም

እንዳጣለት ሰው ነበርኩ፡፡ ኧረ ምኑ ቅጡ ድራ

**አመንሸዋ፡** እንግዲየስ ልጠይቅዎት ፡፡ አንደርስዎ ሐሳብ እንግዲህ በፍቅር ታመኝ የሆነው የማማግጠው የማይወሰልተው ማን መሆኑ ነው ወንድ እንዳይሉኝ ብቻ

**ጨቡዴ** መጠርጠሩ አዎን ወንድ ነው

አመንሸዋ ወንድ ወንደ እኮ/መሪር ሳቅ ትስቀለች/ ወንድ በፍቅር ታማኝ ነው፣ ወንድ አይማግጥም ፣ወንድ አይወሰልትም/ እንዲህ ነው ጨዋታ፡፡ /ትግላች/ ኧረ ለመሆኑ ይህን ደፍረው የሚገገሩት ከማንኛዉ ዳኛ በተሰጠዎት ሥልጣን ነው ደሞ ወንድ ብሉ ታማኝ የማይወሰልት ጨዋ፡ እንዲያማ ልንገርዎት፡ ከማውቃቸው ወንዶች ሁሉ በምንም በምንም ከሟቹ ከባሌ ከግራዝማች እንደሻው ከእግረ እጣኪ የሚደርስ አንድ ሰው የለም፡፡ ግራዝማች ሁሉንም ይበልጣቸዋል፡፡ እኔም በኃለ ስሜቴ በሙሉ ልቤ በሞላ ነፋሴ ወደድኩት፡፡ ልጅግር እንደመሆኑ መጠን ጥልቅ ሰሜት ያለኝ ሴት ልጅ በመሆኒ

ለክ ወጣትነቴን ደስታዩን ህይወቴን ካባቴን ሰጠሁት፣ የኑሮ ጓደኛ ሆኑኩት፣ እንደ ጣዖት አመለክሁት… ታደያስ በኂላስ ምን ተደረገ ይመስልዎታል

ይህ የወንዶች ንጉስ አቶ ወደር የለህ ገና ሀ ሲባል ጀምሮ ለካ ያለአንዳች ይሉኝታ ሊያታልለኝ ኖሯል፡ ከሞተ በኂላ የቤት ዕቃ ሰናናፍርስ የጽሐፊት ጠረጴዛውን ኪስ ሳብ ባደርገው፡ የተዘረገፈው የፍቅር ደብዳቤ አንድ እንቅብ ሞላ፡፡ በህይወቱ ሳለማ የሚሠራውን ሥራ አሁን ሳስታውው ይዘገንነኛል እኔን ብቻዬን እባዶ ቤት ጥሎ ሁለት ሳስት ለስት አራት አምስት ሣምንት እልም ብሉ ይጠፋል፡፡ ዓይኔ ሲያይ እፊት ከሌላ ሴት ጋር ይደራ ነበር ፡፡ በኔ ላይ ውሽማ መቅበጡን መወሳለቱንም አውቃለሁ፡ በገንዘቤ አሥረሽ ምችው አለበት፣ እኔ ግን ይህ ሁሉ ሲሆን መውደዴን አላስታጎልኩም፣ ታማኝነቴን አላጎደ ልኩም፡፡ ይህ ብቻም አይደለ ፣ሞተ፡፡ ቢሞትም እስከ አሁን ታማኝነቴን አላጎደልኩብትም፡፡ ወደፊትም አላጎበትም፡፡ ለዘላለም ከዚህ ካጥር ግቢዬ አልወጣም፣ ከሌን የማወልቀው የለት ሞቴ ለትግቡ መሬት ሰባል ብቻ ነው፡፡

ጨቡዴ፡/በንቃት ይሰቅባታል/

ከል፡ ከል አሉኝ አይደለም እሜቴ ፣ ለነገሩ ማን እመስልዎለሁ እኔ ከል ለብሰው የሚሞነሞበት ከጠር ግቢዎ የማይወጡበት ምክንያት ምን እንደሆነ የማይገባኝ ይመስልዎታል አውቂ ብዎታለሁ ወዛ አጠሁትና ይመስልዎታል አውቂ ብዎታለሁ አጣሁትና ለመመሣጠር ነው ለመራቅ ለመቅለስለስ፡፡ አንዱ የፈረደበት ተማሪ ወዳ ግጥም ሞጫጫሪ ደራሲ በዚህ ቤት አልፎ አምም ሲሄድ የተዘጋውን መስኮት ይመለከት ሊያደንቀ እንደዚህ ብሎ ግምጥም ይገጥም ይሆናል

ከሟች በሏ ጥናት የነማ በአር ግሲ ተቀብራ ከነነፋሷ ወይዘሮ ቆንጆት የመነነችው

የምትኖረው እዚሁ እኮ ነው፡

እባክዋን እንዲህ ያለውን ብልጥነት እናውቀዋለን አላጠነጠውም

**አመንሸዋ** /ትላላች / ምን ፡ እንዴጽ ይበሉ እንዴት እንደ ቢደፍሩ ነው እንደዚህ ብለው የሚናገኝ፡፡

**ጨቡዴ፡-** አዎ፣ ከነነፋሶ ተቀብዋል መንነዋል ባሕታዊ ሆነዋል፣ ዓይንዎና ቅንድብዎን መኳኩሉን ግን አልዘነጉትም፡፡

**አመንሸዋ** ምን ቆርጦዎት ነው ቁርጥ ቢያደርግዎት ነው ደሞ እንዲህ የሚናገኝም በሉ

**ጨቡደ** ፦ አዎ ከነነፋሶ ተቀብረዋል መንነዋል ባህታዊ ሆነዋል፡ ዓይንዎና ቅድድዋን መኳኳሉን ግን አልዘነጉትም፡፡

አመንሸዋን ምን ቆርጦዎት ነው ምን ቁጥር ቢያደርግዎት ነው ደሞ እንዲህ የሚግገሩኝ በሉ

ጨቡዴ አይሉሁ እባዝዎን መሬት ጠባቂ አሽከርዎ አይደለሁመ፡1 ነገሬ ቀጥተኛ ነው በኔ ቤት አካፋ አካፊ ነው ዶማ ዶማ ነው፡፡ በኔ ቤት አካፍ አካፋ ነው ዶማ ዶማ ነው፡፡ ሴት አይደለሁም፣ ፊት ለፊት እውነቱን በግልጥ መግግር ነው ልምዴ፡፡ ስለዚህ አይጨሁ እባክዎ

**አመንሸዋ** የሚጦሁት ራስዎ እኔ አልጦህኩም አሁን ብቻ ይሄዱልኝ ሰላም አይንሱኝ

**ጨቡዴ**፡ በግድዋ ይከፍሉኛል፡፡

**አመንሸዋ** እኔ ደሞ እልህዎን ባለስጨርስዎ ምግለች ይበሉኝ አንዲት ሳንቲመ ቤሳ አልሰጥዎትም ብቻ አሁን ይሂዱልኝ

**ጨቡዴ** ባልዎ ወይም እጮኛዎ አይደለሁም እንደዚህ ያለው ታላቅ እድል አልተሰጠኝም ስለዚህ አይነትርኩኝ... /ይቀመጣል / ንትርክ አልወድም፡፡

**አመንሸዋ**/ የንደት ሲቃ ይይዛታል/ ቁጥ ..ማለት ዎ... ነው

**ጨቡዴ** ቁጭ ..ማለቴ .. ነው

አመንሸዋ በጨዋ ደንብ ልጠይቅዎት ይውጡልኝ ከቤቲ፡፡

**ጨቡዴ**

ገንዘቤን ይሰጡኝና፡፡ /በጎን ለራሱ/ ፈውፊ/ የያዘኝ ንዴት ፡፡ ሰይጣኔ መጥቷል፡፡ የያዘኝ እንዴት ብታዮት!

**አመንሸዋ** እንዲህ እያለ በብልግና ዓይን አውጣነት ታይቶ ይታወቃል አያናግሩኝመ አለሰማዎትም፡፡ በህግ አምላክ ይውጡ ፀጥታ /ይሆናል/ አላዋጣም ነው ? እንቢ ነው፡፡

**ጨቡዴ** አዎን፣እንቢ፡፡

**አመን ሸዋ** እንቢ? አሻፈረኝ

**ጨቡዴ** አዎን፣ አሻፈረኝ፡፡

**አመንሸዋ** መለካም፣ ደና፡፡

/ሉቃስ ይገባል/

እነዚህን ሰዎች በሩን አሳያቸው

**ሉቃስ**፦ ጨቡዴ ይጠጋዋል ጌታው፣ ሄድ ሲባሉ እባክዎ ይሂዱ፡፡ እናንተ ... መሆን፡፡

አያስፈልግም

**ጨብዴ** /ብድግ ይላል/ አፍህን ዝጋ ማንን ይመስልሃል የምታናግረው ?የደግ አመድ ነው የምነግርህ

ለቡዙ በእጁ ይደገፍለ/ ኧረ ያብን ተከለ ሐጥማኖት ያለህ ያብነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያለህ እግዚኦ ማረነ ክርስቶስ ልቤን .. ልቤን ውጋቴ ተቀሰቀሰብኝ/ እሶፋው ላይ እንዘጭ ይላል/ አሞኛል... ታመምኩላችሁ.. ትንፋሽ ... ቁርጥ..ቁርይ ይል ጀመር ልቤን..

**አመንሸዋ** ሀብቴ የታለ? /በመስኮት ትጮዋለች /ወለቴ፡ ወለቴ፡ ሀብቴ፡

**ሉቃስ** ኡፍ፡ እፎይ፡... ሁሉም ኩሽም ለቀማ ሔደዋል ... ማንም ያለ .. ውሃ እባችሁ ውሃ፡

**አመንሸዋ**.../ጨቡደን /ይውጡ ነው የምለው ዛሬ፡

**ጨቡዴ**፡ በጨዋ ደንብ ቢያናግሩኝ አይከፋም፡፡

**አመንሸዋ** /በቁጣ እጅዋን ጨብጣ በእግሯ መሬቱን ትደበድላለች /ዳንዴ ነዎት ዳንዴ አውሬ ዳረጉን ጭራቅ

**ጨቡዴ**፡ ምን ምን አሉ ይበሉ ?እስቲ ይመሱት

**አመንሸዋ** አውሬ ... ደራገን.. ጭራቅ...ነዎት አልኩዎ፡

**ጨቡዴ**፡/በግልፍታ ይጠጋታል/ ይቅርታዎንና በየትኛው ህግ ነው እንዲሰድቡኝ የተፈቀደልዎ?

**አመንሸዋ**፦ አሳምሬ ሰድቤዎታለሁ፡፡ ታዲያስ? ምን ይመጣብኛል? የምፈራዎ ይመስልዎታል?

**ጨቡዴ**፡ ገና ለገና ለስላሳ ቀለስላሳ ፍጥረት ስለሆኑ እደፌለገዎ ሲሳደቡ የሚችሉ ይመስልዎታል? ይሰሏ ይዋጣልና፡ አሁን እዚሁ ይዋጣልናል፡፡

**ሉቃስ**፡ እግዚዎ ማረነ ክርስቶስ ፡ ኧረ የጣድቃን የሰማዕታት ያለህ ውሃ ውሃ ..ልቤን..

**አመንሽዋ**፡ ገና ለገና ጠብደል ዳንዴ ነኝ ብለሁ እነደ ፈረ በሬ ቢደነፋ የምራዎ ይመስልዎል መሰለኝ? እ? የኛ ዳንዴ፡

**ጨቡዴ** ይዋጣልን ብየዎታለሁ ፣ ማንም ቢሆን እኔን ጨቡዴን ሰድቦ እንዲያመልጥ አይፈቀድለትም፡፡ እርስዎ ሴት ቢሆኑና ልጅ ደከማ ነች ቢባል ይሄ በኔ ዘንደ ምንም ልዩነት የለውም፡፡ ይዋጣልን ብየዎታለሁ፡፡

**አመንሽዋ** /በጩሕት/ አውሬ ጭራቅ ፣ ደራጎን ፣ ጭራጭ ጭራቅ/

**ጨብዴ** ሰው ባይኖር በበለጠ ሰወ ክብር በነካ ትጋውን የሚከፈልወንድ ብቻ ነው የሚባለው ከንቲ አምኮ እስከ አሁን መቫር ነበረበት እኩልነት ከተባለ እኩልነት ነው፡፡ ይዋጣልን ብየዎታለሁ በሽጉጥ፡፣

**አመንሽዋ**፡ በጥይት አይደለም የሚሉት? እንታኮሰው አይደለም?መልካም ፡ ጥሩ ነው፡፡

**ጨቡዴ** ይዋጣልን በሽጉይ አሁኑኑ

**አመንሽዋ** አሁኑን ይዋጣልናል የባሌ ሽጉጥ አለ፣ ሔጂ አመጣሉሁ/ ራመድ ራመድ እያለች ትሄድ ዘወር ብላ ቆም ትላለች/ ይህን የበሬ ግምባርዎን ነበጥይት ባልበሰልዎ ዛሬ ቅዱስ ጊዮርጊስ አይለመነኝ፣ እንዲ ነችግ **አመንሽዋ**/ ትወጣለች/

**ጨድዴ** እንደ ቆቅ ነው ጠብ የማደርጋት፡፡ ሕፃን አይደለሁም አላዝላትም፡፡ በኔ ዘንድ ደካማ የሚባል እንስታይ ወይ ተባዕታይ ፆታ የለም፡፡ ሁለቱም ያው ነው እኩል ነው፡፡

**ሉቃስ**፡ ጌቶች የኔ ጌታ እባክዎን … /ይምብረከካል/ ይዩኝ ተምበርክኬያሉሁ እጣማዎ ወድቄያለሁ፡፡ ለሽማግሌ ይፈሩ እባክዎ ለኔ ቢሉ ይሄድ ይውዩ  ከዚህ ቤት ፡፡ ቅድም በድንጋጤ ሊገን ነበር፡ አሁን ደሞ በሽጉይ ሊታኮስ ነው፡

**ጨቡዴ**፡ /ሉቃስ አይሰማውም/ በጥይጥ ይዋጣልናል፡፡ የእኩልነት መብት ይሳል ይኼ ነው የሴት ልጅ ነፃነት ይሉሻል ይኼ ነው የሴት ነች ፊቷ እንደ ፍም ጋለ ዓይኗ ተግ አይልሳችሁም? ቱግ አለች፡፡ ይዋጣልን ብላት ውርርዴን አልፈራችውም ተቀበለሀት ፣ ይዋጣልን አለች ቀኝ እጄን ለሰይፍ የምሰጥበት ነገር ነው፣ እንደች ያለችዋን የያሁት ከተፈጠርኩ ገና ዛሬ ነው፡፡

**ሉቃስ** የኔ ጌታ፣ እባክዎ፣ ይሂዱ፡1 አሁን ከሔፋ፣ በስሎቱ ሁል ቀን አነሳዎታለሃ ስለደግነትናዎ…

**ጨቡይ**፡- ሴት ማለት እንዲህ ነው፡ የሚገባኝ እንዲህ ያለው ነው፡፡ ጥንተ ንጥሯ አስሊዋ እውነተኛዋ ሴት ይች ነች ፡፡ መች ኮሶ ፊት ወኔ የለሽ አልቃሻ ሕፃን ነችና? እሳት ነች እንጂ ባሩድ

**ዳንዴው**…ግሎ ጣት የሳበው ምላጭ በተኮሰው ጥይት ተመትቼ ብወድቅ፣ ምን ያህል ደስታ እንደሚበጠኝ አንቺ አታውቂም ፡፡ ላንዳፍታ ረጋ በይ አሰቢና ፣ አሀኑኑ፡ እዚሁ ቁርጡን አስታውቂኝ፡፡ ዛሬ ከዚህ ቤት ከወጣሁ እንደ ወጣሁ ቀረሁ ማለት ነው ዳግመኛ አንተያየም፡፡ ቁረጭ/ ወሰኝ ባለ መሬት ነኝ ባለቀላድ፡ የጨዋ ወገን ነኝ አሥር ሺህ ጥሬ ብር ባመት ገቢ አለኝ፡፡ ቤሳ ወደ ሰማይ ብትወረወር፣ ምድር ሳይነካ እምብርቷን በጥይት የምበሳ አነጣጣሪ ቅልጥም ሰባሪ ተኳሽ ነኝ፡፡ ምን ምን የመሰሰለ ሰንጋ ፈረስ ስጋር በቅሎ አለኝ፡፡ ሚስቴ ሁኝ፣ ላግባሽ፡፡

**መንሽዋ**፡- /በቁጣ ሽጉጥዋን እያወዛወዘች/ እንታኮሰታለን፡፡ ና እንጆ ሽጉጥህን ያዝ፡

**ጨቡዴ**  ራሴ ዞሯል፣ አንዱም አይገባኝ /ጮሆ ይጣራል/ ማነህ ልጅ ፡ እስቲተ ውሃ፡መንሽዋ /በጨኸት/ ና በሽጉጥ ይዋጣልግል

**ጨብዴ** ልቤን ሰውሮኛል፡ እንደቂል ፍቅር ማርካኛል፡፡ /እጇን ይይዛታል ያስምማትና ትጮሆ ይጣራል/

**መንሻዋ**፡ ኡ-አ አአአ እጄን ሰበርዘው

**ጨቡዴ** ወደደኩሽ ፡፡ /ይምበረከካል/ ከተወኩ እዳንዊ እንደዛሬ ወድጄ ጠልቼ ተቆራርጫለሁ፡፡ ዘጠኝ ሴቶች ወደውኝ ጠልተውኝ እርግፍ አርገው ትተውኛል፡፡ ብቻ አንቺን እንደምወድሽ የወደድኳት ሴት አንድ አትገኝም ፡፡ ቅልስልስ ናየረገኛል ቀለጥኩ፡፡ እንደ ቅቤ ውሃ ሆንኩልስ ይኸው እንደቂል ተምበርክኬ  ሚስቴ ሁኝልን

እላለሁ እለምናለሁ። ማፌሪያ ነገር ነው። ፍቅር  የሚሉት ነገር በደጄ ላይዞር አምስት ዓመቱ ማላአድርጌ ነበር። አሁን በድንገት ኀርፍ ወሰደኝ እላላሁ እለምናለሁ። ማፈሪያ ነገር ነው።  ፍቅር የሚሉት ነገር በደጄ ላይዞር አምስት ዓመቱ ማላአድርጌ ነበር። አሁን በድንገት ኀርፉ ወሰደኝ። መሰረቴን አናጋው። ይኸውልሽ፡ አንቺ ቀኝ እጄን በጋብቻ ሰጥቼሻለሁ.. ታዲያስ? እሺ ነው እምቢ?...  ተይዋ ይቅራ ደኅና ዋይ  መሔዴ ነው /ይነሣና ወደ በሩ ይገሠግሣል/

**መንሸዋ**፡ ቆይ እስቲ ... አንድዬ..

**ጨቡዴ** ፡ /ይቆማል/ ታዲያስ

**መንሸዌ፡-** ተወው ግድየለም ሂድ፡... የለም አንዳፍታ ቆይና አይደለም አትሂድ /የያዘችውን ሽጉጥ እጠረጴዛው ላይ ትወረውራለች /ሽጉይ የማለትን የሰጣን ዕቃ የጨበጥኩበት ጣቴ ደንዝዟል/ ክንዴቷ የተነሣ የገዛ መሐረቡን ቦጫጭቃ ትጥለዋለች/ ምን እዚያ ይገትርሃል? ውጣ፡

**ጨብዴ፡-** ደኀና ሁኝ

**አመንሸዋ፡** አዎ ሂድ ፡ ሂድ፡ ትጮሃለች፡ ታዲያ ወዴት ነው የምትሄደው? ቆይ እስቲ አንዳፍታ.. የለም፣ አይሆንም፣ ሒድ ወዲያ.. በንዴቴ ተቀጥያለሁ፡ ዋ፡ አጠገቤ እንዳትደርስ እንዳትጠጋኝ ኋላ፡

**ጨብዴ፡** /ይጠጋታል/ የኔ ጉድ፡ ይዘገንነኛል፣ እንደ ሕፃን በፍቅር መያዝ መምበርከክ ያንገፈግፋኛል /በደፋርነት/ ወደድኩሽ። አንችን ያሰወደደኝ ከቶ ምን ይሆን ? ነገ ወለዱን  ለረሻ ባንክ መክፈል አለብኝ። ሰብሉን ደሞ አጨዳ ጀምረናል። አንቺ ደሞ አንቺ እዚህ በሰራሁት ስራ ህሊናዬ ዘላለም ሲወቅሰኝ ይኖራል።

**አመንሸዋ**፡ ወግድልኝ፡ አትንዛኝ እጅህን ወዲያ ሰብስብ ታስጠላኛለህ። በጥይት ይዋጣልናለ /ሲሳሳሙ ሉቃስ መጥሪያ ይዞ ፣ አትክልተኛው ዶማ ይዞ፣ በቅሎ ቤቱ አለጋ ይዞ፣ ሙያተኞቹ ደግሞ አካፋቸውን ይዘው ገባአሉ/

**ሉቃስ** እግዚኦ ማርነ ክርስቶስ! አረ የፃድቃን ያለህ! የሰማህታት ያለህ! ጥግ ይዞ /ይቆማል/።

አመንሸዋ /በዓይን አፋርነት/ ሉቃስ፤ ከከብቶቹ ጋር ሂድና፤ ለጉራቻ ዛሬ ገብስ እንዳይሰጡት ብላለች በላቸው።

------------------------ ተ ፈ ፀ መ ------------------------------

## የግለፈተና ጥያቄዎች መልሶች

### ግለፈተና አንድ

#### መመሪያ አንድ

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት

#### መመሪያ ሁለት

1. ትውቂያ፣ ትውስብ፣ ልቀት
2. ተመድራኪነት
   - በቡድን ይዘጋጃል
   - ቀውስ፣ ውዥንብርና ግራ መጋባት የተሞላ ነው፡፡
   - የተዘወተረ መሠረታዊ መዋቅር አለው
   - በድርጊት የታጀበ የአተራረክ ብልሃት አለው

3.ተመድራኪነት

### ግለፈተና ሁለት

#### መመሪያ አንድ

1. እውነት
2. እውነት
3. ሀሰት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. እውነት

#### መመሪያ ሁለት

1. አፋጀሽኝ እና አለም አታላይ
2. የአውሬዎች ተረት፤ በተክለሃዋሪያት ተክለማሪያም
3. አኪለስ፣ ሶፎክልስ
4. አቤት ባዮቹ (the Persians)
5. የህንድ ሳንስክሪት ድራማ

### ግለ ፈተና ሶስት

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. ሀሰት
6. እውነት
7. እውነት
8. እውነት
9. ሀሰት
10. ሀሰት

### ግለ ፈተና አራት

1. ሀሰት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት
6. እውነት

### ግለ ፈተና አምስት

1. ሀሰት
2 .እውነት
3. እውነት
4. ሰእውነት
5. እውነት
6. እውነት
7. ሀሰት
8. እውነት
9. እውነት
10. እውነት

## የሞጅዩሉ ማጠቃለያ

## ውድ የዚህ ሞጁዩል ተከታታይ

የተውኔት መግቢያ ኮርስ ሞጁዩል በዚህ ተጠናቃል፡፡ በሞጅዩል ውስጥ ሰባት ምዕራፎች ተነስተው የነበረ ሲሆን፤ ሁሉም ምዕራፎች ከተውኔት ጋር የተያያዙ ሀሳቦች ቀርበውባቸዋል፡፡

በዚህ ሞጁዩል በቀረቡት ሰባት ምዕራፎች ውስጥ በርካታ እውቀት እንደቀሰምክ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ የየምዕራፎቹ አሰዳደር ከተውኔት መሰረታዊ ሀሳብ በመነሳት ጠንከር ወደሚሉት ጉዳዮች የሚሄድ በመሆኑ ከቀላል ወደ ከባድ ሀሳቦች እንድትነሳ ያበረታታህ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ኮርስ ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦችን የተረዳህ ተረድተህም ወደቀጣይ ምንባቦች የተሸጋገርክ እንደሆነ እናምናለን፡፡

## ውድ የዚህ ሞጁዩል ተከታታይ!

ይህ ኮርስ እንደሚያሳየው ስለተውኔት መግቢያ የሚሆኑ ሀሳቦችን ለማንሳት ሲባል ብቻ የቀረበ ነው፡፡ ስለተወኔት ጥልቅ ንባብ እና ምርምር ለማድረግ መንገድ የሚከፍቱ ሀሳቦች ለማቅረብ የተሞከረውም ከዚህ የመግቢያነቱ ባህሪ በመነሳት ነው፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው ሀሳብ አንጻር በሞጅሉ መጀመሪያ ላይ ስለተውኔት ምንነት፣ ባህሪያት፣ ታሪክ፣ አላባውያን እና መዋቅራዊ ክፍሎች ለማንሳት ተሞክራል፡፡ በቀጣይም የተውኔት ዘውጎች፣ አጻጻፍ ደረጃዎች እና መሰረታዊ የአመደራረክ ጥበቦች በሞጅሉ ተዳሰዋል፡፡ እነዚህን ሀሳቦች በጥልቀት ለመረዳት ቀጣይ የግል ንባቦች እንዲኖሩ ይመክራል፡፡

በሞጅሉ ውስጥ የቀረቡና ወደ ገለጻ የሚወስዱ ጥያቄዎች፣ ገለጻዎች፣ መልመጃዎች፣ የማገናዘቢያ ነጥቦችና ግለፈተናዎች በሞጅሉ የተነሱትን ሀሳቦች ለመጨበጥ እንደረዱህ እናሳስባለን፡፡ ከዚህ ማጠቃለያ በሃላ የሰፈሩት ሁለት ርዕሰ ጉዳዮችም ኮርሱን በሚገባ ለመረዳት ወሳኝ ነጥቦች ናቸው፤፡ የመጀመሪያው የግለፈተናዎች መልሶች ሲሆኑ ምን ያህል በሞጅሉ የቀረቡትን ሀሳቦች እንደተረዳህ ጥቁምታ ይሰጡሃል፡፡ ሁለተኛው ዋቢ ጽሁፎች ናቸው፡፡ ይህ ሞጅሉ በዋነኛነት በነዚህ ጽሁፎች መነሻነት የተዘጋጀ በመሆኑ ጽሁፎቹን ፈልገኅ በሚገባ ብታነባቸው በእርግጠኝነት የተሻለ እውቀት እንደምታገኝ እናረጋግጣለን፡፡ መልካም የንባብ ጊዜ ይሁንልህ፡፡